
« የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ! »

በአንዱ አምላክ በእግዚአብሔር ገላጭነትና ትዕዛዝ የተጻፈ፤

ፀሐፊዉ ከእግዚአብሔር ባሪያ አንዱ፡፡

ከሰዉ መገኛ ከነፍስ መዳኛ ሀገር ከኢትዮጵያ የተገኘ፡፡

# መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ያሉት ሚጢጢዎቹ ሰማያት፣ ዓለም፣ ምድር፣ ገነት፣ ሲኦል፣ ማረፊያ ቦታና ገሃነም እሳት በምን መልኩ እንደሚገኙ የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ




ታህሳስ ፳፻፫ ዓ. ም. (ታህሳስ 2003 ዓ.ም.)


**ኢሜል፡** *servantofgod10@yahoo.com*

## ማዉጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| የፊት ለፊት ሽፋን | 1 |
| ማዉጫ | 2 |
| ማስታወሻ | 3-4 |
| ማሳሰቢያ | 5 |
| መቅድም | 6 |
| መግቢያ | 7 |
| ክፍል አንድ | 8- 28 |
| ክፍል ሁለት | 29-54 |
| ክፍል ሶስት | 55-66 |
| ክፍል አራት | 67-76 |

## ማስታወሻ

-ይህ መጽሐፍ የተጻፈዉ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሆነ ማንም ሰዉ ለንግድ ወይንም ለትርፍ እንዳያዉለዉ።

-ማንም ሰዉ ከመጽሐፉ አንዳች ቃል ሆነ ዐረፍተ ነገር እንዲሁም አንቀጽና ምእራፍ ሳይቀንስና ሳይጨምር ለወገኖቹ ለኢትዮጵያዉንና ለዓለም ሕዝብ በኢንተርኔት፣ በሲዲ፣ በወረቀት እያባዛ፣ በመጽሐፍ መልክ፣ ባጠቃላይ በማንኛዉ መልክ ማስተላለፍ ይችላል።

- በመጽሐፍ መልክ የሚያሰራጭ ሰዉ የድካሙን ዋጋ ብቻ በማተሚያዉ ዋጋ ላይ በመጨመር ማሰራጨት ይኖርበታል እንጂ ለገቢ ማግኛና ለትርፍ ብቻ መሰብሰቢያ የሚያዉለዉ ከሆነ ዋጋ እንደሚከፍልበት ሊያዉቅ ይገባል።

እንዲሁም ማንም ይሁን ማን ከመጽሐፉ በራሱ ስልጣን አንዳች ቢቀንስ ሆነ ቢጨምር በምድርም በመለኮት ስልጣን ታስሮ ፍዳዉን እንደሚቀበልና ነፍስ ከሥጋዉ ከተለየች በኋላ ደግሞ ነፍሱ በረቂቅ አካል ተገልጻና ነጻነቷ ተገድቦ በአንድ ቦታ ላይ በመቶ እጥፍ ፍዳዋን እንደምትቀበል ሊያዉቅ ይገባል።

ስለዚህ አንዳች ከመቀነስና ከመጨመር ይልቅ «አልቀበለዉም» የሚል ሰዉ ከመለኮት ፍርድ ባያመልጥም ፍርዱ ግን እንደሚቀልለት በዚሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ።

ጸሐፊዉ ማንም ሰዉ እንዲያሳትመዉና ለወገኖቹ ለአዳም ዘር እንዲያደርስ ፈቃዱ የሆነና አምስት ሳንቲም ከማንም ሰዉ እንደማይፈልግ በዚሁ ለመግለጽ ይወዳል። ዋናዉ ፍላጎቱ የአዳም ዘር በእግዚአብሔር መልእክት ተጠቅሞ ራሱንና ወገኑን ከጥፋትና ከመደምሰስ እንዲያድን ብቻ ነዉ። ለማሳታምና ለማሰራጨት የሚፈልግ ሰዉ በግልጽ ማንነቱንና አድራሻዉን በኢ-ጦማር

(በኢሜል) አድራሻዬ አሳዉቆኝ ከእኔ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ማሳተምና ማሰራጨት ይችላል:: ምክንያቱን የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መልክ እናዳያሳትሙትና ለንግድ ስራ እንዳያዉሉት፣ እንዲሁም እግዚአብሔር የፈቀደለት አካል ወይንም ግለሰብ ብቻ እንዲያሳትመዉ ለማድረግ በማሰብ ነዉ::

-የእግዚአብሔርን መልእክት መቀበልና አለመቀበል የእያንዳንዱ ሰዉ ነጻ ምርጫ ነዉ:: በእግዚአብሔር መልእክት ላይ መቃወም ግን በራስ ላይ መከራና ችግር እንዲሁም ጥፋት ማምጣት እንደሆነ ሁሉም ሰዉ ሊረዳዉ ይገባል:: ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ላይ በድፍረት የሚቃወም ሰዉ በምድርም በሰማይም በመለኮት እሳት ሰንሰለት የታሰረና ለእያንዳንዱ የዐመጻዉና ክህደት ተግባሩ በምድርም በሰማይም ዋጋ የሚከፍልበት መሆኑን ሊያዉቅ ይገባል::

-ጸሐፊዉ ከዓለም አንዳች ነገር ፈልጎ እንዳልጻፈዉና ከአምላኩ ስለታዘዘ ብቻ መልእክቱን ለወገኖቹ ለአዳም ዘር ለማድረስ እንደፈለገ ሁሉም ሰዉ እንዲያዉቁለት ይፈልጋል::

- በዚህ መጽሐፍ ሆነ መልእክት ለሚመጣ ማንኛዉ ነገር ተጠያቂዉ እኔ መልእክቱ አምጪዉ ሰዉ ብቻ መሆኔን ለመግለጽ እወዳለሁ:: ለምታሳራጩላቸዉ ሰዎች የኢሜል አድራሻዬን መግለጽ ትችላላችሁ::

መልካም ንባብና መረዳት፣ማስተዋል፣ ለወገኖቼ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ በሙሉ!

## ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈዉ በእግዚአብሔር ገላጭነትና ትዕዛዝ ሲሆን ይህም ልክ በአንደበታችን ድምጽ ሳናሰማ በሕሊናችን ብቻ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ስናቀርብ እንደሚሰማን ሁሉ፤እግዚአብሔር ካለ ድምጽ በሕሊናዬ የተናገረኝና የገለጸልኝን ነዉ የጻፍኩላችሁ። «አንተ ማነህና ነዉ እግዚአብሔር የሚናገርህ?» የሚል ሰዉ ካለ ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻዉ ክፍል በትዕግስት ሲያነብ ማንነቴን በሚገባ ይረዳል። ስለ ራሴ የምለዉ ነገር ቢኖር በመንፈሳዊ አገልግሎት ዉስጥ የሌለሁ ተራ መሃይም ምዕመንና በአለማዊ እዉቀትም እዚህ ግባ የሚባል እዉቀት የሌለኝ ከስነ ጽሁፍ ሙያ ዉጭ ባለ ስራ የተሰማራሁ፤ በአለም ዉስጥ ኑሮዬን ለማሸነፍ የምወጣ የምወርድ ሰዉ ነኝ።

እግዚአብሔር ጸሐፊዉን ያጻፈዉ በሚያዉቀዉ የእዉቀት ደረጃ ሲሆን የማያዉቃቸዉን ቃላት ደግሞ ትርጉማቸዉ ተገልጾለት ስለሆነ፤ ግልጽ ያልሆኑ ቃላት ካሉ በመጽሐፉ ላይ ምን እንደሆኑ በግልጽ ተጽፏል።

የሰዉ ዘሮችን ሁሉ ወደ ሕያዉነት ህይወት እንዲያመጣ፤ እዉነት እንድትገለጽ የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ ማንም ሰዉ የባሰ ፍርድ እንዳያገኘዉ ለንግድ ወይንም ለትርፍ እንዳያዉለዉ።  ከእግዚአብሔር የሆነን ማንኛዉንም ነገር ማንም ፍጡር ሊያስቀረው ሆነ ሊያጠፋዉ ስለማይችል፤ ይህን የእግዚአብሔር መልእክት ለማስቀረት ሆነ ለማጥፋት ማንም ሰዉ ሙከራ አያድርግ። እግዚአብሔርን ማንም ፍጡር ሊያሸንፈዉ ሆነ ሊገዳደረዉ ስለማይችል ከእርሱ የሆነዉን የሚቃወም በራሱ ላይ መከራና ችግር ያመጣል እንጂ አንዳች የሚፈይደዉ ነገር የለም፤ የአለም ህዝብ አነድ ሆኖ ሊያጠፋ ቢሞክር እንኳን አይችልም።

በተረፈ የአዳምና ሔዋን ዘሮች የሆናችሁ ሁሉ፤ አባቶቼ እናቶቼ ወንድሞቼ እህቶቼ ለአጠቃላይ መልእክቱ ትኩረት በመስጠት የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራ በተስፋ ተጠባበቁ። ዲያብሎስ በአራቱም ማዕዘን በበላይ ሆኖ አለምን በሚመራበት ዘመን ፤ትዉልዱ ሁሉ ለስልጣን፣ ለገንዘብ፣ ለጥቅም፣ ለክብር፣ ለዝና ሲል ሕሊናዉን በሸጠበት ዘመን ፤የተከደነዉን የገለጠ የተሰወረዉን ያሳወቅ እዉነተኛ አምላክ ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁን።

# መቅድም

የተከበራችሁ አባቶች እናቶች ወንድሞች እህቶች በአጠቃላይ ይህን መጽሐፍ የምታነቡ ሁሉ ፤ መጽሐፉ የተጻፈዉ በስጋዊ ፈቃድ በፍልስፍና ሳይሆን በእዉነተኛዉ አምላክ በአንዱ እግዚአብሔር ገላጭነትና አሳሳቢነት ነዉ።ይህም የነበረዉን፣ ያለፈዉን፣ የአሁኑን፣ የወደፊቱን፣ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ስላለዉ ህይወት እንዲሁም ስለ አለም እዉነታ የሚገልጽ ነዉ።

በሃይማኖት ረገድ ለሕያዉነት ህይወት የሚያበቃዉንና ከእዉነተኛዉ አምላክ ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኘዉን የህይወት መንገድ በግልጽ ያስቀመጠና ትክክለኛነቱን የገለጸ እንዲሁም መሰረታዊ እምነቱን የሚያሳዉቅ ነዉ።

በጽሁፉ ዉስጥ በአንዳንድ የሃይማኖት መምህራን ዘንድ ሆነ በሌላ አካላት የማይታወቁ በጸሐፊዉም ዘንድ ቀድሞ የማይታወቁ ቃላቶችና እዉነታዎች ያሉ ሲሆን ይህም እርሱ አንዱ አምላክ የገለጸልኝና በምርምር ሆነ በፍልስፍና ሊታወቁ ሆነ ሊደረስባቸዉ የማይቻል ነዉ።

እነዚህ ቃላቶች ሆኑ እዉነታዎች በነበረዉ፣ ባለዉ፣ እንዲሁም በሚኖረዉ እዉነተኛ ሃይማኖት (እምነት) ላይ የሚቀንሰዉ፣ የሚጨምረው፣ የሚያሸሽለዉ ነገር የለም። ነገር ግን አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑ ነገሮችን ግልጽና ምሉዕ ሊያደርግ ይችላል። ስለዚህ እዉነተኛ ሊቃዉንቶችና መምህራን የሆናችዉ፤ በነበረዉ እዉቀት ብቻ በመመራት ከእግዚአብሔር የሆነዉን እዉነታ ላለመቀበል ሕሊናችሁን አትዝጉ። ብትቀበሉትም ባትቀበሉትም ለእዉነተኛዉ ድኅነት የሚቀንስባችሁ ሆነ የሚጨምርላችሁ ነገር የለም፤ እዉነተኛዋ እምነት ፍጹም መሆኗን ከማሳወቅ ዉጭ።

በመጨረሻ ለማሳሰብ የምወደዉ ማንም ሰዉ የአዳምና የሔዋን ዘር የሆነ ሁሉ ከአንዱ አምላክ እዉነታ ዉጭ ሊወጣ ስለማይችል ይኸዉም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣን፣ ከፈለገም ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፣ ሁሉ በእርሱ የእርሱ ለእርሱ የሆነ፣ ካለ እርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፣ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ ፊተኛዉና ኋለኛዉ፣ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር ፈጣሪ እግዚአብሔር አንድ ስለሆነ ሁሉም ሰዉ ከዚህ እዉነተኛ አምላክ ለተገለጸ እዉነት ሊያምንና ሊገዛ ይገባል። የህይወትን መንገድ የሚፈልግና እንደ እግዚአብሔር ሕያዉ ሆኖ በተቀደሰና በተመረጠ ህይወት ለመኖር ከፈለገ በጸሐፊዉ በኩል የተላለፈዉን የእግዚአብሔር ቃል ተግባራዊ ያድርግ።

# መግቢያ

በዘመናችን ሰዎች ከቤተሰባቸዉ በወረሱት፣ በተማሩት ትምህርት፣ በሚከተሉት ርዕዮተ አለም፣ ሕሊናቸዉ በሚቀበለዉ የእምነት ጎዳና ይጓዛሉ:: እምነት ይሁን ክህደት፣ እዉነተኛ አምልኮት ይሁን ባእድ አምልኮት፣ ትክክለኛ ይሁን ስህተት፣ ከህሊናቸዉ በላይ ሌላ የበላይ ሃይል እንዳለ በማመን አምልኮትን ይፈጽማሉ::

ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና ሕግ በመተላለፋቸዉና ፈቃዱንም ለመፈጸም ዝግጁ ባለመሆናቸዉ እንዲሁም እዉነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ምክንያት እንደ ራሳቸዉ አስተሳሰብ በመጓዝ ከህይወት መንገድ ርቀዋል:: የእዉነት መንገድ ጠፍቶባቸዋል፤ በአመጻ፣ በክህደት በሞት መንገድ ይመላለሳሉ::

ሰዎች ማንነታቸዉን ባለማወቅ ይኸዉም «ኬት መጣሁ? አሁንስ ምን እያደረኩ ነዉ? ወደፊትስ መጨረሻዬ ምንድ ነዉ?» ብለዉ ራሳቸዉን ሳይጠይቁና ሳይመረምሩ እንደ እንስሳ በደመ ነፍስ በመመላለስ ከእዉነት ርቀዋል:: ክብራቸዉንና ዉርደታቸዉን፣ ታላቅነታቸዉና ደካማነታቸዉን ዘንግተዋል:: እግዚአብሔር ያደረገላቸዉን ታላቅ ዉለታ ረስተዋል:: በመሆኑም ለማይገባ ባህርይና ጠባይ ራሳቸዉን አሳልፈዉ በመስጠት የሞት ሞትን ይሞታሉ፤ዉርደትን ይላበሳሉ::

እንግዲህ ሰዎች ሁሉ፤ ማንነታቸዉን ሊያዉቁና ክብራቸዉን፣ ደካማነታቸዉን፣ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርያቸዉን፣ ተስፋቸዉን በሚገባ አዉቀዉ ራሳቸዉን ለታላቅ ክብር ሊያዘጋጁ ይገባል:: ጥቅሙ ለራሳቸዉ ነዉና:: ከዚያ ዉጭ ሰዎች በረከሱና እዉነትን አንቀበልም ቢሉ ክብራቸዉን ያዋርዳሉ እንጂ በእግዚአብሔር ላይ የሚቀንሱት ሆነ የሚጨምሩት አንዳች ነገር የለም:: ይልቁኑ እዉነት እየተገለጸ አንቀበልም፣ እንደ ቃሉ ሆነን አንገኝም ቢሉ የባሰ ፍርድ ይጠብቃቸዋል::

እዉነትን ቢቀበሉና ቢቀደሱ በክብር በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ፤ ምክንያቱም የተከፈለላቸዉን ታላቅ ዋጋ ፍሬ ቢስ አላደረጉምና:: ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ እግዚአብሔር የፈቀደዉና የወደደዉ ተገልጿል፤ ሰማያዊ ሆነ ምድራዊ እዉነት እንድታዉቁት ቀራቧል:: ሊቀበል የሚገባዉ ይቀበለዉ:: ሊቀበል የማይፈልገዉ ደግሞ በራሱ ላይ ፈርዷልና ምርጫዉ የራሱ ነዉ:: ለአመታት በዉስጤ ተቀምጦ የነበረዉን እዉነት እንድገልጽና ተጨማሪ ምስጢራትን እንዳዉቅ ለፈቀደልኝ አምላክ ክብር ምስጋና ይሁን፤አሜን::

# ክፍል አንድ

ፍጥረታት ከመፈጠራቸዉ በፊት፣ ከተፈጠሩ በኋላ፣ አሁን ስላለዉ፣ ወደፊት ስለሚኖረዉ፣ ከሕያዉነት ዘመን በኋላ ስለሚሆነዉ የሚገልጽ፤

## ምዕራፍ አንድ

እግዚአብሔር የነበረ፣ ያለ፣ ሕያው አምላክ፣ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበትም ጊዜ የማይኖር፣ ፊተኛውና መጨረሻው እሱ ብቻ የሆነ፣ በባህርይው ሞትና እልፊት የሌለበት፣ ያለእርሱ ፍቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፣ ፍጥረታትን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፣ ከፈለገም በፈለገው ጊዜ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፣ እንደ አምላካዊ ባህርይው ማንም ሊያየው ሆነ ሊቀርበው የማይቻል፣ የሁሉ አስገኝና ፈጣሪ፣ በመጀመሪያ (ከፍጥረታት በፊት) መጀመሪያና መጨረሻ በሌለው አማናዊ ህዋ ውስጥ ብቻውን በአማናዊ ባህርይው ይኖር ነበር።

እግዚአብሔር ዘመናት የማይቆጠሩለት፣ በነበረው ሕያውነት ዘመን ውስጥ ምንም እንኳን በባህርይው ምስጉን ቢሆንም የባህርይው ተካፋይ ስሙንም አመስጋኝ እንዲሆኑ የቁጥራቸው መጠን በፈጠራቸው አምላክ ብቻ የሚታወቅ ከሰው ልጅ አይምሮ ቁጥር በላይ የሆኑ መናፍስት (መላእክት) ሕያውነት ባህርይ ያላቸው ከባህርይው አስገኝቶ በምሳሌያዊ ባህርይ እንዲገለጹ ወይንም ምሳሌያዊ ባህርይ እንዲለብሱ በማድረግ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸው ምሳሌያዊ ባህርይ በሆነው በመጀመሪያው ፍጥረት ቦታ ላይ በሰማያት ውስጥ አኖራቸው።

ሕያው በሆነ ባህርያቸው የማይለያዩት ነገር ግን በተገለጹበት ምሳሌያው ባህርይ የሚለያዩት መናፍስት (መላእክት) በሰማያት ውስጥ ራሳቸውን ሲያገኙ፤ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸውን ሲፈልጉና ሲመኙ፤ በምሳሌያዊ ባህርይው ከሌሎች በልጦ ወይንም ገዝፎ የታየው የአሁኑ ዲያቢሎስ የቀድሞው ሳጥናኤል ለሁሉ አለቃ እንዲሆን ተመርጦ የነበረው፤ ራሱን ከሌሎች መናፍስት ጋር ሲያስተያይ የበለጠ(የገዘፈ) መስሎት ስለ ታየው ቀድሞ ያልነበራችሁን (ትዕቢት) ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ ፈጠራትና የሁሉ አስገኚ ፈጣሪ አድርጎ ራሱን በመቁጠር ሌሎች መናፍስት (መላእክት) ሁሉ ለእርሱ እንዲገዙና እንዲያመልኩ መመሪያ ሰጠ።

ይሁንና ሕያው የሆነች የምታስብና የምታመዛዝን ነፍስ ያላቸው መናፍስት በጣም ብዙ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑት ምንም እንኳን በምሳሌያዊ ባህርይው ከነሱ ገዝፎ የሚታይና የበለጠ መሆኑን ቢያውቅም አፈጣጠሩ እንደነእርሱ ስለሆነ፤ ከሚካኤል፣ ከገብርኤል ጀምሮ ያሉት ከቁጥር በላይ እጅግ ብዙ የሆኑት መናፍስት የተቃወሙትና ያልተቀበሉት ሲሆን፤ እጅግ ትንሽ የሆኑት ነገር ግን በሰው አእምሮ ቁጥራቸው የበዛ መናፍስት ደግሞ በእርሱ በማመንና በጥርጥር ተቀብለውታል።

በመጨረሻ ግን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸው አምላክ ሊገባቸው በሚችል አማናዊ ባህርይውን ወስኖ በብርሃናዊ ባህርይው ተገልጾላቸው እንደ እምነታቸው ፅናት ፈርዶላቸዋል። የካዱትንና የተጠራጠሩትን ፈርዶባቸዋል።

እግዚአብሔር ለተፈረደባቸው መናፍስት መኖሪያ ይሆን ዘንድ ሁለተኛውን ምሳሌያዊ ባህርይ መኖርያ ቦታ የሆነዉን ይህችን ዓለም ካላመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የከዱትንና የተጠራጠሩትን መናፍስት እንደ አመጻቸውና ክህደታቸው ደረጃ የተሰጣቸውን ፀጋ ገፎ ከክብራቸው አዋርዶ በተጎሳቀለ ባህርይ እንዲኖሩ ወደዚህች ዓለም ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ ወደ ሆነችው ወደዚህች ምድር ጣላቸው ። እነእርሱም ቅድስናና ክብር አጡ፤ በጭንቀትና በስጋት በመከራ ሕይወት ውስጥ

መኖር ጀመሩ:: ስማቸው ርኩሳን መናፍስት ወይንም ሰይጣናት ተባሉ፤ ዋና አሳሳቻቸውም ዲያብሎስ ተባለ::

ምንም እንኳን በእምነታቸው የጸኑት ቁጥራቸው ብዙ እጅግ በጣም ብዙ ቢሆኑም እግዚአብሔር ግን ወደ ድቅድቅ ጨለማ ወደዚህች ምድር ውስጥ በተጣሉት ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) ምትክ እንደ ቅዱሳን መላእክት በአርያውና በአምሳያው ሌላ ሕያው ነፍስ ለመፍጠር በዚህች ዓለም ውስጥ ምሳሌያዊ ባህርይ የሆነችዉ ገነት የተባለች ቦታ ካለ መኖር ወደ መኖር አምጥቶ ሁለት ነፍሳትን እንደ ቅዱሳን መላእክት ከባህርይው በማስገኘት ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸው ምሳሌያዊ ባህርይ እንዲለብሱ ወይንም እንዲገለጹበት አድርጎ በገነት ውስጥ አኖራቸው::

በገነት ውስጥም በምሳሌያዊ ባህርይ ግንኙነት በሁለቱ ነፍሳት በኩል ብቻ ሌሎች ነፍሳት ቁጥራቸው ወደ ምድር ከተጣሉት ርኩሳን መናፍስት እኩል እስከሚሆን ድረስ ካለመኖር ወደ መኖር እንዲመጡ በማድረግ፤ በመጨረሻ ወደ ሰማያት ሊያስገባቸው ነበር የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ የነበረዉ :: በሌላ በኩል ደግሞ ርኩሳን መናፍስት፣ ከላይ የተገለጹት በሁለቱ ነፍሳት አማካይነት ሌሎች ነፍሳት ካላመኖር ወደ መኖር መጥተው ቁጥራቸው ከእነርሱ እኩል እስከሚሆን ድረስ በዚህች ምድር በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ በጭንቀትና በስቃይ ተፈርዶባቸው እንዲኖሩና በመጨረሻም በእነርሱ ምትክ የተፈጠሩት ነፍሳት ወደ ሰማያት ሲገቡ ይህች ዓለም ከመኖር ወደ አለመኖር አልፋ፤ እግዚአብሔር በአምላካዊ ስልጣኑና በቸርነት የርኩሳን መናፍስት ምሳሌያዊ ባህርይ ወደ አለመኖር አሳልፎ አማናዊ ባህርይቸውን በመመለስ አንጽቷቸው ወደ ራሱ ባህርይ በማስገባት ሕልውናቸውን ሊያጠፋ ነበር የእግዚአብሔር ፈቃድና ዕቅድ የነበረዉ::

እግዚአብሔር ሁሉቱን ነፍሳት (አዳምና ሔዋን) በመባል የሚታወቁትን በምሳሌያዊ ባህርይ እንዲገለጡ አድርጎ በዚህች ዓለም ውስጥ በፈጠራት በምሳሌያዊ ባህርይ በተዋቀረች ገነት ውስጥ ካስገባቸው በኃላ፤ በምሳሌያዊ ባህርይ ግንኙነት፣ ከእግዚአብሔር ባህርይ የሚገኙት ነፍሳት ካለመኖር ወደ መኖር እንደሚመጡና፣ስራቸውም እግዚአብሔርን ማመስገን ብቻ እንደሆነ ገልጾላቸዋል:: በመቀጠልም እንደ ቀደሙት መናፍስት በትዕቢትና በአመፃ ምክንያት በራሳቸው ምኞትና ሐሳብ እንደወደቁት እንዳይወድቁ፤ በግልፅ ተገዥነታቸውን የሚያረጋግጡበትን በገነት ውስጥ አንዲት ከምሳሌያዊ ባሕርይ ፍሬ በመፍጠር እንዳይበሏት አዘዘ:: ከበሏት ግን የሞት ሞትን እንደሚሞቱ ነግሯቸው ተሰወረባቸው::

ሁለቱ ነፍሳት በምሳሌያዊ ባህርይ የተገለጹት ለተወሰነ ጊዜ የታዘዙትን ትዕዛዝ በመጠበቅ አምላካቸውን በማመስገን በቅድስና ሕይወት ከኖሩ በኃላ፤ በእርሱ ምትክ ካለመኖር ወደ መኖር መተው በገነት የሚኖሩትን ሁሉቱን ነፍሳት ፣ የእምነት ፅናታቸው ይታይ ዘንድ የቀድሞው ሳጥናኤል የአሁኑ ዲያቢሎስ (እባብ) ተፈቅዶለት በዓለም ውስጥ ወዳለችው ገነት በመግባት የገነት ውስጥ አኗኗራቸዉን አንደኛዋን ነፍስ (ሔዋን) በመባል የምትታውቀውን ጠየቃት:: እሷም ፣እግዚአብሔር በዚህች ገነት ውስጥ እንዳኖራቸው፣ ስራቸዉም እሱም ማመስገን ብቻ እንደሆነ፣ ለመገዛታቸው ምልክት በገነት ውስጥ ያለችውን ፍሬ እንዳይበሉ እንደታዘዙና ከበሉ ግን የሞት ሞትን እንደሚሞቱ የተናገራቸው መሆኑን ገለጸችለት:: እሱም (ዲያቢሎስ) ክፋትና አመጻ የሞላበት ስለሆነ፤ አትብሉ የተባሉትን ፍሬ ከበሉ እንደ እግዚአብሔር እንደሚሆኑና ሁሉን ነገር እንደሚያውቁ የሐሰት ትምህርት ከሰጣት በኃላ ወደዚህች ድቅድቅ ጨለማ ወደ ሞላባት ምድር ተመለሰ::

ይህች ነፍስ (ሔዋን) በመባል የምትታወቀው በምኞት ተሸንፋ በራሷ ፍቃድ ያልተፈቀደላትን ፍሬ በመብላት፤ ለሌላኛው ነፍስ (አዳም) በመባል ለሚታወቀው የዲያብሎስን ሐሰት ትምህርት

በመግለጽ እሱንም አበላቸው:: በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ፀጋ ተለያቸው፣ ባዶነት ተሰማቸው፣ ቅድስናና ክብር አጡ ፣ላደፈና ለጎሰቆለ ባህርይ ተላልፈው ተሰጡ::

እግዚአብሔር አምላክም፤ትዕዛዝ መተላለፋቸውን፣ በአመጻ መውደቃቸውን ተመልክቶ፣ ከዚያ በፊት በተገለጸላቸው ብርሃናዊ ባህርይ ተገልጾ ያልተፈቀደላቸውን ፍሬ ለምን እንደበሉ ጠየቃቸው:: አንደኛው ነፍስ (አዳም) በሌላኛው ነፍስ (ሔዋን) በመባል በምትታወቀው አሳበበ:: ሌላኛዉ ነፍስ (ሔዋን) በዲያብሎስ (እባብ) አሳበበች:: ነገር ግን ሁሉትም ነፍሳት በነጻ ፈቃዳቸው በፈተና ወድቀው በክፉ ምኞት ተሸንፈው የፈጸሙት ስለሆነ፤ ምክንያታቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ የሞት ሞት ተፈረደባቸው::

እግዚአብሔር ይህች ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ ሞልቶት የርኩሳን መናፍስት መኖሪያና መቀጫ ቦታ የነበረችው ምድር፤ ከሰይጣናት ቀጥሎ ላመጹት ነፍሳት (ለአምዳና ሔዋን ከነዘሮቻቸው) መኖሪያና መቀጫ ቦታ ትሆን ዘንድ በውስጧ አስፈላጊ የሆኑ ምሳሌያዊ ፍጥረታት፤ በስጋዊ አይናችን የምናያቸውንና የማናያቸውን እንደ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ አዝዕርት፣ ዕፀዋት፣ እንስሳት፣ አዕዋፋት፣ መሬት፣ ውሃ፣ አየር፣ ንፋስ የመሳሰሉትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ::

እግዚአብሔር አንደኛውን ነፍስ (አዳም) ቀድሞ የለበሰውን ወይንም የተገለጸበትን ምሳሌያዊ ባህርይ ወደ አለመኖር አሳልፎ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ ያለውን ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆነውን ስጋ ከምድር(ከመሬት) አበጅቶ እንዲገለጽበት በማድረግ በወንድ ጾታ ሰው አደረገው:: ስሙንም አዳም አለው:: የሌላኛዋን ነፍስ (ሔዋን)፣ ቀድሞ የተገለጸችበትን ምሳሌያዊ ባህርይ ወደ አለመኖር አሳልፎ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ ካለው ምሳሌያዊ ፍጥረት ከሆነው ከአዳም ጎን አጥንት ወስዶ በሴት ፆታ ሰው አደረጋት:: ስሚም ሔዋን ተባለች::

እግዚአብሔር፣ «ብዙ፣ ተባዙ፣ ምድርንም ሙላት፣ በውስጣ ያሉት ግዙ፣ እዘዙ፣» ካላቸው በኋላ፤ ቀድሞ በገነት በምሳሌያዊ ባህርይ ግንኙነት ብቻ ነፍሳት (ልጆቻቸው) ከሁለቱ ነፍሳት ከአዳምና ሔዋን ካለመኖር ወደ መኖር እንዲመጡ የታዘዘውን ሽሮ፣ እነርሱና የልጅ ልጆቻቸው በምሳሌያዊ ፍጥረት ግንኙነት (በወንድ ጾታና በሴት ጾታ በለበሱት ስጋ ግንኙነት) እንዲዋለዱ፣ በኑሮዋቸውም ወጥተው፣ ወርደው፣ ሰርተው እንዲበሉ፣ በለበሱት ስጋ እንደሚሞቱ፣ ነፍሳቸው ከስጋቸው እንደምትለይ፣ ከስጋ ሞት በኋላ ከዓለምና ከሰማያት ውጭ ወደተዘጋጀው ሶስተኛዋ ምሳሌያዊ ባህርይ ቦታ ወደ ሆነችዉ ሲዖል እንደሚጋዙ፣ ሔዋንም በጭንቅ እንደምትወልድ፣ ከእነሱም የሚወለዱት ዘሮቻቸው (ልጅና የልጅ ልጆቻቸው) ሁሉ ባደፈና በጎሰቆለ ባህርይ እንደሚኖሩ ነገራቸው::

እግዚአብሔር፤ ምሳሌያዊ ባህርይ የሆነችዉን ሲዖል ከዓለምና ከሰማያት ውጭ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣት ሁለቱ ነፍሳት( አዳምና ሔዋን) በገነት የታዘዙትን ትዕዛዝ በተላለፉበትና ከገነት በተባረሩበት ወቅት ነው::

# ምዕራፍ ሁለት

ምሳሌያዊ ባህርይ የሚባሉት ሁሉ፤ ረቂቅ፣ በስጋዊ አይን የማይታዩ ሲሆን ለምሳሌ ቅዱሳን መላእክት የሚገለጹበት፣ ርኩሳን መናፍስት የሚገለጹበት፣ ሰማያት፣ ዓለም፣ ገነት፣ ምድር፣ ሲዖል የተሰሩበት፣ የእንሰሳት ደማዊ ነፍስ የተሰራችበት፣ በአጠቃላይ በሰማያት፣ በዓለም፣ በሲዖል ውስጥ በስጋዊ አይናችን የማይታዩ ረቂቃን ነገሮች ናቸው። እንዚህም ቀድሞ ያልነበሩ በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ሃይል የተዋቀሩ (የተፈጠሩ)፣ እግዚአብሔር በፈለገው ጊዜ ወደ አለመኖር ሊያስልፋቸው የሚችል አማናዊ ያልሆኑ ፍጥረቶች ናቸው።

ምሳሌያዊ ፍጥረት ደግሞ፤ በስጋዊ አይናችን የሚታዩ፣ የሚዳሰሱ፣ በዚህ አለም ውስጥ ያሉ ነገሮች ሲሆኑ ለምሳሌ የሰዎች ነፍስ የተገለጸችበት ስጋ፣ በአይናችን የምናያቸው ፍጥረቶች በሙሉ ናቸው። እንዚህም እንደ ምሳሌያዊ ባህርይ ቀድሞ ያልነበሩ፣ እግዚአብሔር በቅዱስ መንፈሱ ሃይል ያዋቀራቸው (የፈጠራቸው)፣ በፈለገ ጊዜ ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያሳልፋቸው የሚችል አማናዊ ያልሆኑ ፍጥረቶች ናቸው።

አማናዊ ፍጥረቶች ደግሞ፤ ከነበረ፣ ካለ፣ ሕያው ሆኖ ከሚኖር ከእግዚአብሔር ባህርይ የተገኙ ፣የማይሞቱ፣ እንደ ምሳሌያዊ ባህርይና ምሳሌያዊ ፍጥረት ከመኖር ወደ አለመኖር የማያልፉ ሕያው የሆኑ ፍጥረቶች ናቸው ። እነዚህ አማናዊ ፍጥረቶች ወደ አለመኖር ሊያልፉ የሚችሉት፣ እግዚአብሔር ወደ አማናዊ ባህርይው ሲመልሳቸው ብቻ ነው። እነዚህ ፍጥረቶች የቅዱሳን መናፍስት (መላእክት)ነፍስ፣ የርኩሳን መናፍስት ነፍስ፣ የሰዎች ነፍስ ብቻ ናቸው።

አማናዊ ህዋ የሚባለው፤ ምንም ዓይነት ፍጥረት ከመፈጠሩ በፊት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው እግዚአብሔር አምላክ በአማናዊ ባህርይው ብቻ የሚገለጽበት የነበረ፣ ያለ፣ ለወደፊትም የሚኖር ቦታ ነው። በአሁን ሰዓት አማናዊ ሕዋ የሚባለው ከሰማያት፣ ከዚህች ዓለም፣ ከሲዖል፣ ከማረፍያ ቦታ ውጭ ያለው ቦታ ነው። ይህ ቦታ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፣ እግዚአብሔር በአማናዊ ባህርይው የሚገለጽበት (የሚኖርበት) ስለሆነ፤ ማናም ፍጥረት የማያየውና ፍጡርም የማይገኝበት ቦታ ነው።

ምሳሌያዊ ሕዋ፤ ያለው በሰማያት፣ በዚህች ዓለም፣ በሲዖልና፣ በማረፍያ ቦታ ነው። ይህም በስጋዊ አይናችን ምን እንደሆነ የማናየውና የማንዳስሰው ቦታ ሁሉ ማለት ነው። ይህ ቦታ ምሳሌያዊ ባህርይ ስለሆነ፤ እግዚአብሔር በሚፈልግበት ጊዜ ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያሳልፈዉና በአማናዊ ሕዋ ሊተካው የሚችል ነው።

አማናዊ ባህርይ፤ ይህ የእግዚአብሔር ባህርይ ሲሆን ይህም በአማናዊ ሕዋ ውስጥ እግዚአብሔር የሚገኝበት ባህርይ ነው። በዚህ ባህርይው ማንም ፍጡር እግዚአብሔርን ሊያየው ሆነ ሊቀርበው አይችልም። ከሰማያት፣ ከዓለም፣ ከሲዖል፣ ከማረፍያ ቦታ ውጭ ባለው አማናዊ ሕዋ ውስጥ እግዚአብሔር በአማናዊ ባህርይው ይገኛል። በሰማያት ግን አማናዊ ባህርይውን ወስኖ በብርሃናዊ ባህርይው በመገለጽ ይመለካል።

ማናኛውም ፍጥረት ምሳሌያዊ ባህርይና ምሳሌያዊ ፍጥረት፤ በአማናዊ ባህርይው በቅዱስ መንፈስ ሃይል የተፈጠሩ ስለሆነ በዓይን የሚታየው፣ የማይታየው ረቂቅ ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ዕይታና ቁጥጥር ውስጥ በመሆናቸው እግዚአብሔር ሳያዉቀው ወይንም አቅቶት ሊከናወን የሚችል አንዳች ነገር የለም። ሁሉ ከእርሱ በወጣ ሃይል የተዋቀረ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ዕይታና ፍቃድ ውጭ ሊሆን የሚችል አንዳች ነገር የለም።

ቀድሞ ያልነበሩ ከመኖር ወደ አልመኖር ሊያልፉ የሚችሉ ፍጥረታት

1. ምሳሌያዊ ባህርይ
2. ምሳሌያዊ ፍጥረት
3. ምሳሌያዊ ሕዋ ናቸው::

እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩት (የተዋቀሩት) ከእግዚአብሄር አማናዊ ባህርይ በወጣው በቅዱስ መንፈስ ሃይል ስለሆነ፤ ይህ ሃይል በእግዚአብሔር ቁጥጥር ውስጥ ስለሚሆን እግዚአብሄር የፈለገውን ነገር በፈለገው ጊዜ ሊያደርግ የሚችል፤ከፈለገም ከአይን ቅጽበት ባነሰ ጊዜ (ከማይክሮ ሰከንድ ባነሰ ጊዜ) ውስጥ ወደ አለመኖር ሊያሳልፋቸዉ ይችላል::

አማናው ፍጥረት የሆኑት የቅዱሳን መናፍስት (መላእክት) ነፍስ፣ የርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) ነፍስ፣ የሰዎች (የአዳምና ሔዋን ዘሮች) ነፍስ፣ ከእግዚአብሔር ሕያው ባህርይ የተገኘ ከነበረ፣ ካለ፣ ከሚኖር፣ ያልኖረበት ጊዜ ከሌላ፣ የማይኖርበት ጊዜም ከማይኖር ከእግዚአብሔር አማናዊ ባህርይ የተገኙ ሲሆን፤ በምሳሌያዊ ባህርይና በምሳሌያዊ ፍጥረት የሚገለጹ ናቸው::

እነዚህ አማናዊ ፍጥረቶች ቅድስናን፣ ክብር፣ ጸጋ፣ እርካታ፣ እውነተኛ ደስታ፣ ሰላም፣ በተቃራኒ ደግሞ ርኩሰት፣ ጉስቁልና፣ጭንቀት፣ ስጋት፣ድንጋጤ፣ ፍርሐት፣ስቃይ፣የሚያገኙት በተገለጹበት ምሳሌያዊ ባህርይና በምሳሌያዊ ፍጥረት አማካይነት ነው::

ምሳሌያዊ ባህርይና ምሳሌያዊ ፍጥረት ቀድሞ ያልነበሩ፣ ነገር ግን ፍጥረታት መፈጠር (ካለመኖር ወደ መኖር በሚመጡበት ወቅት) የተፈጠሩ ሲሆን፤ ከዓለም ዕልፈት በኋላ የሚቀሩት አማናዊ ፍጥረትና ምሳሌያዊ ባህርይ ብቻ ይሆናል:: ምሳሌያዊ ፍጥረታት በሙሉ፤ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ:: በቦታውም አማናዊ ሕዋ ይተካል፤ እግዚአብሄር በአማናዊ ባህርይው ይኖርበታል::

ከዓለም ዕልፈት በኋላ ወደ አለመኖር የሚያልፉት ምሳሌያዊ ባህርይ በዝርዝር በስተመጨረሻ ላይ የሚገለጽ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ ከዓለም ዕልፈት በኋላ ከህያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ የሚኖረውን ህይወት በስተመጨረሻ ላይ ከጽሑፉ መረዳት ይቻላል::

## ምዕራፍ 3

አዳምና ሔዋን (ዘሮቻቸው ጭምር)ና ርኩሳን መናፍስት፤ በዚህች ዓለም ውስጥ ባለችሁ ምድር ውስጥ በተላላፉት የእግዚአብሄር ትዕዛዝ፣ በትዕቢትና አመጻ ምክንያት እየተቀጡ ይገኛሉ:: ሰዎች ባደፈና በጎሰቆለ ባህርይ፤ ይኸውም እግዚአብሄር በግልጽ «አታድርጉ» ብሎ ያዘዛቸውን በድፍረት በመተላለፋቸው ምክንያት እየተቀጡ ይኖራሉ::

ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) ደግሞ፤ በራሳቸው ሐሳብና ምኞት የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በመተላለፋቸው ምክንያት በጎሰቆለ ባህርይ ብቻ በዚህች ምድር እየተቀጡ ይኖራሉ:: በመሆኑም ይህች ምድር፤ ሁለቱም (የሰዎች ነፍስና የርኩሳን መናፍስት ነፍስ) ትዕዛዝ በመተላለፋቸውና በአመጻቸው ምክንያት በተገለጹበት ምሳሌያዊ ፍጥረትና ምሳሌያዊ ባህርይ ቅድስናቸው፣ ክብራቸውና ፀጋቸው ተገፎ ባደፈና በጎሰቆለ ባህርይ እየተቀጡ ይገኛል::

በሰው ዘሮች ላይ ያለው ጎሰቋላ ባህርይ የሚከተሉት ናቸው፤ ሞት ( ይኸውም ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆነው ስጋ ከአማናዊ ፍጥረት ከሆነችው ነፍስ) መለየት፣ ድካም ፣ጭንቀት፣ ፍርሃት፣ ስጋት፣ ሐዘን፣ ለቅሶ፣ የዓለም ውጣ ውረድ ማሰብ፣ ኑሮን ለማሸነፍ መስራት፣ ማንቀላፋት፣ መታመም፣ መራብ፣ መጠማት፣ መቸገር፣ ሰላምንና ደስታን ማጣት፣ ርካታን አለማግኘት ወዘተ.. ናቸው:: አጠቃላይ ጉስቁልና ህይወት ሁሉ፤ የእግዚአብሄር ጸጋ ከሰዎች በመገፈፉ ምክንያት የሰው ዘሮች የተላበሱት ጉስቁልና ባህርይ ነው::

በሰው ዘሮች ላይ ያለ ያደፈ ባህርይ የሚከተሉት ናቸው፤ በለበሱት ስጋ ምክንያት መሽተት፣ የበሉት መብል ወደ አይነምድር /ሰገራ/ መለወጥ፣ የጠጡት መጠጥ ወደ ሽንትና ላበት መለወጥ፣ ንፍጥ፣ አክታ ወዘተ ናቸው::የእግዚአብሔር ጸጋ ከሰዎች በመገፈፉ ምክንያት የሰው ዘሮች ላይ የሚታይ ያደፈ ህይወት ነዉ::

ሁለቱ ነፍሳት (አዳምና ሔዋን) ፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባይተላለፉ ኖሮ በገነት ኑሮዋቸው ከላይ የተገለጹት ጎስቋላና ያደፈ ባህርይ አያገኛቸውም ነበር:: ነፍሳቸው በምሳሌያዊ ባህርይ ሰለምትገለጽ መብላት፣ መጠጣት፣ አያስፈልጋቸውም ነበር:: ድካም፣ ሐሳብ፣ ጭንቀት፣ ስጋት፣ ፍርሀት፣ ሐዘን፣ ህመም፣ ችግር፣ መዉጣት፣ መውረድ አያገኛቸውም ነበር:: መለያየትና አድሉ፣ ራስ ወዳድነት፣ ንዴት፣ ብስጭት፣ ጥላቻ፣ ደስታንና እርካታን ማጣት፣ እንቅልፍ አይኖርባቸውም ነበር::በአጠቃላይ የነፍስ ተግባር እንደ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን ማመስገንና በደስታ መኖር ብቻ ነበር::

ከዚህ በተጨማሪ የመጀመሪያ ፍጥረት የሆኑት ሁለቱ ነፍሳት (አዳምና ሔዋን) ፤ በምሳሌያዊ ባህርይ ግንኙነት ብቻ የሰዎች ነፍስ ካለመኖር ወደ መኖር እየመጡ ቁጥራቸው ወደ ምድር ከተጣሉት ርኩሳን መናፍስት ቁጥር እኩል እስኪሚሆን ድረስ በገነት ኖረው፤ ከዚያ በኋላ ቅዱሳን መላእክት በሚኖሩበት ሰማያት ውስጥ በመግባት እንደ ሰማያዊ ስርዓት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ሕያው ሆነው ይኖሩ ነበር::

የሰይጣናት ጉስቁልና ባህርይ ደግሞ ጭንቀት፣ ስጋት፣ ፍርሃት፣ ሰላምንና ደስታን ማጣታ ፣ርካታን አለማግኘት፣ መቅበዝበዝ የመሰሳሉት ናቸው:: ዲያብሎስ፤ በገነት ውስጥ በመግባት ሁለቱን ነፍሳት (አዳምና ሔዋንን) ባያሳስት ኖሮ፤ አዳምና ሔዋን ከነዘሮቻቸው ወደ ሰማያት በሚገቡበት ወቅት የእግዚአብሄር ቸርነት በዝቶ እግዚአብሔር በአምላካዊ ስልጣኑ ርኩሳን መናፍስትን በማንጻትና ወደ ቀደመዉ ባህርያቸዉ በመመለስ ወደ አማናዊ ባህርይው አስገብቶ ህልውናቸውን ያሳጣቸው

ነበር፡፡ የቅጣት ዘመናቸውም ያጥርላቸው ነበር፡፡ ነገር ግን በትዕቢትና አመጻ ላይ ክፋትና ተንኮል ስለፈጸሙ በዚህ ምድርም፣ ከዓለም ዕልፈት በኋላም ለህያዉነት ዘመን በምሳሌያዊ ባህርያቸው በገሃነም እሳት ዉስጥ ሲቀጡ ይኖራል፡፡

ሰዎች ከደረሰባቸው ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ በተጨማሪ በዚህች ምድር ቆይታቸው በራሳቸው የፈጠሩት የሚከተሉት ባህርይና ጠባይ ናቸዉ፤ ቅናት፣ ምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ትዕቢት ፣ ጭከና፣ ግፍ፣ ስስት፣ ንቀት፣ መለያየት፣ አድሎ፣ ራስ ወዳድነት፣ ሐሰተኝነት፣ አመዝራነት፣ ገዳይነት፣ ስርቆት፣ ስድብ፣ አድመኝነት፣ አመጻ፣ ጠረኝነት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥንቆላ፣ መተተኝነት፣ አስማተኝነት ወዘተ.. ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ የርኩሳን መናፍስት ፍሬዎች የሆኑ፤ ሰዎች እግዚአብሄርን መፍራት ከሕሊናቸው በማራቅ የሰይጣናትን ክፉ መንፈስ በማቅረብ ለማይገባ ባህርይና ጠባይ ራሳቸውን አሳልፈው ሲሰጡ የሚፈጽሙት ተግባር ነው፡፡

በዚህ ምክንያት ሰዎች ህሊናቸውን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከማድረግ ይልቅ የርኩሳን መናፍስት ርኩስ መንፈስ ማደሪያ በማድረጋቸው በከፋ ጉስቁልና፣ መከራ፣ ስቃይ፣ ችግር ውስጥ ይመላለሳሉ ፡፡ በመልካም ህይወትና በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር ሊያገኙት የሚችሉትን መጠነኛ ደስታንና ርካታን ማግኘት ተስኗቸው በተቅበዘበዘና ተስፋ ቢስ በሆነ ህይወት ይኖራሉ፡፡

# ምዕራፍ 4

አዳምና ሔዋን ባደፈና በጎሰቆለ ባህርይ በመመሳለስ ምድራዊ ኑሮአቸውን ጀመሩ:: ይሁንና የእግዚአብሄር ትዕዛዝ በመተላለፋቸው ምክንያት በሐዘንና በለቅሶ፣ በንስሐ ህይወታቸውን ሲመሩ፤ እግዚአብሐር ርህሩህ አምላክ ነውና ንስሐቸውን (መጸጸታቸውን) ተቀበለ:: እግዚአብሔር፤ የአምላኩን ትዕዛዝ በመተላለፉ እጅግ ሲያዝን ለነበረው አዳም፤ ወደ ቀደመ ክብሩ እንደሚመልሰውና ለመጀመሪያ ዓላማ ወደ ተፈጠረበት እንደሚያስገባው ቃል ኪዳን ገባለት:: ይህም የሆነበት ሁለቱ ዋንኛ ምክንያቶች

1. አዳምና ሔዋን በእውነት በመጸጸታቸውና ይቅርታ በመጠየቃቸው::

2. በሁለት ነፍሳት መሳሳት (ትዕዛዝ መተላለፍ) ምክንያት፤ ዘሮቻቸው (የልጅ ልጆቻቸው ባለወቁትና ባልፈጸሙት በደል ምክንያት የሞት ሞት ስለተፈረደባቸው እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የድኅነትን መንገድ አዘጋጀ:: በዚህ ምክንያት ልክ የሩቁን ነገር በሩቅ መነጽር ተመልክቶ ማወቅ እንደሚቻል ሁሉ፤ እግዚአብሐርም በባህርይው፣ ከአዳምና ሔዋን የሚወለዱትን የሰዉ ዘሮች ቁጥራቸው ወደ ምድር ከተጣሉት ርኩሳን መናፍስት እኩል እስከሚሆኑ ድረስ ያሉትን ነፍሳትን ተመለከተ:: በነጻ ህሊናቸው የሚፈጽሙትን ህይወት አወቀ:: በዕይታው ውስጥም እጅግ የበቃች ነፍስ፣ የበቁ ነፍሳት፣ ምርጥ ነፍሳት፣ የቀለሉ ነፍሳት፣ እንደ ዲያብሎስና ተከታዮቹ የአመጻ ሐሳብና ምኞት ያለባቸውን ነፍሳት ተመለከተ::

እግዚአብሄርም ለአዳም፣ እጅግ የበቃች ነፍስ በምትወልድበት ዘመን፤ ያኔ ወደ ገነት እንደሚያስገባቸውና በምድራዊ ህይወታቸውም እሱን በመፍራትና በህገ ልቦና በመገዛት ምድራዊ ኑሮአቸውን እንዲኖሩ በማጽናናት ነገረው::

እነእርሱም በእግዚአብሄር ቃል ተጽናንተው፤በህገ ልቦና እግዚአብሄርን እያመለኩ፣ ነፍስ ከስጋቸው እስከምትለይ ድረስ ከዘጠኝ መቶ አመት በላይ በዚህች ምድር ኖሩ:: ተዋለዱ፣ በዙ:: ምንም እንኳን እግዚአብሄር በነጻነት የሚገዛ አምላክ ቢሆንም፤ የሰዎች አመጻና ግፍ፣ በዚህች የሰዎችና የሰይጣናት መቀጫ ምድር ውስጥ እየከፋ፣ ቅንነትና እግዚአብሄር መፍራት በልቦናቸው ውስጥ ያሉት ሰዎች ደግሞ መከራና ስቃይ፣ በደል ሲፈጽምባቸው፤ እግዚአብሄር በቁጣው አመጸኞችንና ግፈኞችን በዚህ ምድር ውስጥም በመቅሰፍት ይቀጣቸዋል:: እድሜያቸውንም ያሳጥራል::

በዚህም ምክንያት የሰው ዘሮች እየበዙ በሄዱበት ወቅት፤ በህገ ልቦና እግዚአብሄርን ባለመፍራት ከመመሳሳሳቸው በላይ በግፍ፣ በጭከና፣ በርኩሰት ህይወት እግዚአብሄርን እጅግ ስላስቆጡት፤ በህገ ልቦና ተመርቶ በቅንነትና በመልካም ህይወት የሚመላለሰዉን ኖህንና ቤተሰቡን እንዲሁም ለርሱ በቀጣዩ ህይወቱ የሚያስፈልገውን ፍጥረታት፣ ኖህ መርከብ እንዲያዘጅ አድርጎ በማትረፍ፤ ሌሎች በአመጻና በግፍ ያሉ ሰዎችን ሁሉ በጥፋት ውሃ ከምድር አጠፋቸው(ገደላቸው)::

አዳምና ሔዋን እንዲሁም ሌሎች የሰው ዘሮች ነፍስ፤ በሞት ጊዜ ነፍሳቸዉ ከስጋቸው ስትለይ የሚኖሩት ምሳሌያዊ ባህርይ ለብሰው ከዚህ ዓለም ውጭ በተዘጋጀው ሲኦል ውስጥ ነዉ:: በዚያ ያለው ቅጣታቸው ደግሞ በህገ ልቦና ተመርተው በሰሩት መልካም ስራና ቅንነት የተሞላ ህይወት እንዲሁም በሰሩት አመፃና ግፍ ይለያያል::

ከዓለምና ሰማያት ውጭ የሆነችሁ ሲዓል፤ በምሳሌያዊ ባህርይ የተዋቀረች፣ ውስጣም ድቅድቅ ጨለማ የሞላት፣ የሰዎች ነፍስ በምትገለጽበት ምሳሌያዊ ባህርይ የምትቀጣበት ቦታ ነው:: በምድራዊ ህይወታቸው ዘመን ሰዎች በህገ ልቦና በነጻ ህሊናቸው ተመርተው በሚሰሩት ተግባርና በሕሊናቸው ጸጸት፣ ባላቸው መልካምነት ደረጃ፣ ቅጣታቸው የሚለያይ ሲሆን፤ እጅግ አመፃንና ግፍ የፈጸሙ

ሰዎች በሲዖል እጅግ የከበደ ጭንቀትና መከራ ያገኛቸዋል:: በቅንነት ፣በመልካም ህይወት የተመላለሱና በበደላቸው የህሊና ጸጸት ያደረጉ ሰዎች፣ ምንም እንኳን ኑሮዋቸው በድቅድቅ ጭለማ ውስጥ ቢሆንም ስቃይና ጭንቀት አያገኛቸውም ነበር::

አካሄዳቸውን ፍጹም ከእግዚአብሄር ጋር ያደረጉ የበቁና ምርጥ ነፍሶች (ሰዎች) ደግሞ፤ በረድኤት እግዚአብሄር ተጠብቀው በተረጋጋና በደስታ መንፈስ ውስጥ ይኖሩ ነበር እንጂ የሲዖል ህይወት አያስጨንቃቸውም:: ይሁንና ሁሉም ነፍሳት ቀድም በገነት የነበራቸው ፍጹም የቅድስናና የደስታ ህይወት ማግኘት አይችሉም ነበር::

ከውሃ ጥፋት በኋላ እግዚአብሄር ኖህንና ቤተሰቡን ባርኮ፤ በምድር ላይ እንደገና መኖር ጀመሩ፣ ተዋለዱ፣ በዙ:: ይሁንና ከትንሽ ዘመን በኋላ እንደገና የሰው ዘሮች በህገ ልቦና እግዚአብሄርን ከመፍራት ይልቅ የሰይጣናትን ፈቃድ በመፈጸማቸው፣ በአመጻና በግፍ፣ በርኩሰት ህይወት መመላለስ ጀመሩ:: ከዚያም አልፎ እግዚአብሄርን እጅግ የሚያስቆጣ ተግባር በመፈጸማቸው ምክንያት ቋንቋቸውና ንግግራቸው አንድ የነበሩ ሰዎች፤ ቋንቋቸው እንዲለያይና በአራቱም ማዕዘን እንዲበተኑ አደረገ::

በዘመናት አኗኗራቸው ውስት በህገ ልቦና ተመርቶ እግዚአብሄርን በመፈለጉ፤ ቅንና መልካም ህይወቱን ተመልክቶ እግዚአብሄር አብርሃምን ከሚኖርበት ሀገር እንዲለይ አድርጎ ለራሱ ዓላማ አዘጋጀው:: ቃል ኪዳንም እዲጠብቅ ከእርሱ ጀምሮ ዘሮቹ እንዲሁም እርሱን የተጠጉ ሰዎች ጭምር ወንዶች ሁሉ እንዲገረዙ ነግሮት ዘሮቹን ባረከለት::

በዚያን ዘመን በሶዶምና ገሞራ እጅግ የከፋ ርኩሰት ይፈጸም ነበረና፤ እግዚአብሄር መላእክትን ልኮ ሎጥንና ቤተሰቡን ከከተማ እንዲወጡ ካደረገ በኋላ ከተማዋንና በውስጣ ያሉትን ሰዎች በእሳት ዲን አጠፋቸው ::

እግዚአብሄር ለአብርሃምና ለሳራ በእርጅና ዘመናቸው ይስሐቅ የተባለ ልጅ ሰጣቸው፤ ባረከላቸው:: ይስሐቅም ከርብቃ ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ከሊያና ከራሄል አስራ ሁለቱን የእስራኤል ነገድ ወለደ፤ ለአብረሃም ቃል በተገባለት ምድር በከነዓን ተቀመጠ::

የያዕቆብ ልጆች፤በወንድማቸው ዮሴፍ ቀንተው ለግብፅ ሰዎች ሸጡት፤ ዮሴፍም እግዚአብሄርን የሚፈራ ቅንነትና ጽናት ያለው ስለሆነ የተለያዩ ፈተናዎችን በፅናት አልፎ፤ ከእግዚአብሄር ግርማ ሞገስ አግኝቶ በግብፅ ከዋናው አገሪ መሪ ቀጥሎ አዛዥ ሆነ፤ ከፍ ከፍ አለ::

በከነዓን ምድር ረሀብ በሆነበት ዘመን ያዕቆብ በግብፅ እህል እንዳለ ሰምቶ ልጆቹን በዚያ ላከ፤ ዮሴፍንም በዚያ አገኙት፤ እርሱም ቸርነትን አደረገላቸው፤ አባቱንም ከነቤተሰቡ አስመጣቸው፤ ያዕቆብም ዮሴፍ በህይወት በመኖሩ ደስ ተሰኝቶ እግዚአብሄርን በመጠየቅ ከቤተሰቡ ጋር ከከነዓን ወደ ግብፅ ሄደ፤ በዚያም መኖር ጀመሩ::

ትውልዱ ከአራት መቶ ዓመት በላይ በግብፅ ከኖሩ በኋላ፤ ዮሴፍን ያላወቀ አዲስ ንጉሥ በግብፅ ተነስቶ የያዕቆብ ዘሮች እስራኤላዊያን ላይ መከራ፣ ስቃይ፣ እንግልት አደረሰባቸው:: የአብረሃም፣ የይሳሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ፤ የእስራኤላውያንን መከራና ችግር አይቶ ታላቁን ነብይ ሙሴን በማስነሳት ህዝቡን ከግብፅ ባርነት በታላላቅ መቅስፍትና ተአምር ነጻ አውጥቶ ወደ ከነዓን ምድር አስገባቸው::

በዚያን ጊዜ እግዚአብሄር፤ በህገ ልቦና ይመራ የነበረውን ህዝብ ህግና ስርዐት ሰራለት፤ በሙሴ አማካይነት ፍርድን አዘጋጀለት:: በህገ ኦሪት የተሰጡት አስርቱ ትዕዛዛት፣

«እግዚአብሄር ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ- ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁ እግዚአብሄር አምላክ እኔ ነኝ። ከኔ በቀር ሎሎች አማልክት አይሁኑልህ።

በላይ በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድርም ካለው፣ ከምድርም በታች፣ በውሃ ካለው ነገር፣ የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው አታምልካቸውምም፤ በሚጠሉኝ እስከ ሦስትና እስከ አራትኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፣ ለሚወዱኝ ትዕዛዜንም ለሚጠብቁኝ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምህረት የማደርግ እኔ እግዚአብሄር አምላክ ቀናተኛ አምላክ ነኝ።

የእግዚአብሄር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ እግዚአብሄር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።

የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፣ ስድሰት ቀን ስራ፣ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፣ ሰባተኛ ዉ ቀን ግን ለእግዚአብሄር ለአምላክህ ሰንበት ነው አንተ፣ ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረድህም፣ ከብትህም፣ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ስራ አትሥሩ፣ እግዚአብሄር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባህርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጠሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና፣ ስለዚህ እግዚአብሄር የሰንበት ቀን ባርኮታል፣ ቀድሶታልም።

አባትህንና እናትህን አክብር፣ እግዚአብሄር አምላክ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።

አትግደል።

አታመንዝር።

አትስረቅ።

በባልንጀራህ ላይ በሀሰት አትመስክር።

የባልነጀራህን ቤት አትመኝ፣ የባልንጀራህን ሚስት፣ ሎሌውንም፣ ገረዱንም፣ በሬውንም፣ አህያውንም፣ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማንኛውንም አትመኝ።» ኦሪት ዘፀአት 20:1-7

እግዚአብሄር እስራኤላውያንን በድንቅ ተአምራት ከግብፅ ባርነት ነጻ አውጥቷቸዉ በአስፈላጊው መግቦትና ጥበቃ ቢመራቸውም፤ እንደ ፈቃዱ ባለመመላለሳቸውና ተደጋጋሚ የድፍረት አመጻ በመፈጸማቸው ምክንያት ወደ ከነዓን በአርባ ቀን መግባት የሚችሉትን አርባ ዓመት ፈጀባቸው፤ ከዚህ በተጨማሪ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ከግብፅ ከወጡት ሰዎች መካከል እግዚአብሄርን እስከ መጨረሻው ደስ አሰኝተው እንደ ፈቃዱ በመመላለስ ከነዓን የገቡት ከታላላቅ ሰዎች መካከል ካሌብና ኢያሱ ብቻ ሲሆኑ፤ ሌሎቹ የተወለዱት ልጆቻቸው ናቸው ወደ ከነዓን ምድር የገቡት።

እግዚአብሄር በኃጢአት ከሚመላለሱ ሚሊዮን ሆነ ቢሊዮን ሰዎች ይልቅ፤ እርሱን በመፍራት እንደፈቃዱ ለሚመላለሱ እጅግ ጥቂቶች ሰዎች ወይንም አንድ ሰው ካገኝ ከዚያ ሰው ጋር ይቆማል፤ ይፈርዳል እንጂ፤ እንደ ሰው በቁጥር ብዛት የሚያምንና ጠማማን መንገድ ስለሰዎች ብዛት አያጸናም። ይልቁንም ሰለ አንድ የተመረጠ ሰው ሲል መአትንና ምህረትን ያደርጋል።

በከነዓን ምድር፤ በዘመነ መሳፍንት የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ላይ አመጹ፤ ከህግና ትዕዛዝ ውጭ በመሆን በጣዖትና ባዕድ አምልኮ ተመላለሱ፤ ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን የአባቶቻቸው አምላክ እግዚአብሔርን ረሱ፤ የአህዛብ አማልክትን ተከተሉ፤ አመለኩ፤ እግዚአብሔርን እጅግ አስቆጡ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርም በቁጣው ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጣቸው።

የእስራኤል ልጆች መከራ ሲበዛባቸው ወደ እግዚአብሄር ይጮኻሉ፤ እግዚአብሔርም ስለ አባቶቻቸው አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ሲል ከመካከላቸው ሰው እያስነሳ ነጻ ያወጣቸው ነበር፤

እንደገና ወደ አህዛብ አማልክት ልባቸው ሲመለስ የአህዛብ ነገስታት እየተነሱ መከራ ያደርሱባቸው ነበር።

በዚህ ህይወት የእስራኤል ልጆች ለብዙ ዓመታት (ዘመናት) ከኖሩ በኋላ፤እግዚአብሔር ዳዊትን መርጦ በነብዩ ሳሙኤል አማካይነት ቀብቶ የእስራኤል ንጉሥ አደረገው። ዳዊትም እንደ ቀደሙ አባቶቹ እንደ አብርሃም፣ ይስሐቅ ፣ያዕቆብ በቅን ህይወት የሚመላለስና እስከ ምድራዊ ህይወቱ ፍፃሜ ድረስ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ «እንደ ልቤ» የተባለ ታላቅ አባት ነው። በእስራኤልም 40 ዓመትነገሰ፤ እግዚአብሔርም በዳዊት ህይወት ስለተደሰተ« ልጆችህ መንገዳቸውን ቢጠብቁ፣ በፊቴም በፍፅም ልባቸውና በፍፅም ነፍሳቸው በእውነት ቢሄዱ፣ ከእስራኤል ዙፋን ሰው አይቆረጥብህም።» መ.ነ.ቀዳማዊ.2:4 ተብሎ ቃል የተገባለት ታላቅ ሰው ነው።

ዳዊት ከሞተ በኋላ፤ ሰለሞን በአባቱ በዳዊት ዙፋን ተቀመጠ፣ እግዚአብሔር ማስተዋልና ጥበብን፣ባለጠግነትንና ክብርን ሰጠው። የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ ከአራት መቶ ሰማንያ ዓመት በኋላ፤ንጉሥ ሰለሞን በእግዚአብሔር ተፈቅዶለት የእግዚአብሄርን ቤተመቅደስ ሰራ፤ የእግዚአብሔር ቃልኪዳን ታቦት ከነፅላቱ ካህናቱ ከዳዊት ከተማ ከጽዮን እንዲያመጡ አድርጎ በኢየሩሳሌም ባሰራው ቤተ መቅድስ በታላቅ ድምቀት ባለው ክብረ በዓል እንዲገባ አደረገ። በዚያን ጊዜም የእግዚአብሄር ክብር ቤተመቅደሱን ሞልቶ ነበር። ሰለሞንም በህዝቡ ፊት ቆሞ በመጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 8:22-68 እንደተፃፈው ለእግዚአብሄር ፀሎትና መስዋእት አደረገ። እግዚአብሄርም በመፀሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 9:1-9 እንደተጻፈው ለሰለሞን ቃል ገባለት።

እግዚአብሄርም፤ንጉሥ ሰለሞን በሰራው መልካም ስራ፣ ቅን ሐሳብ ግዛቱን አስፋለት፤በዓለምም አገነነው፤በመጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ 10፤23-29 እንደተፃፈው፤በባለጠግነትና በጥበብ ከምድር ነገስታት ሁሉ በልጦ ነበር። በዚያን ጊዜ ነው የሳባም ንግስት፤ በእግዚአብሄር ስም የወጣለትን የሰለሞንን ዝና በሰማች ጊዜ ወደ እርሱ የመጣችሁና «ንጉሡንም አለቻው -ስለ ነገርህና ስለ ጥበብህ በአገሬ ሳለሁ የሰማሁት ዝና እውነት ነው። እኔም መጥቼ በዓይኔ እስካይ ድረስ የነገሩኝም አላመንሁም ነበር፣ ጥበብህና ስራህ ከሰማሁት ዝናህ ይበልጣል።

በፊትህ ሁል ጊዜ የሚቆም፣ ጥበብህንም የሚሰሙ ሰዎችህና እነዚህ ባሪያዎችህ ምስጉኖች ናቸው። አንተን የወደደ፣ በእስራኤል ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሄር የተባረከ ይሁን፣ እግዚአብሄር እስራኤልን ለዘላለም ወድዶታልና ስለዚህ ፅድቅና ፍርድ ታደርግ ዘንድ ንጉሥ አድርጎ አስነሳህ» መ.ነገስት ቀዳማዊ 10፤1-9 በማለት ነበር በህገ ልቦና እግዚአብሄርን የምታመልክ ምስክርነትን የሰጠችሁ።

ጠቢቡ ንጉሥ ሰለሞን ለተወሰኑ ዓመታት አካሄዱን ከእግዚአብሄር ጋር ቢያደርግም፤የስጋ ፍላጎቱ አሸንፎት፣ ከፍ ከፍ ያደረገውን አምላክ ዘንግቶ በአህዛብ ሴቶች ፍቅር ተነደፈ ፣ ብዙ ሚስቶችና ቁባቶችን ለራሱ አደረገ፣ ሚስቶቹ ሌሎች አማልክት ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉት፣ በኢየሩሳሌምም አማልክት አቆመ። እንደ አባቱ ዳዊት አካሄዱን አላሳመረም።

በዚህም ምክንያት እግዚአብሄር ሰለሞንን ተቆጣ፤ ትዕዛዙንና ስርዕቱን ባለመጠበቁ ምክንያት መንግስቱን አካፍሎ ለባሪያው እንደሚሰጠው፤ ይህም ስለ አባቱ ዳዊት ሲል በእርሱ ዘመን እደማያደርገውና ነገር ግን በልጁ ዘመን እንደሚያደርገዉ ነገረው ። ንጉሥ ሰለሞንም አርባ ዘመን ከነገሰ በኋላ እንደ አባቱ ሞተ፣ ልጁም ሮብዓም በፋንታው ነገሰ።

ሮብዓም እንደ ዳዊት አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያለደረገ ሲሆን ፤እንደ እግዚአብሃሔር ቃልም እስራኤል ለሁለት ተከፈለች፤ሁሉት ነገድ ከተማቸውን በኢየሩሳሌም፤ ሌሎቹ አስር ነገድ

ከተማቸውን በሰማሪያ አድርገው እርስ በራሳቸው ይጣሉ ነበር። አመጻ፣ ርኩሳት፣ ግፍ ፣ጣዖትን ማምለክ ተስፋፋ፣ እንደ ንጉሥ ዳዊት በቅንነትና በእውነት በእግዚአብሔር ፊት የሚመላለስ አልነበረም።

የይሁዳ ንጉሥ በኢየሩሳሌም፣ የአስሩ ነገድ የእስራኤል ንጉሥ በሰማሪያ መቀመጫቸውን አድርገው ለዓመታት (ዘመናት) የተለያዩ ንጉሦች እየተፈራረቁ በገዙበት ዘመን ፤ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝና ህግ ቀናኢ የነበሩ የተለያዩ ነብያቶች እየተነሱ ስለ እዉነት ይመሰክሩ ነበር።

በእስራኤላዊያን በደልና ኃጢአት ምክንያት፤ በባቢሎን ንጉሥ በናቡኩደነጾር የኢየሩሳሌም ቅጥር ሁሉ ፈረሰ፤ የእግዚአብሃሔር ቤተመቅደስ ተቃጠለ፤ንዋየ ቅድሳት ወደ ባቢሎን ተወሰዱ፤ ህዝቡም በምርኮ ወደ ባቢሎን ፈለሱ፤ ነብዩ ኤርሚያስ እንደተናገረው ለ70 ዓመት በባርነት ቆዩ።

ነብዩ ዳንኤል፣ አናንያን ፣ሚሳኤል፣ አዛርያ፣ የመሳሰሉት ሰዎች፤ እምነታቸውን አጽንተው በባቢሎን ንጉሥ ፊት ግርማ ሞገስ አግኝተው በተቀደሰ ህይወት ይኖሩ ነበር።

የባርነት ዘመን 70 ዓመት ካለፈ በኋላ፤ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ ዘመን የባቢሎን ንጉስ ናቡከደነጾር የማረካቸው እስራኤላዊያን ልጆቻቸው ወደ ኢየሩሳሌም ይሁዳ ከተሞች ተመልሰው የፈረሰውን የእግዚአብሔር ቤተ መቅድስና ኢየሩሳሌምን መስራት ጀመሩ። ይሁንና በሰማርያና በዙሪያቸው የነበሩት አህዛብ፣ ለፋርስ ንጉሥ ለአርጤክስስ፣ በመጽሐፍ ዕዝራ 4፡ 11-16 እንደ ተፃፈው የክስ ደብዳቤ ጻፉ፤ ንጉሡም በኢየሩሳሌም ያለው የእግዚአብሔር ቤት ሥራ አስቆመ፤ ይሁንና ከሁለት ዓመት በኋላ፤ በእግዚአብሔር ሰዎች፣ ነብያት ትምህርትና ትንቢት ተመርተው የእግዚአብሔር ቤተ መስራት ጀመሩ፣ ምንም እንኳን በድጋሚ እንዳይሰሩ ተቋዋሚዎች ቢያጋጥማቸውም የፋርስ ንጉሥ ዳርዮስ ከዚህ በፊት በንጉሥ ቂሮስ እንዲሰሩ የተፈቀደላቸው መሆኑን፣ ከንጉሥ ቤተመዛግብት ውስጥ በመመርመርና በማረጋገጥ እንዲሰሩ ፈቀደላቸው።

የእስራኤል ልጆችም፣ ካህናት የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ አከበሩ፣ መምህራን ትዕዛዙን፣ ህጉን፣ ስርዕቱን፣ ፍርዱን ለህዝቡ አስተማሩ፣ ህዝቡም እግዚአብሔርን እያመሰገነ በትዕዛዙና በስርዕቱ መመላለስ ጀመረ። ይሁንና ከተወሰነ ዓመትና ዘመናት በኋላ እስራኤላውያን በኃጢአት እየወደቁ፣ እየተነሱ፣ ሕጉንና ትዕዛዙን እየጠበቁ፣ ሕጉንና ትዕዛዙን በመተላለፍ በዘልማድ እየኖሩ፣ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ፣እያስቆጡ በተደባላለቀ ህይወት በሚኖሩበት ዘመን፤ የሮም ግዛት በተስፋፋችበትና እስራኤልም በሮም ግዛት ውስት በነበረችበት ዘመን ፤ በነብያት አስቀድሞ ትንቢት የተነገረለት፣ ራሱ እግዚአብሔር በቃል ኪዳን የገለጸዉ፣ በዓለም ላይ ብዙዎች ሳያስቡትና ሳይጠብቁት አዲስ ክስተት መጣ። ይኸውም የክርስቶስ መወለድ ነው።

# ምዕራፍ 5

እግዚአብሄር በሰማያት ያመጹትን መናፍስትና ተባባሪዎቹን ሁሉ፤ ከሰማያት ወደዚህች ዓለም ውስጥ ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ ወደ ነበረችው ምድር እንደጣላቸውና ፀጋቸው ተገፎ በጉስቁልና ባህርይ እንዲኖሩ እንደፈረደባቸው ሁሉ፤ አዳምና ሄዋን የተባሉት ሁለቱ ነፍሳት በገነት ውስጥ አትብሉ የተባሉትን ፍሬ በመብላታቸው ምክንያት፤ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ በድፍረት ስላፈረሱ ከገነት ተባረው ይህች ምድር ለእነርሱ እንደሚያስፈልጋት ተደርጋ በመዘጋጀት (አስፈላጊ ፍጥረቶች) በውስጧ በመፍጠር ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆነውን ስጋ ለብሰው በዚህች ምድር እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል።

ይሁንና አዳምና ሔዋን የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው፤ በነጻ ሕሊናቸው ስለተጸጸቱና ይቅርታ ስለጠየቁ እንዲሁም በእነርሱ አመጽ ምክንያት ዘሮቻቸው ላይ ሁሉ የሞት ሞት ፍርድ በመፈረዱ ምክንያት፤ እግዚአብሄር በባህርይው የሰው ዘሮች ቁጥር ከርኩሳን መናፍስት ቁጥር እኩል እስከሚሆን ድረስ ያሉትን ነፍሳት ተመልክቶ እጅግ የበቃችው ነፍስ በምትወለድበት ዘመን ወደ ቀደመ ክብሩ እንደሚመልሰው ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን መሰረት፤ እስራኤላውያን በህገ ኦሪት በሚኖሩበት ዘመን፣ በእግዚአብሄር የሚያምኑ ሰዎች በእምነትና በዘልማድ በሚመላለሱበት ዘመን ፣ የእግዚአብሄር ትዕዛዝና ህግ እየተሻረ፣ የእግዚአብሄር አገልጋይ የተባሉ ሰዎች እንደ ስጋ ሐሳባቸውና ጥቅማቸው በእግዚአብሄር ቤት በሚመላለሱበት ዘመን፣ የእግዚአብሄርን ህዝብ በሚገባ የሚያስተምር ወደ ንስሐ የሚመልስ፣ ስለእውነት የሚመስክርና በእውነት የሚመላለስ ሰው በጠፋበት ዘመን፣ አመጻና ተንኮል፣ ርኩሰት፣ ግፍ፣ ትዕቢት፣ ጣኦት አምልኮት፣ ዝሙት በነገሰበት ዘመን፣ ሮም ግዛቷን አሳፋፍታ እስራኤልን በምትገዛበት ዘመን፣ በትንቢት የተነገረላት፤በተለያዩ ምሳሌ የተገለጸች፣ እጅግ የበቃችሁ ነፍስ፣ በእግዚአብሄር የተመረጠችው፣ በቅድስናና ንጽህና ህይወት በእውነት እግዚአብሄርን ከሚያመልኩ ቤተሰቦች ከኢያቄምና ከሀና ተወለደች። ስሟም ማርያም ተባለ።

ይህች የሰው ዘሮች ሁሉ፤ የመዳኛቸው ምክንያት የሆነች፣ በእግዚአብሄር የተመረጠችና እጅግ የበቃች ነፍስ፣በእናትና በአባቷ ቤት እንዲሁም በእግዚአብሄር ቤተመቅደስ ከኖረች በኋላ፤ ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ፤ ለአዳም ወደ ቀደመ ክብሩ እደሚመልሰው ቃል የገባለት አምላክ፣ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ ፍጥረታትን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፣ ከፈለገም በፈለገው ጊዜ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፣ ሁሉ በእርሱ ለእርሱ የሆነ፣ ካለ እርሱ ፈቃድና እዉቅና ውጭ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፣ ዘመን የማያቀጠርለት፣ ፊተኛውና ኋላኛ፣ መጀመሪያዉና መጨረሻው፣ አልፋና ያሜጋ የሆነ የጌቶች ጌታ፣ የአማልክት አምላክ ፣ የነገስታት ንጉሥ፣ የፍጥረታት ፈጣሪ እግዚአብሄር፤ በሉቃስ ወንጌል 1:26-56 እደተጻፈው አማናዊ ባህርይውን ወስኖ፣ ከሰማያት ሳይጎል፣ ከአማናዊ ሕዋ ውስጥ ሳይጎል፣ ከዓለም መግቦቱና ጥበቃው ሳይጎል፣ እንድ ነፍስና ስጋ ውህደት ከተወለደችው ሴት፤ ከድንግል ማርያም ከስጋዋ ስጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ በተዋህዶ ካለ አባት በመንፈስ ቅዱስ ግብር ተጸንሶ ሰው ሆኖ ተወለደ።

እንደማንኛውም ሰው በማህጸን ዘጠኝ ወር ቆይቶ፤ የሮማ ገዥ በነበረው በአውግስጦስ ቄሳር ትዕዛዝ፣ በእስራኤል ያሉ ሰዎች እያዳንዳቸው ይመዘገቡ ዘንድ በተላለፈው አዋጅ መሰረት ከዳዊት ወገን የሆኑት የድንግል ማርያም ጠባቂ ዮሴፍና ድንግል ማርያም ይመዘገቡ(ይጻፉ) ዘንድ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተንስተው ቤተልሄም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ይሁዳ በሄዱ ወቅት፤ በሰማያት ከቁጥር በላይ በሆኑ ቅዱሳን መላእክት የሚመሰገን፣ በባህርይው ምስጉን የሆነ፣ ሰዎችን ባላጠጋ የሚያደርግ፣ የሚያደኸይ፣ ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ የሚያዋርድ፣ ለፈለገው የፈለገውን ስጦታ

*የሚያደርግ፣ ምንም የሚሳነው ነገር የሌለ እግዚአብሄር፤ እንደ ተራ ሰው ዮሴፍና ማርያም ማደሪያ ቦታ አጥተው በከብቶች ማደሪያ በግርግም ውስጥ ድንግልናዋ እንዳለ ተወለደ:: ስሙም ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ ኢየሱስ፣ የአለም መድኃኒት፣ የሰዉ ልጅ፣ የእግዚአብሄር ልጅ ተባለ::*

*ከዚያም እንደማንኛው ሰው ለአሳዳጊው ዮሴፍና ለእናቱ ድንግል ማርያም እየታዘዘ አደገ፤ በዚህች ምድር ላይ ተመላለሰ :: ዓለም ግን ማን እንደሆነ አላወቀውም ነበር :: እንኳን እያንዳንዱ ሰው የሚሰራውን፣ የሚናገረውን ቀርቶ የሚያስበውን የሚያውቅ አምላክ ፤ ምንም እንደማያውቅ ሰው በሰዎች መካከል ተገኝቶ እንደሰው ይመላለስ፤ ይኖር ነበር::*

*በሉቃስ ወንጌል 3:1-22 ታላቁ ነብይና ሐዋርያ ዮሐንስ መጥምቅ፤« የጌታ መንገድ አዘጋጁ ፣ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ድምጽ፣ ዐዘቅቱ ሁሉ ይሙላ ተራራውና ኮርብታው ሁሉ ዝቅ ይበል፣ጠማማዉም የቀና መንገድ ይሁን፣ሸካራዉም መንገድ ትክክል ይሁን፣ ሥጋም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ይይ» ተብሎ እንደተፃፈ:*

*ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ፣ ከኃጢአት ወደ ጽድቅ፣ ከዘልማድ ህይወት ወደ እውነተኛ ህይወት እንዲለወጡ፤« አብርሃም አባት አለን ፣ እግዚአብሔርን እናመልካለን» እያሉ የሚመጻደቁትን ሰዎች እየገሰጸ፣ «መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፣ ወደ እሳትም ይጣላል» እያለ፣ እንደ አብርሃም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ህይወት ካልያዙ እግዚአብሔር ከአህዛብ መካከል ለአብርሃም ልጆች እንደሚያስነሳ ማንንም ሳያፍርና ሳይፈራ ያስተምር፤ ይገስጽ ነበር::*

*ሰዎች« ክርስቶስ ይሆን» እያሉ ሲያስቡ፤እውነተኛ የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነውና« እኔስ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፣ ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ፣ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፣ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፣ መንሹም በእጁ ነው፣ አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል፣ ስንዴውንም በጎተራ ይከታል፣ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል» በማለት የአምላኩን ክብርና ማንነት ስለሚያውቅ፣ እርሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ነገር ግን የክርስቶስን ክብርና ማንነት በሚገባ ገልጾላቸዋል::*

*ዮሐንስ ምስክርነቱን ከጨረሰና ወደ ውኒኒ ከገባ በኋላ፤ ክርስቶስ፣ አማኑኤል፣ ኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የሰው ልጅ በመባል የሚጠራው፤ ዘመን የማይቆጠርለት አምላክ ፤ በዚህ ምድራዊ ቆይታው ሠላሳ ዓመት ሲሞላው ለህዝቡ በግልፅ ተገልጾ ማስተማር ጀመረ:: ለሰው ዘሮች አርአያና ምሳሌ ሊሆን የመጣው አምላክ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ከተጠመቀ በኋላ እንደ ቀደሙት ነብያት አርባ ቀን ጾመ፤ ወንጌልን በተለያዩ ቦታ አስተማረ፤ የታመሙትን ፈወሰ፤ አጋንንትን አወጣ፤ ተአምራትን አደረገ፤ ለምጻሞችን አነፃ፤ ሙታንን አስነሳ፤ ድውያንን ሁሉ አዳነ ::*

*ይሁንና እርሱ በሚያደርገው ሁሉ፤ በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች አመለካከታቸው የተለያየ ነበር:: የመረጣቸው ሐዋርያት፣ ምንም እንኳን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም መሆኑን ቢያምኑም፤ በውስጣቸው ተስፋ የሚያደርጉት ምድራዊ ክብርን፣ ስልጣንን ነበር:: የተወሰኑ ሰዎች ድግሞ በትምህርቱ ተስበው የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ነበር:: የተወሰኑት ደግሞ ከህመማቸው ለመዳንና ለመፈወስ ነበር:: የተወሰኑት ደግሞ በተአምራቱ ለመጠቀም ነበር:: የተወሰኑት ደግሞ ውበቱን ፣ዝናውና ለማየት ነበር:: የተወሰኑት ቅናትና ምቀኝነት ያደረባቸው በነገር እርሱን ለማጥመድና በስጋዊ ወንበርና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ከተቀመጡ የስጋ መሪዎችና መንፈሳዊ መሪዎች ጋር ለማጣላት ነበር:: በአጠቃላይ ሲታይ እግዚአበሔር ሰው ከሆነበት ዓላማ ውጭ ነበር::የእግዚአብሔር ዓላማ ድኅነተ ስጋ ድኅነተ ነፍስ ለመስጠትና የሰው ዘሮች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድና እውነት አውቀው ወደ ህይወት እንዲመጡ፤ ወደ ትልቁ ተስፋቸው ገነትና መንግስት ሰማያት ለማስገባት ነበር::*

እርሱ ሰው የሆነ አምላክ፤በአራቱ ወንጌላት የተጻፉትንና ያልተጻፉትን በሚገባ ካስተማረና በኦሪት ያሉትን አስርቱ ትዕዛዛት ካጸና በኋላ፤የቀደመዉን ፍርድ በማሻሻል በሐዲስ ዘመን (በምህረት ዘመን) የጠበቀ ትዕዛዝ ሰቷቸዋል::

ይኸዉም በማቴዎስ ወንጌል 5:21-48 እንደተገለጸዉ «ለቀደሙት -አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፣ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል::እኔ ግን እላችዋለሁ፣ ወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፣ ወንድሙን ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፣ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል:: እንግዲህ መባህን በመሰዊያዉ ላይ ብታቀርብ፣ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፣ በዚያ በመሰዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፣ አስቀድመህም ከወንደምህ ጋር ታረቅ፣ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ:: አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፣ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ፣ ዳኛም ለሎሌው ወደ ወህኒው ትጣላለህ፣ እውነት እልሃለሁ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም::

አታመንዝር እንደተባለ ሰምታችኋል፣ እኔ ግን እላችዋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል:: ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፣ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና :: ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፣ ሙሉ ሰውነትህ ከገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካልህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና::

ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ፅህፈት ይስጣት ተባለ:: እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፣ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል::

ደግሞ ለቀደሙት -በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ ከቶ አትማሉ፣ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሄር ዙፋን ነውና፣ በምድርም አይሆንም የእግሩ መርገጫ ናትና፣ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉስ ከተማ ናትና፣ በራስህም አትማል አንዲቱን ጠጉር ነጭ፣ ወይ ጥቁር ልታደርግ አትችልምና:: ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፣ ከእነዚህ የወጣ ከክፉ ነውና::

ዓይን ስለ ዓይን ፣ጥርስም ስለ ጥርስ፣ እንደተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ክፉውን አትቃወሙ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፣ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ:: ለሚለምንህ ስጥ፣ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል::

ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላታችሁን ውደዱ፣ የሚረግሚችሁንም መርቁ፣ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፣ ስለሚያሳድድአችሁም ጸልዩ፣ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፣ በጻድቃንና በኃጢአታኞችም ላይ ዝናቡና ያዘንባልና:: የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ:: ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሱ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተ ፍፁማን ሁኑ ::ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸዉ:: » በማለት ነበር፤ የሐዲስ ዘመን ሰዎች አስርቱን ትዕዛዛት ብቻ መጠበቅ ሳይሆን የሚጠብቃቸው፣ ፍፁማን እንዲሆኑ ከላይ የተገለጹትን ሁሉ መፈጸም እንደሚጠበቅባቸዉ፤ እርሱ እግዚአብሄር ሰው ሆኖ በምድር ላይ በሚያስተምርበት ወቅት የገለጸው::

ከዚህ በተጨማሪ በዮሐንስ ወንጌል 3:1-15 ድረስ እንደተጻፈው፣ በእውነትና በቅንነት ይመላለስ ለነበረው ከፈርሳውያን ወገን ፣ የአይሁድ አለቃ ለሆነው ኒቆዲሞስ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ (በጥምቀት ከእግዚአብሔር ልጅነትን) ካላገኘ በስተቀር ወደ እግዚአብሄር መንግስት እንደማይገባ የገለጸ ሲሆን፤ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 6:53-59 ድረስ እንደተጻፈዉ «ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸዉ - እዉነት እዉነት እላችኋለሁ፣የሰዉን ልጅ ስጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ህይወት የላችሁም:: ስጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ህይወት አለዉ፤ እኔም በመጨረሻዉ ቀን አስነሳዋለሁ:: **ስጋዬ እዉነተኛ መብል ደሜም እዉነተኛ መጠጥ** ነዉና:: ስጋዬ የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ:: ህያዉ አብ እንደላከኝ እኔም ከአብ የተነሳ ህያዉ እንደምሆን፣ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሳ ህያዉ ይሆናል:: ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነዉ አባቶቻችሁ መና በልተዉ እንደ ሞቱ አይደለም ይህን የሚበላ ለዘላለም ይኖራል::» ተብሎ እንደተገለጸዉ የክርስቶስን ስጋ ያልበላ፣ ደሙንም ያልጠጣ የዘላለም ህይወት የለውም (ሕያው ሆኖ በእግዚአብሔር መንግስት አይኖርም::)

በመሆኑም ማንኛውም የአዳምና ሔዋን ዘር፤ ከእግዚአብሔር ልጅነት በጥምቀት ካላገኘና እውነተኛው መለኮት የተዋሀደውን የክርስቶስ ስጋ ካልበላ፣ ደሙንም ካልጠጣ ሕያው ሆኖ በእግዚአበሔር መንግስት መኖር አይችልም::

## *ምዕራፍ 6*

እግዚአብሔር ሰው ሆኖ በተመላለሰበት ዘመን፤ ለሐዋርያነት የመረጣቸው ሰዎች በተለያየ የስራ መስክ ተስማርተው የነበረና ስራቸውም ዝቅተኛ የተባለ፣ ያልተማሩ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ውሰጥ ያልተመላለሱ፣ ነገር ግን ከክፉ ትንቢት ፈጻሚዉ ከይሁዳ በስተቀር፤ ውስጣቸው ቅንነት፣ የዋህነትና መልካም ህይወት የተላበሱ ሰዎች ናቸው።

ክርስቶስ በሚያስተምርበት ወቅት የንሰሐ ልብ የነበራቸውና በእርሱ ያመኑት፤በኃጢአት ውስጥ የወደቁ ዘማውያን፣ በቅን ህይወት የሚመላለሱ ስጋውያን፣ በህመም ይሰቃዩ የነበሩ በሽተኞች፣ በአጠቃላይ የኦሪትን ትዕዛዝና ህግ በሚገባ የማያውቁ፣ በዘልማድ የሚመላለሱ፣ ውስጣቸው ቅንነትና መልካምነት ያላቸው ሰዎች ናቸው።

በተቃራኒ ደግሞ የንስሐ ልብ ያልነበራቸውና በእርሱ ያላመኑት፤ የኦሪቱን ህግና ትዕዛዝ ፣ስርዐቱንና ፍርዱን እናውቃለን የሚሉ ነገር ግን እንደ ቃሉ የማይኖሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን፣ የአይሁድ ካህናት፣ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ተቀምጠው በመንፈሳዊ እውቀት ብቻ የሚያገለግሉና ምዕመኑን የሚመሩ፣ ራሳቸውን ፍጹም አድርገው የሚቆጥሩ ከእግዚአብሔር ጋር ግን ግንኙነት የሌላቸው፣እንዲሁም በትንሳኤ ሙታን የማያምኑ ሰዱቃውያን፣ በስጋዊ ወንበር ላይ ተቀምጠው ለክብራቸውና ለዝናቸው ለጥቅማቸው የቆሙ ስጋዊ መሪዎች ከነሰራተኞቻቸው (አገልጋዮቻቸው) ጭምር ያሉ ሰዎች ናቸው።

በዚህም ምክንያት የአብርሃም ዘሮች ነን እያሉ የሚመጻደቁት አይሁድ፣ ጸሐፍት ፈሪሳዊያን እንዲሁም የአይሁድ ካህናት፣ በእውቀት ብቻ እንጂ በመንፈሳዊ ህይወት የማይመላለሱ፤ ትዕዛዙንና ሕጉን ስርዕቱን መግለጽ እንጂ እንደ ትዕዛዙና ስርዕቱ የማይኖሩ፤ እነርሱ የማይፈጽሙትን ስርዓት በምዕምኑ ላይ የሚጭኑ፤ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ያነቡታል እንጂ ያላስተዋሉት፤ ክርስቶስን ለስጋ ክብርና ስልጣን ያበቃናል ብለው ይጠብቁታል እንጂ ለታላቁ ሰማያዊ ክብርና ማዕረግ ያበቃናል ብለው የማይጠብቁ፤ እርሱ ክርስቶስ ከምስኪን ቤተሰብ ተወልዶ በመካከላቸው ሲመላለስ፣ ስለ እውነት ሲያስተምር በእውነት እየኖረ ለሌሎች አርአያ ሲሆን፤ በሰንበት መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ፣ ሲፈዉስ፣ ሲያድን፣ ሰዎች እንዳይሰናከሉበት ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደመጣና ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆኑ ሲገልጽ፤በቅናት ተነስተው ውስጣቸው ክፋትና ተንኮል፣ ትዕቢት የሞላባቸው ክብርና ዝናን የሚፈልጉ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ስጋዊነት ያደላባቸው በመሆኑ፤

እርሱን ንፁሃ ባህርይ የሆነ፤ ኃጢአት የማይሰማማው፤ የቅድስና ምንጭ፤እውነተኛ ፈራጅ ፤ ዳኛ፤ ሕሊናን የሚመረምር፤ እንኳን ያለፈውን፤ ያለውን ቀርቶ የወደፊቱን የሚያውቅ አምላክ ፤ማንም ሊያዘው ሆነ ሊያስገድደው የማይችል፤ፍጥረትን በሙሉ ከዓይን ቅጽበት ባነሰ ጊዜ (ከማይክሮ ሰክንድ ባነሰ ጊዜ) ውስጥ ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፤ከፈለገም በካትርሊዮን እጥፍ በላይ አዲስ ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር ሊያመጣ የሚችል፤ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ቅዱስ ስጋዉን ቆርሶ ክቡር ደሙን አፍሶ የሰው ዘሮችን <u>*ለማዳን ፈቃዱ ስለሆነ ብቻ*</u> ካለበደሉ እንደበደለኛ፣ ካለኃጢአቱ እንደ ኃጢአተኛ፣ ካለወንጀሉ እንደ ወንጀለኛ፣እንደአቅመ ቢስ በጲላጦስ አደባባይ ለፍርድ ቆመ፤ በሐሰት ተወነጀለ፤ ተሰደበ፤ በጥፊ ተመታ፤ ተገረፈ፤ ተጎተተ፤ ተተፋበት፤ ተሳለቁበት፤ እንደ ደካማ እየወደቀ እየተነሳ መስቀሉን ይዞ ወደ ቀራንዮ ሄደ፤ እንደ ዋና ወንጀለኛ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ተሰቀለ፤ሞተ፤በሶስተኛዉ ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ፤በአርባኛዉ ቀን አረገ፤ ወደ ቀደመ ክብሩ ተመለሰ ።

በምድር ላይ ከአንዲ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ ዓመት በፊት በቀራንዮ አደባባይ የተከሰተው ልዩ ክስተት ይህ ነበር። ዓመት ኩነኔና ዓመተ ምህረትን የለየ፤ ነገር ግን ዓለም ያላሰተዋለሁ፤ ያልተረዳው ታላቅ ምስጢር።

ክርስቶስ በምድር በተገለጸበት ወቅት ነው የእግዚአብሄር አንድነትና ሶስትነት የታወቀው ። በባህርይ፣ በስልጣን፣ በአገዛዝ፣ በመለኮት፣ በህልውና፣በመፍጠር አንድ የሆነ፣ በስም፣ በአካል፣ በግብር ሶስት የሆነ አምላክ ማንነቱ በግልጽ የታወቀዉ እግዚአብሄር ወልድ በተለየ አካሉ ባህርይውን ወስኖ ከእመቤታችን ከአደራ እናታችን ከቅድስተ ቅዱሳን ፣ ከንጽህት ድንግል ማርያም ከስጋዋ ስጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ፣ ከሁለት አካል አንድ አካል በመሆን ሰው በሆነበት ዘመን ነዉ። በሐዲስ ዘመን ነዉ የእግዚአብሄር አንድነትና ሶስትነት በግልጽ በዓለም የታወቀው ።

ለዚህም ነው በማቴዎስ ወንጌል 28:18 ላይ እንደተፃፈው፣ «ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ » ብሎ እርሱ አምላካችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ያዘዛቸው ።

አምላካችን ክርስቶስ በዕለት አርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነፍሱ ከስጋው በተለየች ጊዜ፤ በአካል ነፍስ በብርሃናዊ ባህርይው በመገለጽ፤ ከዚህች ምድር በስጋ ሞት ተለይተው ምሳሌያዊ ባህርይ በመልበስ በሲኦል የነበሩትን ነፍሳት በሙሉ ከሲኦል አውጥቶ በገነትና በማረፊያ ቦታ አስገብቷቸዋል።

ገነት በመጀመሪያ ሁለቱ ነፍሳት (አዳምና ሔዋን) ሲፈጠሩ የተዘጋጀላቸውና ለጥቂት ጊዜ የነበሩበት ሲሆን፣ ማረፊያ ቦታ ግን ከሰማያት፣ ከዓለም፣ ከሲያል፣ ቀጥሎ በምሳሌያዊ ባህርይ የተዋቀረች(ካለመኖር ወደ መኖር የመጣች) በአማናዊ ህዋ ውስጥ የተፈጠረች አራተኛ መኖሪያ ቦታ ናት ።

ከሲያል መጥተው ወደ ገነት የተመለሱ ሰዎች (ነፍሳት)፤ በምድራዊ ህይወት ዘመናቸው አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉ፤ በህገ ልቦና እየተመሩ መልካም የሰሩ፤ በኃጢአት ሲወድቁም በህሊናቸው የተጸጸቱ፤ እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ ድረስ በመልካም ህይወት የተመላለሱ ፤በሕገ ኦሪት ተመርተው የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ የጠበቁና በኃጢአት ሲወድቁም የኃጢአት ስርየት የተደረገላቸው ንስሐ የገቡ ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚህም ዓለም ስታልፍ ለፍርድ የማይቀርቡ አጠቃላይ የፍርድ ዉሳኔዉን ተመልክተዉ ከገነት ቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማያት የሚገቡ ናቸው።

ከሲያል ወጥተው ወደ ማረፊያ ቦታ የገቡት ደግሞ፤ በምድራዊ ሕይወታቸው ዘመን አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም ያላደረጉ፤ በህገ ልቦና ተመርተው መልካም ያላደረጉና ስለኃጢአታቸው በሕሊናቸው ያልተጸጸቱ፤ በርኩሰትና በአመጻ፣ በግፍ ህይወት የተመላለሱ ፤በምድራዊ ህይወታቸው እግዚአብሄርን ያላወቁ ነገር ግን በበደል ውስጥ ያልኖሩ፤ በህገ ኦሪት ጊዜ የእግዚአብሄርን ትዕዛዝ ያልጠበቁና ንስሐ ሳይገቡ ከነኃጢአታቸው የሞቱ፤ በአጠቃላይ እግዚአብሄርን ባለማወቅና ባለመፍራት የተመላለሱ ሲሆኑ፤ እንዚህ ሁሉ ዓለም በምታልፍበት ጊዜ ለመጨረሻ ፍርድ ይቀርባሉ። እግዚአብሄርን ያላወቁ ነገር ግን በበደል ሕይወት ያልተመላለሱ፣ በማረፍያ ቦታ ቆይታቸው በሚኖራቸው ውስጣዊ እምነትና ቅድስና በፍርድ ቀን ወደ መንግስተ ሰማያት ሊገቡ ይችላሉ።

በሲዖል ሆነ በማረፊያ ቦታ ያለው አኗኗር፤ ነፍሳት ሁሉ በምሳሌያዊ ባህርይ ስለሚገለጹ መብላት፣ መጠጣት አያስፈልጋቸውም፤ ማንቀላፋትና ድካም የለባቸውም፤ የፈለጉትን ለማድረግና ለመሆን ነፃነት የላቸውም::

እንደምድራዊ ህይወት በደላቸው፣ ኃጢአታቸው፣ አመጻቸው ደረጃ መጠን በምሳሌያዊ ባህርያቸው ይቀጣሉ፤ ይህም በጭንቀትና በስጋት፣በስቃይ ስሜት ነው:: በምድራዊ ህይወታቸዉ እግዚአብሄርን ያላወቁ ነገር ግን በበደል ያልተመላለሱ ሰዎች፤ በነጻ ሕሊናቸው እግዚአብሄርን ሊፈልጉና በእምነት ሊያመልኩት ይችላሉ:: በዚህ ውስጣዊ እምነታቸው ነው በፍርድ ቀን ሊፈረድላቸው ሆነ ሊፈረድባቸው የሚችለው::

ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ፣ በእርሱ በክርስቶስ አምነው ከእግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ (ከሥላሴ) ልጅነት ያገኙ፤ እንደ ትዕዛዙና ቃሉ በመኖር በስጋ ሲሞቱ (ነፍስ ከስጋ ስትለይ) በቀጥታ ምሳሌያዊ ባህርይ ተላብሰው ወደ ገነት ይገባሉ:: ከእግዚአብሔር ልጅነትን ያላገኙ፤ እንደ እግዚአብሔር ቃል ትዕዛዝ ያልተመላለሱ ሰዎች፤ ነፍሳቸው ምሳሌያዊ ባህርይ ተላብሳ እንደ ኃጢአታቸውና እንደ አመጻቸው ደረጃ ወደ ሲዖልና ማረፊያ ቦታ ነው የሚሄዱት:: ለበደላቸውና ለኃጢአታቸው ምንም ፍርድ የማያስፈልጋቸው ወደ ሲዖል ሲገቡ፤ እግዚአብሔርን ያላወቁ ነገር ግን በበደል ያልተመላለሱ እንዲሁም በመሰላቸው ህይወት በቅንነትና በመልካም ህይወት የኖሩ ሰዎች ደግሞ ወደ ማረፊያ ቦታ ነው የሚገቡት:: በማሪፊያ ቦታ በሚኖራቸው እግዚአብሔርን መፈለግና ውስጣዊ እምነት በፍርድ ቀን ሊፈረድላቸው ወይንም ሊፈረድባቸው ይችላል::

ከዚህ ዉጭ ደግሞ፤ እግዚአብሔር በአምላካዊ ስልጣኑ አካሄዳቸውን በፍጹም ከእርሱ ጋር ያደረጉትን፣ በምድራዊ ህይወት ዘመናቸው ነፍሳቸው እጅግ የብቃት ደረጃ ላይ የሚያደርሷት፣ በታላቅ ቅድስናና ሰማዕትንት እግዚአብሄርን የሚያከብሩትን ስጋዊ ሞትን ሳያዩ ሆነ በስጋ ሞተው ነፍሳቸው እንደ ቅዱሳን መላእክት ምሳሌያዊ ባህርይ ለብሳ የዓለም ዕልፈትንና የፍርድ ቀንን ሳይጠባበቁ በቀጥታ እርሱ በብርሃናዊ ባህርይው ተገልጾ በሚመለክበት ሰማያት ውስጥ የገቡና የሚገቡ አሉ::

የዓለም ዕልፈት የሚሆነው በነጻ ህሊናቸው ተመርተው በትዕቢታቸውና አመጻቸው ምክንያት ከሰማያት ወደዚህች ዓለም ምድር ውስጥ የተጣሉት ርኩሳን መናፍስት፤ ከአዳምና ሄዋን ዘሮች (የሰዎች ነፍስ) ቁጥር እኩል በሚሆንበት ወቅት ነው::

የሰዎች ነፍስ (በዚህች ምድር፣በሲዖል፣ በማረፊያ ቦታ፣ በገነት፣ በሰማያት ያሉት ሁሉ ተደምረዉ) ና የርኩሳን መናፍስት (የሰይጣናት) ቁጥር እኩል በሚሆንበት ጊዜ ይህች ምድር በውስጣ ካሏት ነገሮች ጋር ምሳሌያዊ ፍጥረት ናትና ከመኖር ወደ አለመኖር ታልፋለች፤ በዓለም ውስጥ ያለችው ገነት በውስጧ ያሉት ነፍሳት ወደ መንግስተ ሰማያት ሲገቡ ገነትም ሆነች ትልቋ ዓለም ምሳሌያዊ ባህርይ ናቸዉና ወደ አለመኖር ያልፋሉ::

በዓለም ዕልፈት ጊዜ አምስተኛው ምሳሌያዊ ባህርይ የሆነችው ገሃነመ እሳት ከሰማያት፣ ከዓለም፣ ከሲዖል፣ ከማረፍያ ቦታ ቀጥሎ በአማናዊ ህዋ ውስጥ ትፈጠራለች (ካለመኖር ወደ መኖር ትመጣለች):: ውስጧም የማይጠፋ ምሳሌያዊ ባህርይ የሆነ እሳት የሚሞላባትና የማይሞቱ ምሳሌያዊ ባህርይ የሆኑ ትሎች የሚሞሉባት ሆና ትዘጋጃለች::

በዓለም ዕልፈት ጊዜ በሲዖል ያሉት ነፍሳት በቀጥታ ወደ ገሃነም እሳት ሲገቡ፣ በዓለም ዕልፈት ጊዜ በዚህች ምድር ነፍሳቸው ከስጋቸው የሚለዩት ፍርድ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ወደ ማረፍያ ቦታ ገብተው ከእነርሱ ቀደም ብለው ከሚኖሩት ነፍሳት (ሰዎች) ጋር በመሆን የአምላካችን የእግዚአብሄር የኢየሱስ ክርስቶስ ፍርድ ያገኛሉ:: በምድራዊ ህይወት ዘመናቸው የሰሩት በደልና

ኃጢአት ሁሉ በሕሊናቸው እየታወሳቸው ፍርዳቸውን ይቀበላሉ:: ያን ጊዜ የሚኖር የህሊና ጸጸት ዋጋ የለውም፤ ያን ጊዜ የሚኖር ጩኸትና ሐዘን ዋጋ የለውም ፤ያን ጊዜ የሚኖር ልመና ዋጋ የለውም:: ሁሉም እንደ ሥራውና እምነቱ ተፈርዶለትና ተፈርዶበት ወደ መንግስተ ሰማያትና ወደ ገሃነም እሳት ይገባሉ::

ከዚህ በኋላ ዓለምም፣ሲዖልም፣ ማረፊያ ቦታ፤ ሶስቱም ቦታዎች ምሳሌያዊ ባህርይ ናቸውና ከመኖር ወደ አለመኖር አልፈው በአማናዊ ህዋ ይተካሉ:: በአማናዊ ህዋ ውስጥም፤ ሁለቱ ምሳሌያዊ ባህርይ የሆኑት ቦታዎች ሰማያትና ገሃነም እሳት ብቻ ይቀራሉ::

በነዚህም ሁለት መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩት ህያው የሆኑ ፍጥረቶች ሲሆኑ፤ በሰማያት ውስጥ ቅዱሳን መላእክት( ቅዱሳን መናፍስት) ፣ የጸደቁ ቅዱሳን ነፍሳት (ሰዎች) ናቸው:: በገሃነም እሳት ውስጥ የሚኖር ደግሞ ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት)ና ርኩሳን ነፍሳት (የተኮነኑ ሰዎች) ናቸው ::

በመጨረሻም ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት ለሕያዉነት ዓመታት( ዘመን) በሰው አእምሮ ሊቆጠርና ሊደረስበት የማይችል ዘመን ከካትሪሌየን አመታት እጅግ በጣም በላይ የሆነ ዘመን እግዚአብሔርን በብርሃናዊ ባህርይዉ እያመለኩትና እያመሰገኑት ይኖራሉ:: ከህያውነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ግን የእግዚአብሔር ቸርነቱ እጅግ ትበዛለች:: የእነዚህም ቅዱሳን ፀጋቸው እጅግ ይበዛል፤ በመሆኑም እነዚህ ሁለት ፍጥረታት (ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት) የተገለጹበት ምሳሌያዊ ባህርይ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋል ፣ ሁሉቱም አማናዊ ፍጥረቶች እንደ አማናዊ ባህርያቸው የመጨረሻውን ቅድስናና ደስታ ፣ እርካታ አግኝተው እግዚአብሔርን በአማናዊ ባህርይው በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ያመልኩታል፤ ሕያዉ ሆነዉ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ይኖራሉ:: ምሳሌያዊ ባህርይ የሆነችው ሰማያትም ከመኖር ወደ አለመኖር ታልፋለች::

በተቃራኒዉ ደግሞ ከህያወነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ በሰው አእምሮ ሊቆጠርና ሊደረስበት የማይችል ዘመን በኋላ የእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት ትበዛለች:: በገሃነመ እሳት ውስጥ እሳቱ በማይጠፋ ትሉ በማያንቀላፋ በምሳሌያዊ ባህርይ እንደ ኃጢአታቸው ደረጃ የሚቀጡትና የሚሰቃዩት ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት (ኃጢአተኛ ሰዎች)፣በሰው አእምሮ ሊቆጠርና ሊደረስበት የማይችል ዘመን ከካትሪሌየን አመታት እጅግ በጣም በላይ እስከሆነ ዘመን ድረስ ከተቀጡና ከተሰቃዩ በኋላ እግዚአብሄር ቸርነቱን በማብዛት ምሳሌያዊ ባህርያቸውን ከመኖር ወደ አለመኖር ያሳልፋል:: ነፍሳቸው በመጀመሪያ ስትፈጠር የነበራትን ፀጋና ቅድስና ይመልሳል::ካነጻቸውና ወደ መጀመሪያ ቅድስና ባህርያቸው ከመለሰ በኋላ ወደ አማናዊ ባህርይው እንዲመለሱ አድርጎ ህልውናቸውን ያጠፋል:: በዚህ መንገድ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ:: ገሃነም እሳትም ምሳሊያው ባህርይ ናትና ከመኖር ወደ አለመኖር ታልፋለች::

በስተመጨረሻ፤ መጀመሪያ መጨረሻ የሌለው አማናዊ ሕዋ ብቻ ይቀራል:: በውስጡም ያልነበረበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበትም ጊዜ የማይኖር፣ መጀመሪያውና መጨረሻው፣ አልፋና ዖሜጋ፣ በአንድነትና በሶስትነት የሚመለከው አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በመባል የሚታወቀው እግዚአብሔር አምላክ ፤ቀድሞ እንደነበረበት በአማናዊ ባህርይው ብቻ ይኖራል:: ከህያውነት ዘመን በኋላ የተፈጠሩ ሁለቱ አማናዊ ፍጥረታት፤ ቅዱሳን መናፍስት (ቅዱሳን መላእክት)ና ቅዱሳን ነፍሳት (የጸደቁ ሰዎች) በአማናዊ ባህርያቸው በአማናዊ ሕዋ ውስጥ ለሕያውነት ዘመን ሕያው ሆነው ይኖራሉ:: ቀድሞ ያልነበሩ፣ ነገር ግን የማይኖሩበት ጊዜ የማይኖር ይሆናል::

ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ማለት ኳትሪሊየን *ኳትሪሊየን*ኳትሪሊየን*ኳትሪሊየን* ኳትሪሊየን* ኳትሪሊየን* ኳትሪሊየን* ኳትሪሊየን* ኳትሪሊየን* ኳትሪሊየን ሲባዛ ከሚሰጠን ቁጥር

እጅግ ብዙ ብዙ የሆነ በፍጡር ሕሊና የማይደረስበት በእኛ ሕሊና ደረጃ ሕያዉ ዘመን ቢባል የሚቀል ሲሆን፤ ከዚህ ዘመን በኋላ ነዉ ሰማያት ሆነ ገሃነም እሳት ከመኖር ወደ አለመኖር የሚያልፉትና በሰማያት ዉስጥ የሚኖሩት ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ሰዎች ወደ መጀመሪያዉ(ጥንተ ተፈጥሯቸዉ) የመጨረሻዉን ደረጃ ቅድስና ይዘዉ የመጨረሻዉን ደስታና እርካታ አግኝተዉ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ በአማናዊ ባህርያቸዉ ሕያዉ ሆነዉ የሚኖሩት፡፡

በተቃራኒዉ ደግሞ ከህያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ በገሃነም እሳት ዉስጥ የሚኖሩት ርኩሳን መናፍስት( ሰይጣናት)ና ርኩሳን ነፍሳት( ኃጢአተኛ ሰዎች) ወደ መጀመሪያዉ(ጥንተ ተፈጥሯቸዉ) ባህርያቸዉ ተመልሰዉ ወደ እግዚአብሔር አማናዊ ባህርይ በመመለስ ህልዉናቸዉን በማጣት በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ በጥቁር ነጥብ መልክ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፤ ይኸዉም ልክ እኛ ሰዎች እንቅልፍ ስናቀላፋ ነፍሳችን ህያዉ ብትሆንም ምንም የምታስተዉለዉና የሚሰማት ነገር እንደሌለ ሁሉ፤ እነዚህ አመጸኛ ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳትም እንዲሁ በአማናዊ ህዋ ዉስጥ በጥቁር ነጥብ መልክ በአንድ ቦታ ላይ ህልዉናቸዉን አተዉ አንዳች ማስተዋል ሆነ የሚሰማቸዉ ስሜት ሳይኖር ይኖራሉ፡፡ ከህያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ የሚኖረዉ ቦታ የነበረዉ፣ ያለዉ፣ የሚኖረዉ አማናዊ ህዋና በስዕላዊ መግለጫ ዉስጥ የታየችዉ አራት ማዕዘን የምትመስል ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት ህልዉናቸዉን አተዉ የሚኖሩበት ነጥብ ቦታ ብቻ ነዉ፡፡ እንግዲህ ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ የሚፈረድለትንና የሚፈረድበትን እዉነተኛ የእግዚአብሔርን ፍርድ ብቻ ሳይሆን መመልከት ያለብን፤ ይህ እዉነተኛ ፈራጅ አምላክ ባህርይዉን ዝቅ አድርጎ ስጋችንን ተዋህዶ ሰዉ ሁኖ የተለያየ መከራዎችን ተቀብሎ ፍቅሩን በመስቀል ላይ ስጋዉን በመቁረስ ደሙን በማፍሰስ የገለጸልንን በሚገባ ማስተዋል ይጠበቅብናል፡፡ ተፈጸመ፡፡ ወስብሐት ለእግዚአብሄር፡፡

የእግዚአብሄር አብ ቸርነት፤ የእግዚአብሄር ወልድ ፍቅርና ምሕረት፤ የእግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ አንድነትና ጸጋ ፤የእመቤታችን፣ የአደራ እናታችን፣ የቅድስተ ቅዱሳን፣ የአዛኝቱ፣ የእመ አምላክ፣ የምስጋና ጸጋ የበዛላቸዉ የአባ ሕርያቆስ የአባ ኤፍሬም የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እመቤት፣ የነብያት ትንቢት፣ የሐዋርያት ስብከት፣ የሰማዕታት አክሊል፣ የጻድቃን እመቤት፣ የኃጢአን ተስፋ፣ ኢትዮጵያ አስራት ሀገሯ የሆች፣ ምሳሌ ተመስሎላት ተመስሎላት ተመስግና ተመስግና የማትጠገብ፣ የሰዉ ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነች፣ ለሰዉ ዘሮች መዳን በምልጃና በሐዘን በአምላክ ፊት የቆመች፣ ክብሯ እጅግ የበዛ፣ እኛ ሰዎች ሳይገባን እማማ እናታችን እንድንላት የተፈቀደልን፣ በሀዘናችን በችግራችን በመገፋታችን ቶሎ የምትደርስልንና የምታጽናናን፣ ብቻ ሁለመናችን የሆነች የህይወታችን ምስጢር ቁልፍ፣ እዉነተኛ ወዳጆቿን ለታላቅ ክብር ጸጋ የምታበቃ፣ እንኳን እርሷን የናቀና ያቃለለ ቀርቶ ያላፈቀራት ያልተማጸናት ያላመሰገናት የእግዚአብሔርን መንግስት የማያይ፣ በአምላኳና በልጇ በተሰጣት ስልጣን ሁሉን ማድረግ የምትችል፣ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ የሆነች፣ እኔን ዉዳቂዉን ኃጢአተኛ ሰዉ ለዚህ ያበቃችኝ የድንግል ማርያም ፍቅርና ምልጃ፤ የቅዱሳን መላእክት ጥበቃና ምልጃ፤ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የነብያት፣ የሐዋርያት በረከትና ምልጃ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ ይላል ሳይገባዉ ለዚህ መልዕክት አስተላላፊነት የተመረጠ ተራና ወራዳ ኃጢአተኛ ሰዉ፡፡

# ክፍል ሁለት

## ለዓለም ህዝብ የተላለፈ የእግዚአብሄር ግሳጼና ቃል

## ምዕራፍ አንድ

ክፍል አንድ በእግዚአብሄር ገላጭነትና አሳሳቢነት፣ ዓለም ሳይፈጠር በፊት የነበረውን፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያለውን፣ ከዓለም ዕልፈት በኋላ የሚኖረውን፣ እንዲሁም ከህያዉነት ዘመን በኋላ የሚሆነውን ጠቅለል ባለ መልክ የቀረበ ነዉ:: በዚህ ክፍል ደግሞ፣በዓለም ውስጥ ያለውን እውነታ እግዚአብሄር የሚናገረንን ነዉ:: የአንዳንድ ክፉ ትንቢት ፈጻሚዎችና የእግዚአብሄርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ሰዎች ስም በቀጥታ ስማቸው ያልተገለጸዉ ለምህረት የታሰቡ ሰዎች እንዳይሰናከሉበትና የተመረጡት ሰዎች ደግሞ ስራቸዉ ብርሃን ሆኖ ስለሚገልጻቸዉ ነው::

«እናንተ ሰዎች ክብራችሁን ያላወቃችሁ፣ አፈጣጠራችሁን ያልተረዳችሁ፣ ማንነታችሁን ያልተገነዘባችሁ፣ ታላቅ ተስፋችሁን የማትጠባበቁ፣ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርያችሁን በውል ያልተረዳችሁ፣ ራሳችሁን የተለየ አድርጋችሁ የቆጠራችሁ፣ አቅማችሁ እስከ ምን ያህል ድረስ መሆኑ ያልተገነዘባችሁ፣ በአጠቃላይ እንደ ስጋ ፈቃዳችሁ የምትመላለሱ ሁሉ፤

እኔ የፈጠርኳችሁ ለታላቅ ክብር ነበር፤ስራችሁም እኔን ብቻ ማመስገን፤መኖሪያችሁም በመንግስቴ ካለእኔ ፈቃድ አንዳች ሊኮን በማይቻልበት፤ መልካም የሆነ ፈቃዴ ብቻ በሚጸናበት ነበር:: አባታችሁና እናታችሁ (አዳምና ሔዋን) በመባል የሚታወቁት ሰዎች፤ሁለቱ ነፍሳት በምሳሌያዊ ባህርይ ተገልጸው በገነት ሲኖሩ ተገዥነታቸውን የሚገልጹበት እንዲት ቀላል ትዕዛዝ ብሰጣቸው፤ እንደ እኔ ለመሆን ፈለጉና በምኞት ተሸንፈው አትብሉ የተባሉትን ፍሬ በሉ:: በዚህም ምክንያት ፍርዴ እንደሰው ያልሆነ፣የባህርዬ የሆነ፣ዕቅዴ የማይለወጥ፣ውሳኔዬንም የማላስቀር እውነተኛ አምላክ ነኝ::

አዳምና ሔዋን ስፈጥራቸው፤ ከሰማያት በአመጻና በትዕቢታቸው ምክንያት ወደዚህች ምድር በመጀመሪያ ስትፈጠር ድቅድቅ ጨለማ ወደ ነበረችው ምድር በተጣሉት ርኩሳን መናፍሳት (ሰይጣናት) ምትክ ነበር:: ነገር ግን ተጨማሪ ነፍሳት (ልጆች) ገና ካለመኖር ወደ መኖር ሳይመጡ ትዕዛዜን ተላለፉ:: በዚህም ምክንያት የሞት ሞትን ፈረድኩባቸው ::

በመጀመሪያ ዕቅዴ መሰረት ቁጥራቸው ከርኩሳን መናፍስት እኩል እስከሚሆን ድረስ እነእርሱና የልጅ ልጆቻቸው በምሳሌያዊ ፍጥረት ግንኙነት አማካይነት እንዲወለዱ አደረኩ:: እንኳን አትብሉ ብዬ ያዘዝኩትን ትዕዛዝ በድፍረት ተላልፈው ቀርቶ፤ በብርሃናዊ ባህርዬ ተገልጬ በሰማያት መመለክ ሳልጀምር በፊት ከሰው አእምሮ ቁጥር እጅግ በጣም እጅግ የበዙ መናፍስትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቼ በመጀመሪያው ምሳሌያዊ ባህርይ ፍጥረት በሆነው ቦታ በሰማያት ውስጥ እንዲገለጹ ባደረኩበት ወቅት ለአለቅነት የመረጥኩት፣ በምሳሌያዊ ባህርይው ከሌሎች መናፍስት ለየት ያለው (የገዘፈው) የቀድመው ሳጥናኤል የአሁኑ ዲያብሎስ በራሱ ነጻ ህሊና ተመርቶ በፈጠረው ምኞትና ሐሳብ ተነሳስቶ - እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ እኔን አምልኩ በማለት የተወሰኑ መናፍስትን ያሳሳታቸው፤ እርሱንም በእርሱ ያመኑቱንና የተጠራጠሩትን ሳይቀር አማናዊ ባህርዬን በመወሰን በብርሃናዊ ባህርይ ተገልጬ የፈረድኩባቸውና ይህች ሁለተኛው ምሳሌያዊ ባህርይ ቦታ የሆነችዉን ዓለምን በመፍጠር ወደዚህች ምድር ውስጥ የጣልኳቸው:: ሁሉም አውቀው በነጻ ሕሊናቸው የካዱና ያመጹ፤ የተጠራጠሩ ስለሆነ የንስሐ ሕሊና አላገኙም:: አሁንም ወደፊትም የንስሐ ሕሊና አያገኙም:: እንደ አመጻቸው ደረጃ በዚህች ዓለምም፣ ከዚህች ዓለም ዕልፈት በኋላም ይቀጣሉ ፤ይሰቃያሉ::

እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ሰዎች ሁሉ፤ እናንተም እንደ ርኩሳን መናፍስ በአመጻችሁ ምክንያት በዚህች ዓለም ውስጥ ለስጋዊ ሕይወታችሁ የሚያስፈልጋችሁ ሁሉ በምድር ውስጥ ተፈጥሮላችሁ ነፍሳችሁ እየተቀጣች ቢሆንም፤ ከእነርሱ የምትለዩበት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. አዳምና ሔዋን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው ምክንያት ከገነት ተባረው ወደዚህች ምድር ገብተው መኖር በጀመሩበት ወቅት በኔ ላይ ማመጻቸውንና እኔንም ማስቆጣታቸዉን ተገንዝበዉ እጅግ አዝነዉ ይቅርታ በመጠየቃቸዉ

2. የእነርሱ ልጆች የሆናችሁ ሁሉ፤ ባላወቃችሁት ምክንያት በነእርሱ ላይ የተፈረደው የሞት ሞት ፍርድ በእናንተ ላይም ስለጸና፤ በነጻ ሕሊናችሁ ተመርታችሁ በምታደርጉት መልካም ነገርና እኔንም በእውነት በምታመልኩት ሕይወት ወደ ቀደመው ክብራችሁና መንግስቴ መመለስ እንድትችሉ በእነዚህ ሁለት ዋንኛ ምክንያቶች ነዉ  አዳም ከሐዘኑ እንዲጽናና ወደ ቀደመው ክብሩም እንደሚመለስ ቃል የገባሁለት::

እናንተ ሰዎች ግን ይህን እውነት አውቃችሁ አካሄዳችሁን ከኔ ጋር በማድረግ፣እንደፈቃዴ በመመላለስ፣ይህን ያደፈና የጎሰቆለ ባህርያችሁን ተገንዝባችሁ ምድራዊ ህይወታችሁን በመልካም መርታችሁ፣ወደ ቀደሞ ክብራችሁና ሰማያዊ መንግስት ውስጥ ለመኖር መናፈቅና በቅድስና ህይወት መትጋት ሲጋባችሁ፤ በብሉይ ዘመንም ሆነ አሁን ባላችሁበት ሐዲስ ዘመን እኔን የሚያስቆጣና የሚያሳዝን ተግባር ትሰራላችሁ::

አሁን ያላችሁ እናንተ ሰዎች፤ በብሉይ ዘመን እጅግ አስቆጥተውኝ ከምድር ገጽ ያጠፋዋቸውን ሰዎች ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ አላነበባችሁምን? መምህራን አላስተማሯችሁምን? ታዲያ ያኔ በሕገ ልቦና ተመርቶ በነጻ ሕሊናው እኔን ይፈራ የነበረ፤በቅንነትና በመልካም ህይወት ይኖር የነበረውን አባታችሁ ኖህ፤ ከነቤተሰቡ አድኘዋለሁ:: አሁኑም ታድያ እጅግ ያስቆጣችሁኝ ሰዎች፤ እንዲሁ አደርግባችኋለሁ:: ቅንነትና መልካምነት የሚገኝባችሁን ከጥፋት አድናችኋለሁ::

እናንተ አፈጣጠራችሁ ታላቅ የሆነ፣ነገር ግን ክብራችሁን ያዋረዳችሁ፣ ማንነታችሁን የዘነጋችሁ፣ ሕያው የሆነች ነፍስ፣ የማትሞት የማታልፍ ህይወት እያላችሁ የቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(ኢቮሊሽን)  አማካይነት ከጦጣ (ከዝንጅሮ) መሰል እንስሳ ወደ ሰው ተለወጥን እያላችሁ የምታምኑ፣  ሌላውንም የምታሳምኑ  የአመጻ ልጆች፤  ምን ዓይነት ሕሊና ነው ያላችሁ? አስራ ሺህ ዕድሜ እንኳን የሌላትን ዓለም፤ እናንተ ለሰው ዘሮች  በሚሊዮን የሚቆጠር ዕድሜ እየሰጣችሁ ለክህደታችሁ ማሳመኛ የምታቀርቡ፤ ለመሆኑ ሰዎች በሚሊዮን የሚቆጠር እድሜ ታሪክ ቢኖራቸው እንኳን ይህች መሬት አይደለም አስር እጥፍ ሌላ መሬት ቢኖር ለመኖሪያነት ይበቃችሁ ነበርን? እስቲ በእናንተ ዘመን እንኳን የሰው ልጆች ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ ምን ያህል እንደሆነ በዚህች በትንሿ ጠባብ አእምሯችሁ ገምቱ?

ታድያ የሚሊዮን ዓመት የሚቆጠር ከሆነ የሰው ዘሮች ታሪክ፤ አሁን ያለው የሰው ልጆች ቁጥር ብዛቱ በትርሊዮንና በካትርሊዮን አይደለም ከሰው አእምሮ በላይ የሆነ ቁጥር ሊኖራችሁ ይገባ ነበር:: እናንተም ስታችሁ ሌላውንም ታስታላችሁ፤ ይህ ሁሉ ጥረታችሁና ሐሳባችሁ እንደ መሪያችሁ ዲያብሎስ የኔን ሕልውና ለማጠራጠርና ተፈጥሮን ያስገኘውን ሃይል እኔን እግዚአብሄርን ለማስካድ ነው:: ግን ከዚህ ከአደፈና ከጎሰቆለ ቅርፊት ከሆነ ስጋችሁ ተለይታችሁ ስትመጡ ወዴት ይሆን መግቢያችሁ? እናንተ ይህ አክብዳችሁ ሞት የምትሉት ይህች እውነተኛ ባህርያችሁ የሆነች አማናዊ ፍጥረት ህያው ነፍሳችሁ ከዚህ ከምትቀጡበትና በዚህች ምድር ከተገለጻችሁበት ምሳሌያዊ ፍጥረት ከሆነው ስጋችሁ መለየት ነው:: አካሄዳቸውን ከእኔ ጋር ያደረጉ ሰዎች እኮ ይህን እናንተ

የምትፈሯትን ሞት የሞትሏትን እጅግ ይናፍቃሉ:: ምክንያቱ ከአደፈና ከጎሰቆለ ባህርይ እንዲሁም ከዓለም ዉጣ ዉረድ ውጭ ሌላ የሚቀርባቸው መልካም ነገር የለምና::

ለመሆኑ ይህን ያደፈ፣ የጎደፈና የጎሰቆለ ባህርያችሁን ተገንዝባችሁታልን? ኑሮአችሁ በገነት ቢሆን ኖሮ ነፍሳችሁ የምትገለጽበት በምሳሌያዊ ባህርይ ስለሆነ መብላት፣ መጠጣት አያስፈልጋችሁም፤ መራብና መጠማት አያገኛችሁም፤ ማሰብ፣ ማዘን፣መጨነቅ፣ መውጣትና መውረድ መከፋት የለባችሁም፤ ተንኮል፣ ትዕቢት፣ ክፋት፣ ቅናት፣ ርኩሰት አይኖርባችሁም ነበር:: መለያየት መከፋፈል፣ አድሎ፣ አድመኝነት፣ አመጻ በህይወታችሁ አይታይምነበር:: ማንቀላፋት፣ መድከም የሚባል ነገር አይከሰትባችሁም ነበር:: ሞት የሚባል አያገኛችሁም ነበር:: ይህን ስጋ በመልበሳችው ምክንያት የመጣባችሁ ያደፈ ባህርይ የሆነው አይነ ምድር( ሰገራ)፣ ሽንት፣ ላበት ና ንፍጥ፣ አክታ፣ መሽተት አያጋጥማችሁም ነበር:: ስራችሁ ሁሉ እኔን በእዉነት አምልካችሁ ማመስገን ብቻ፤ በዚህም ደስታና እርካታ ብቻ በሞላበት ህይወት ትኖሩ ነበር::

አሁን ግን ያደፈና የጎሰቆለ ባህርያችሁ አንሷችሁ፤ በዚህች ምድር እጅግ እጅግ አነስተኛ የሆነችውን ደስታና እርካታ፣ በመልካም ተግባርና በቅን ሐሳባችሁ ማግኘት ስትችሉ፤እናንተ ግን ገዥያችሁ ያደረጋችሁትን የዲያብሎስ መንፈስ በሕሊናችሁ አሳድራችሁ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በትዕቢት፣ በቂም በቀል፣ በጥላቻ፣ በርኩሰት፣ በአመጻ፣ በክህደት ህይወት ውስጥ በመመላለስ በበለጠ በከፋ ጉስቁልና ህይወት ውስጥ ትኖራላችሁ:: ፍዳችሁ በዚህች ምድር ብቻ ቢያበቃ ጥሩ ነበር፤ ምሳሌያዊ ባህርይ ለብሳችሁ እስከ ዓለም ፍጽሜ ድረስ ሶስተኛው ምሳሌያዊ ቦታ በሆነች በሲዖል፣ ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ደግሞ አምስተኛዉ ምሳሌያዊ ቦታ በምትሆነው ገሃነም እሳት የባሰ ስቃይና መከራ ይጠብቃችኋል::

ይህ ሁሉ ቃሌን አልሰማ በማለታችሁ፤ በንስሐ ወደ እኔ አልመለስ በማለታችሁ፤ በአመጻና በክህደታችሁ በመጽናታችሁ ምክንያት ነው:: እኔ ይቅርታና ምህረት ለሚጠይቁ፤ ስለ ኃጢአታቸው የሚጸጸቱትን የምምርና ለታላቅ ክብር የማበቃ፤ በኃጢአት ህይወትና በአመጻቸው፣ በክህደት የሚጸኑትን ደግም እንደ አመጻቸው ደረጃ በዚህች ምድር ላይም ሰላምና ደስታን፣ እርካታን እንዳያገኙ አድርጌ ፍዳቸውን የማሳይ፤ ይህች ቅርፊት ስጋቸው ከነፍሳቸው በምትለይበት ጊዜ ደግሞ የመንቀሳቀስ ነጻነታችሁን ገድቤ በአንድ ቦታ የምቀጣ ነኝ:: ምህረትም ፍርድም ከኔ ዘንድ ነው:: አንደ ሰው ተለዋዋጭ ሐሳብና ፍርድ ያለኝ አይምሰላችሁ :: » ይላል የሰራዊት ጌታ የአብርሃም የይሳሐቅ የያዕቆብ አምላክ::

## *ምዕራፍ ሁለት*

*« እናንተ የዓለም ጠበብት ነን፣ ምሁር ነን ፣ አዋቂዎች ነን የምታሉ ሁሉ፤ ለመሆኑ እውቀትንና ጥበብን የሚሰጥ ማነው? ነፍሳችሁ ሆነ የለበሳችሁት ስጋ እንደማንኘውም ሰው ነፍስና ስጋ ነው ። አእምሯችሁን የምከፍት፣ ማስተዋልና እውቀትን የምሰጥ እኔ ነኝ፤ እንግዲህ በተሰጣችሁ ጥበብና እውቀት መልካም የሆነውን ብቻ ስሩ። ከዚህ ጎስቋላ ከሆነ ህይወታችሁ የምትላቀቁበት፣የሰው ዘሮች የሚጠቀሙበት፣እኔ አምላካችሁ በምትሰሩት መልካም ነገር የምመሰገንበት ይሁን እንጂ፤ ለሰው ዘሮች መጥፊያ፣ ማጥፊያ የምትሰሩ ከሆነ በተሰጣችሁ እውቀትና ጥበብ በአግባቡ አልተጠቀማችሁበትምና የባሰ ፍርድ ታገኛላችሁ።*

*እናንተ በስጋዊ ወንበር የተቀመጣችሁ ከዋና መሪ እስከታች ድረስ ያላችሁ፤ ለመሆኑ በሃላፊነት የተሰጣችሁ የስራ ድርሻችሁ ምን እንደሆነ አውቃችኋልን? የማንን ፈቃድ ነው የምትፈጽሙት? መሪያችሁስ መንፈስ ቅዱስ ነው ወይስ የዲያቢሎስ መንፈስ ነው? ህዝቡ እኔን እንዲያውቅ፣ እኔን በፍፁም ህይወት እንዲያመልከኝ፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከትዕቢት፣ ከአመጻ፣ ከግፍ፣ ከጣዖትና ባዕድ አምልኮት፣ ከዝሙት፣ ከዘረኝነት፣ ከዘፋኝነት፣ ከዳንኪርተኛነት፣ ከግድያ፣ ከስርቆት፣ ከጥንቆላ፣ ከአስማት፣ ከመተት፣ ከሟርት፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት በአጠቃላይ የሰይጣናት ፍሬ ወደ ሞት ከሚወስዱትና እኔንም ከሚያስቆጣ ተግባራት እንዲለይ አድርጋችኋልን ?*

*እስቲ ራሳችሁን መርምሩ? እንኳን የምትመሯቸውን ሰዎች ከዚህ ከርኩስ መንፈስ ፍሬ ልትለዩ ቀርቶ እናንተ ራሳችሁ ከእነዚህ ተግባር ተለይታችኋልን ? እንግዲህ መሪያችሁ እኔ እንደሆንኩ ወይንም ዲያብሎስ አንደሆነ ራሳችሁ ፍረዱ! እኔና ዲያብሎስ አንድነት የሌለን፤ የኔ ፈቃድ የሆነው ከላይ ከተገለጸው የአመጻ ፍሬ ውጭ የሆነ፣ ሰዎች ሁሉ በቅንነት ፣ በመልካምነት፣ በትህትና፣ በትዕግስት፣ በፍቅር፣ በመረዳዳት፣ በመተሳሰብ፣ በቸርነት ፣ በእውነት ፣ በእምነት፣ በአጠቃላይ በቅድስና ህይወት በመመላለስ እንዲኖሩ ብቻ ነው።*

*እናንተ ግን መሪያችሁ ዲያብሎስን ስላደረጋችሁ፤ ከርኩሰት ፍሬ በተጨማሪ ሰዎችን በነገድ፣ በዘር፣ በቋንቋ እየለያያችሁ ጥላቻ የምትፈጥሩ፤ ሰዎች አንድ ሆነው በፍቅር እኔን እንዳያመልኩ የምታደርጉ፤ « ወገኔ፣ ዘመዴ፣ ዘሬ፣ ጎጤ ፣ ቤተሰቤ ነው» እያላችሁ አድሎ በማድረግ ራስ ወዳድነትን የምትፈጥሩ፤ ሰዎች በስግብግብነት ህይወት እንዲኖሩ አድርጋችሁ ህዝቡን በችግርና በረሀብ የምትቀጡ፤ የምታወሩት ሌላ የምትሰሩት ሌላ የሆነ፤ ንግግራችሁና ተግባራችሁ የማይገናኝ፤ አስመሳይ ሸንጋይ የሆናችሁ፤ እውነተኛውንና ሕሊናዬን አልሸጥም የሚለውን የምታሳድዱ፤ የምታስሩ፤ የምትገሉ፤ በሐሰት የምትወነጅሉ ናችሁ ። ታድያ ይህን ሁሉ ስታደርጉ ዝም ብዬ የማያችሁ አይመስላችሁ፤ እናንተ ለረጅም ጊዜ እንኖራለን፣ የራሳችንን ሐሳብ እናጸናለን፣ ለትውልዳችን እናስተላልፋለን ትላላችሁ። ነገር ግን ይህ ሐሳባችሁ ይሻራል፤ ይቆረጣል፤ ፍሬ ሊያፈራ ለሚችል ይሰጣል።*

*ለመሆኑ የምትሰሩትንና የምትናገሩትን ቀርቶ የምታስቡትን የማዉቅና ሁሉ ነገር በኔ ቁጥጥር ውስጥ የሆነ ፤ እንኳን አሁን ያላችሁበትን ቀርቶ አይደለም የወደፊቱን የማዉቅ አምላክ ነኝ ። በተቀመጣችሁበት ወንበር ላይ ሁላችሁም እንዳላችሁ አይናችሁ እያየ በትል ተበልታችሁ እንድትሞቱ ማድረግ የሚያቅተኝ ይመስላችኋልን? እንኳን እናንተ አመጸኞችን ቀርቶ በመጀመሪያ አካሄዳቸው ከኔ ጋር አድርገው በኋላ የረሱኝን እንኳን ቀጥቻቸዋለሁ፤ አዋርጃቸዋለሁ፤ ሐሳባቸውንና ምኞታቸውን ቆርጫለሁ።*

ስለዚህ ማንኛችሁም ብትሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ በስጋዊ ወንበር ላይ ስትቀመጡ የራሳችሁን ምኞትና ሐሳብ ለመፈጸም ሳይሆን የኔን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ብቻ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም የምትመሩትና የምታስተዳድሩት ህዝብ ዲያብሎስ የፈጠረውና የሚመግበው አይደለም፡፡ ፈጣሪዉም እኔ ፤ መጋቢውም እኔ ነኝ፡፡ መገዛትና ማምለክ ያለበት እኔ ነው እንጂ ዲያብሎስን አይደለም፡፡ እናንተ ግን እኔን አታወቁም፤ በበላይ ሆኖ የሚመራችሁንም ዲያብሎስን አታዉቁትም፤ አታስተውሉትም፤ ብቻ የሚያሳሰባችሁን ሐሳብ ወደ ተግባር ትለውጡለታላችሁ፤ ፈቃዱን ሁሉ እናንተም እየፈጸማችሁ ሌላውንም ታስፈጽማላችሁ፡፡ እውነትን በቅን ሐሳብና በመልካም ህይወት አልፈለጋችሁምና ሕሊናችሁ የኔን ፈቃድና ሐሳብ ሆነ፤ የመሪያችሁ ዲያብሎስ ፈቃድና ሐሳብ ሊያስተውልና ሊያውቅ አልቻለም፡፡እንደ ስጋ ሐሳባችሁና ምኞታችሁ ትፈጽማላችሁ፤ ታስፈጽማላችሁ፡፡

ለመሆኑ ስንት አምላክ አለ? ስንት ፈጣሪ አለ? ስንት የሁሉ አስገኝ አለ? አንድ እኔ ብቻ አይደለ ያለሁት!? ፍጥረታትን ሁሉ ካላመኖር ወደ መኖር ያመጣሁ፤ ከፈለኩም ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የምችል እኔ ብቻ አይደለሁምን !? እናንተ ግን ለራሳችሁ ብዙ አምላክ ፈጥራችሁ፤ ሰዎችም በብዙ አምላክ እንዲመሩ አደረጋችሁ፡፡ እውነትን አጥፍታችኋል፤ እኔ በእውነትና በእምነት እንዳልመለክ አድርጋችኋል፡፡ አንድ እግዚአብሄር እንደሆንኩ ሁሉ፤ «በፈጣሪ አምላክ አምናለሁ» የሚል ሰው ሁሉ በአንድ ሃይማኖት ሆኖ እኔን ማምለክ አልነበረበትምን !?

እናንተ ግን ተስፋችሁና ተግባራችሁ ምድራዊ፤ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚ ስለሆናችሁ፤ ለእናንተ ሁሉም ሃይማኖት ትክክል ነው፤ «ሁሉም በፈለገው መንገድ አምላክን ማምለክ ይችላል» እያላችሁ በሽንገላ ቋንቋ ዕድሜያችሁን የምታራዝሙ መስሏችኋል፡፡ እኔ እንደ ሰው አይደለሁም፤ አልቸኩልም፤ ግብታዊ ውሳኔም አልሰጥም፤ ሁሉን በጊዜው የማከናውንበት ወቅት ስላለኝ፤ ለዚህ ነው የአመጻ ተግባራችሁን እያየሁ ዝም የምለውና የአመጻዉ ፅዋ ሞልቶ ሲፈስ ርምጃ የምወስደው፡፡ አሁን ግን ይበቃችኋል፤ የምሰራበት ወቅት ደርሷልና ባለጊዜ አትሆኑም፤ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚነታችሁ ይሻራል፤ ቦታውን ፈቃዴን ለሚፈጽሙና ሊሚያስፈጽው ትለቃላችሁ፡፡

እናንተ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ፤ለመሆኑ በወንበሩ ላይ የተቀመጣችሁበትን ዓላማ አውቃችኋልን? በውኑ የምታመልኩትን አምላክ በእውነት ታመልኩታላችሁን? በእውነትስ ታገለግላላችሁን? ለመሆኑ እርሱ ማነው? እናንተስ ማናችሁ?

እስቲ ስለምትሰሩት ስራና ስለ መንፈሳዊ ህይወታችሁ ልትነግሩኝ ትችላላችሁን? የእናንተን በባዶ ህይወት የተሞላ ወሬ የሚሰማችሁ አምላክ ያለ ይመስላችኋልን ? ምን እየፈጸማችሁ ምን እያስፈጸማችሁ ነው ያላችሁት? ማንን ነው የምታታልሉት? በዚህች ዓለም፣ በሌላዉም ዓለም፣ አማናዊ ህዋ ውስጥም፤ ሁሉን በበላይ የምገዛ፣ የምቆጣጠር፣ የሁሉ አስገኝ፣ አልፋና ያሜጋ፣ መጀመሪያውና መጨረሻው፣ ፊተኛውና ኋላኛው እኔ ነኝ፡፡ ከኔ ውጭ ማን አለና ነው እናንተ በክህደት፣ በአመጻ፣ በውሸት፣ በማስመሰል የምታመልኩትና የምታሰመልኩት? እንኳን እኔን ቀርቶ፤ በዚህች ምድር እንደፈለገ የሚያሽከረክራችሁን፤ ሕሊናችሁን ለእርሱ ማደሪያ አድርጋችሁ እኔን የሚያስቆጣ ተግባር የምትፈጽሙለትን ዲያብሎስን ታውቁታላችሁን?

እንግዲህ በስጋዊ ወንበር ላይ ከተቀመጡት በላይ የባሰ ፍርድ እንደሚጠብቃችሁ እወቁ፡፡ ምክንያቱም በእኔ ስም ነውና የነገዳችሁት፡፡ እስቲ ፍሬ አፍርተናል የምትሉት አንዳች ነገር ካለ ንገሩኝ? ሰዎችን ከክፋት ወደ ደግነት፣ ከጠማማነት ወደ ቀናነት ፣ ከአመጻ ወደ ታዛዥነት ፣ ከክህደት ወደ ታማኝነት ፣ ከርኩሰት ወደ ቅድስና፣ ከራስ ወዳድነት ወደ ወገን(አዳምና ሔዋን ዘር) ወዳድነት፣ ከስስት ወደ ቸርነት ፣ከስግብግብነት ወደ መርካት፣ ከጠብ ወደ ዕርቅ፣ ከጥላቻ ወደ

ፍቅር፣ከጣዖትና ከባዕድ አምልኮ ወደ እውነኛ አምልኮ፣ ከሰይጣናዊ ሥራ (ጥንቆላ፣ አስማት፣ መተት ወዘተ..) ወደ መንፈሳዊ ሥራ፣ ከመለያየት ወደ አንድነት፣ ከመቅበዝበዝ ወደ መረጋጋት፣ ከልመና ወደ ሥራ፣ ከድንቁርና ወደ እውቀት፣ ከስንፍና ወደ ትጋት፣ ከሐዘን ወደ ደስታ፣ በአጠቃላይ ከዲያብሎስ ፍሬ ወደ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ ለውጣችኋልን ?

እሲቲ ራሳችሁ ፍረዱ! ወደ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ ለውጣችሁ ለንስሐ አብቅታችሁ ያከበራችሁት ሰው አለን ? እናንተ ግን እንደ ስጋውያን መሪዎችና ሠራተኞች ክብርና ዝናን፣ ጥቅምንና ድሎትን ፣ ውዳሴንና ሽልማትን ፈለጋችሁ:: እኔን ረስታችኋል፤ ህዝቡን ለነጣቂ ተኩላ ለዲያብሎስ አሳልፋችሁ ሰጥታችኋል፤ ከህይወት ይልቅ ወደሞት ወስዳችኋል፤ እውነት እንዳትታወቅ በዘልማድ እንዲመላለሱ አድርጋችኋል፤ በክህደትና በአመጻ ህይወት ኖራችኋል፤ አንድ እግዚአብሄር እኔ ብቻ እንደሆንኩ ብታውቁም ማስተዋልና እኔን መፍራት በውስጣችሁ የሌለ ስለሆነ ፤ «ሁሉም ሃይማኖት (እምነት) ወደ መንግስተ ሰማያት ያስገባል» ብላችሁ ስለምታስቡ ለእናንተ ሁሉም እምነት ትክክል ነው:: ሰዎች ወደ እውነተኛው ሃይማኖት እንዳይመለሱና ድኅነትን እንዳያገኙ ሆናችኋል:: በእውነተኛ ሃይማኖት ውስጥ ያሉትን፤ በቅድስና ህይወት እንዳይመላለሱ እንቅፋትና ማሰናከያ ሆናችኋል:: እውነተኞቹንና በሃይማኖት የጸኑትን ታሳድዳላችሁ፤ ታስገድላላችሁ፤ ታሳስራላችሁ፤ ትወነጅላላችሁ::ታድያ በስጋዊ ወንበር ላይ ያሉት ከፍርድ የማያመልጡ ከሆነ፤ እናንተ ከነእርሱ በባሰ ሁኔታ እንዴት አይፈረድባችሁም! እጅግ ይፈረድባችኋል:: ለእውነተኛ ለበጎች እረኛ ቦታውን ትለቃላችሁ::

እናንተ በተለያየ ኃጢአት የምትመላለሱ፤ ማመዛዘንና ማገናዘብ የሚችል ነጻ ሕሊና አልተሰጣችሁምን?በእረኞች ምክንያት እንዳታሳብቡ ክፉና ደጉን የምትለዩበት ነጻ ሕሊና ተሰቷችኋል:: በቅን ሐሳብና በመልካም ህይወት ውስጥ ልትመላለሱ ይገባ ነበር::

እናንተ ግን በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በትዕቢት፣ በአመጻ፣ በክህደት፣ በጥል፣ በጥላቻ፣ በዝሙት፣ በዘፈን፣ በዳንኪርተኛነት፣ በጣኦትና በባዕድ አምልኮ፣ በስካር፣ በጥንቆላ፣ በአስማት፣ በመተት፣በሟርት፣ በጠብና በክርክር ፣ በቂም በቀል፣ በመለያየትና በመከፋፈል፣ በራስ ወዳድነት፣ በስስት፣ በስግብግብነት ህይወት ትመላለሳላችሁ :: ይህ ሁሉ፤ እንኳን ከስጋ ሞት በኋላ ላለው ህይወት ቀርቶ ምድራዊ ህይወታችሁንም የሚያጎሳቁል፤ችግርና መከራ የሚያመጣባችሁ፤ከእኔ የሚለያችሁ፤ ሰላምን፣ደስታን፣ እርካታን፣ ቅድስናን የሚያርቅባችሁ ነው::

ስለዚህ ሁላችሁም ከዚህ የሞተ ህይወት ራሳችሁን ለይታችሁ በእኔ በአንዱ እግዚአብሄር ብቻ አምልኩ:: ሃይማኖታችሁም በነበረችው፣ አሁንም ባለችው፣ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በምትኖረው፣እኔ በደሜ በመሰረትኳት፣ ሐዋርያት ደቀመዛሙርቴ በሰበኳት፣ አበው ሐዋርያት ባስፋፏት፣ ሰማዕታት በተጋደሉላት፣ ጻድቃን ባጸኗት፣ ሊቃውንት መምህራን ባስተማሯት **ብቸኛዋ የህይወት መንገድ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት** ሥር ሆኖችሁ፤ እንደ እምነቱ ስርዓት በመመላለስ እንደ ቃሌ ኑሩ:: ያኔ በስጋችሁ በረከትን ፤ በነፍሳችሁ ድኅነትን ታገኛላችሁ:: ከዚያ ውጭ በስጋም በረከት፤በነፍስም ድኅነትን አታገኙም:: እውነተኛውን ሰላም፣ ፍቅር፣ ደስታና እርካታ የምታገኙት በዚህችው ቀጥተኛዋ ተዋህዶ ሃይማኖት ብቻ ነው ::

እናንተ በተለያየ የእምነት ድርጅት ውስጥ ያላችሁ፤ እንግዲህ ከእናንተ በላይ ሌላ ሐይል እንዳለ አምናችሁ ነው እምነት የሚባለውን ስያሜ ይዛችሁ በመመላለስ ያላችሁት:: ይሁንና ፈጣሪ እግዚአብሄር አንድ ሆኖ ሳለ በስጋዊ ምኞትና ሐሳብ በመመራት ሕሊናችሁን ለዲያብሎስ መንፈስ ማደሪያ በማድረጋችሁ ምክንያት እውነተኛውን እግዚአብሄር ለማወቅና ለማምለክ አልቻላችሁም::

አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ የነበረ እግዚአብሄር፤ አሁንም ያለው እግዚአብሄር፤ ለወደፊትም የሚኖረው አንድ ብቻ ነው:: በባህርይው ሰማያትና ዓለም ከመፈጠራቸው በፊት ብቻውን በአማናዊ ሕዋ ውስጥ በአማናዊ ባህርይው የነበረ፤ በኋላም በሰማያት መናፍስትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ ፤ ዓለምንና ሰዎችን በዓለም ውስጥ ያሉትን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፤ ዓለምንም አሳልፎ የሚኖር እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነዉ::

በመሆኑም እስካሁን ባለማወቅ የተመላለሳችሁበት ዘመን ይብቃ :: የኦሪት ሕግ እስክትመጣ ድረስ በህገ ልቦና ይመለክ የነበር፤ ከዚያም በሙሴ አማካይነት ህገ ኦሪትን የሰጠ፤ በኋላም ባህርይውን ዝቅ አድርጎ ካለበት ቦታ ሁሉ ሳይጎል፤ አዳምና ሔዋን ይቅርታ በጠየቁ ጊዜ «ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ» ባለው ቃል ኪዳን መሰረት፤ የሰው ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነችው፤ በእግዚአብሄር ባህርይ አስቀድማ ስትታይ በነጻ ሕሊናዋ እጅግ በቅድስናዋ በቅታ የተገኘች ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደችበት ዘመንና ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በድንግልና እንደምትጸንስ ተነግሯት ባመነች ጊዜ ስጋዋን ተዋህዶ በማህጸን እንደማንኛውም ሰው ዘጠኝ ወር ቆይቶ በድንግልና የተወለደው ያው የነበረው፣ ያለው፣ ሕያው ሆኖ የሚኖረው እግዚአብሔር፤ ሰው ሆኖ በምድር በተመላለሰበት ዘመን በሰራት ወንጌል አምናችሁና በእውነት አምልካችሁ ራሳችሁን ለማታልፈው ሰማያዊ መንግስት አዘጋጁ::

እናንተ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በክህደት እምነት ውስጥ ያላችሁ፤በቅንነትና በእውነተኛ ህይወት ውስጥ ሆናችሁ እውነተኛውን አምላክ እግዚአብሄርን ብትፈልጉ ኖሮ፤ በእውነት እሱ እውነተኛውን እግዚአብሄርን ታገኙት ነበር:: እውነተኛውንም ሃይማኖት ታውቁ ነበር:: ነገር ግን እንደ ራሳችሁ ፍልስፍናና አስተሳሰብ እንዲሁም ምኞትና ሐሳብ ስለምትመሩ፤ ውስጣችሁም አመጻና ትዕቢት ስለሞላ፤ እውነትን ማወቅ አልቻላችሁም ::በዚህ ምክንያት እግዚአብሄር ሊገለጽላችሁም ሆነ ወደ እውነተኛ ሃይማኖት ሊመራችሁ አልፈቀደም ::

እንኳን እናንተ በግፍና በአመጻ ውስጥ ያላችሁት ቀርቶ፤ በእውነተኛ ሃይማኖት ውስጥ ሆነው በቅንነት የማይመላለሱ፣ አመጽና ትዕቢት የሞላባቸው ሰዎች፣ እንዲሁ በዘልማድ የሚመላለሱ፣ መንፈሳዊ እውቀታቸውን እንደ ስራ መስክ ቆጥረው የሚያገለግሉ፣ እግዚአብሄርን ያገለገሉ እየመሰላቸው በክህደት ህይወት ውስጥ የሚመላለሱ፣ እግዚአብሄርን በግልጽ አያውቁትም፤ አያስተውሉትም፤ ቢያውቁትም በውስጣቸው እግዚአብሄር መፍራት የሌለባቸውና የድፍረትን በደልና ኃጢአት ስለሚሰሩ ለሰማያዊ መንግስትና ክብር አይበቁም::» ይላል እውነተኛውና ብቸኛ እግዚአብሄር አልፋና ያሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው የሆነዉ የአዳምና ሔዋን ፣ የሄኖክ፣ የኖህ፣ የሙሴ፣ የኢያሱ፣ የሳሙኤል፣ የዳዊት፣የኢሳኢስ፣የኤልያስ፣የኤልሳ፣የኤርምያስ፣ የዳንኤል፣የአናንያ፣ አዛርያ፣ሚሳኤል፣የዮናስ፣የዘካርያስ፣ የእዮብ፣ የአቤል፣ የኢትዮጵያዉያኑ አቤሜሌክ፣ ንግስት አዜብ፣ ካህኑ ዮቶር፣ መልከ ጼዴቅ አምላክ ::

## ምዕራፍ ሶስት

« እናንተ ማንነታችሁን ለማወቅ የምትፈልጉ ሰዎች፤ ይህ ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆነ ስጋ ለብሳችሁ በዚህች ምድር የተገለጻችሁት፣ የቀደሙት እናትና አባታችሁ አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ ልክ መናፍስት በሚገለጹበት ምስሌያዊ ባህርይ እነእርሱም በዚህ ምሳሌያዊ ባህርይ ተገልጸው ሲኖሩ፤ ለመገዛታቸው ምልክት የሆነችዉን ትዕዛዝ አትብሉ ያልኳቸውን ፍሬ በመብላታቸው ምክንያት ጸጋቸው ተገፎ ይህን ስጋ ከመሬት አዘጋጅቼው፤ በመጀመሪያ የተገለጹበትን ምሳሌያዊ ባህርይ ወደ አለመኖር በማሳለፍ፤ ነፍሳቸው ከተፈጠረው ስጋ ጋር እንዲዋሀድ በማድረግ ሲሆን ፤ ይህም ስጋ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ የተላበሰ ነው ። ነፍሳችሁ በዚህች ምድር የምትቀጣው በዚህ በለበሳችሁት ስጋ አማካይነት ሲሆን ፤ ጽድቅም ሰርታችሁ ለሰማይዊ መንግስት የምትበቁት በዚህ በለበሳችሁት ስጋ ተመርታችሁ በምትፈጽሙት መልካም ስራና እውነተኛ እምነታችሁ አማካይነት ነው።

ይህን ስጋችሁ በሳይንሱ አውቃችሁታል ፤ ያላወቃችሁት የነፍሳችሁንና የሰይጣናትን ሁኔታ ነው። ይህች ነፍሳችሁ ከኔ ከአምላካችሁ ባህርይ የተገኘች፤ ሕያዊት የማትሞት ስትሆን ፤ ለዚህ ስጋችሁ ሕይወትን የምትሰጥ፣ የምትቆጣጠር፣ የምትመራ እርሷ ናት። በአካል ደረጃ የምትገኘው በግንባራችሁ ፊት ለፊት አንጎላችሁ ዉስጥ ነዉ።እናንተ ሕሊና (አእምሮ) የምትሏት ናት ። የምታስበው፣ የምታወራው ፣ስራዎችን የምታከናዉነው እርሷ ናት። ከእርሷ በወጣ ሃይል ይህን ስጋ ተዋህዳ ስለምትገኝ፤ በስጋ ላይ የሚደርስ ማናኛውም ጉዳት ይሰማታል። ያልተዋሃዳችሁ ነገር ቢኖር ከሰውነታችሁ ጋር ከተያያዘው አካል ውጭ የሚበቅለው ጠጉር፣ ጥፍር፣ የቅንድብ ሽፋሽፍት፣ ጢም ነው። እነዚህ ከነፍስ የሚወጣው ሐይል ያልተዋሀዳቸው ስለሆነ በሚቆረጡበት ጊዜ የህመም ስሜት አይሰማትም ።

በዚህች ምድር ቆይታዋ እርሷ የማታየው ይኸውም በዚህ ስጋ ስለተገለጠች፤ እርሱ ግን የሚያያት ፈተኝ ያለባት ሲሆን፤ እነዚህ ፈታኞች በአመጻቸውና በትዕቢታቸው ምክንያት ከሰማያት ወደዚህች ምድር የተጣሉት ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) ናቸው።

እነዚህ መናፍስት፤ ይህ ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆነው ስጋችሁ የማያግዳቸው፣ እንኳን የምትሰሩትንና የምትናገሩትን ቀርቶ እያሰባችሁት ያለውን ሐሳብ እዛው ሕሊናችው (ነፍሳችሁ) ጋር ተቀምጠዉ የሚሰሟችሁ (የሚያውቁባችሁ ) ነው ። ለዚህም ነው ክፉ ሐሳብና ምኞት ሕሊናችሁ ሲያመነጭ፤ያሰባችሁትን ክፉ ሐሳብ ስለሚያዉቁ ወደ ተግባር እንድትለውጡት የሚገፏፏችሁና የሚፈታተኗችሁ ።

ታድያ ይህ ፍጡር፤ ርኩሳን መናፍስት በቅርበት ሆኖ የሚቆጣጠራችሁና የሚፈታተናችሁ ከሆነ ፤ እኔ የሁሉ አስገኝ ሁሉን ማድረግ የምችል አምላካችሁ እንዴት አብልጬ ሐሳብችሁንና ተግባራችሁን አላውቅ!? ለዚህም ነው እንኳን በተግባርና በንግግር ኃጢአት መፈጸም ቀርቶ በሐሳባችሁም ኃጢአት እንዳታስቡ « ወደ ሴት ያየ ሁሉ : የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝራል።» ብዬ በመዋዕለ ስጋዌ ዘመን ያስተማርኩት ። ስለዚህ እኔን መፍራት ያለባችሁ በምትሰሩት ስራና ንግግር ብቻ ሳይሆን በምታስቡት ሐሳብ ሁሉ ልትፈሩኝ እና በፍጹም ሐሳባችሁ፣ ንግግራችሁ፣ ተግባራችሁ ልታመልኩኝ ይገባል።

አሁን ምን ያህል በኔ ቁጥጥር ውስጥ እንዳላችሁና ሰይጣናትም በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚፈታተኗችሁ ተገነዘባችሁ? እንግዲህ በቅን ሐሳብ ብቻ ተመላለሱ፤ ሁል ጊዜ ለመልካም ነገር ትጉ፤ ያኔ የሚፈታተናችሁ ሰይጣን በሕሊናችሁ ማደሪያ ቦታ ስለማያገኝ እናንተን ምንም ሊያደርጋችሁ አይችለም። ልክ የሚነፍስ ንፋስ አትንፈስብኝ ማለት እንዳማትችሉ ሁሉ ሰይጣናትንም

« ወደ ሕሊናዬ (ወደ ነፍሴ) አትምጣ» ማለት አትችሉም::ምክንያቱም ይህች ምድር ሁለታችሁም የምትቀጡበት የጋራ መኖሪያችሁ ናትና፤ ይልቁንም የሰይጣናት የመጀመሪያ መኖሪያቸዉ የሆነ እናንተ በድፍረት አመጻችሁ ምክንያት በስደት የመጣችሁበት ሀገር ነዉ:: ነገር ግን በቤት ውስጥ ወይንም በሌላ መከለያ ውስጥ ሆናችሁ ንፋስን እንደምትከላከሉ ሁሉ፤ በቅን ሐሳብና በመልካም ተግባር፣ በፀሎት፣ በፆም፣ በስግደት ወደ ሕሊናችሁ የሚቀርበዉ ርኩስ መንፈስ፤ ሃይል እንዳይኖረዉና እንዳያሸንፋችሁ እንዲሁም እንዲቃጠል (እንዲቀጣ) ማድረግ ትችላላችሁ:: ከዚህ ውጭ ልታርቁት ሆነ ድል ልታደርጉት  አትችሉም:: በመሆኑም ቅን ለማሰብና መልካም ለመስራት ቃሌን በሚገባ ተምራችሁ ወደ ህይወታችሁ ለመለወጥ በተቀደሰ አኗኗር ተመላለሱ ::

ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) በዚህች ምድር ዉስጥ በሁሉም ቦታ የሚገኙና ማንኛዉንም ሰዉ ከህፃን እስከ አዋቂ ድረስ የሚፈታተኑ ናቸዉ:: ለዚህም ነዉ በተቀደሰዉ ቦታ ሳይቀር የማይገባ ተግባር የሚፈጸመዉ፤ የማይገባ ንግግር የሚነገረዉ፤ የማይገባ ሐሳብ የሚታሰበዉ:: ስለዚህ ሰዎች፤ መቼም ይሁን በየትኛዉም ስፍራ ሰይጣናት በተለያየ መልኩ ስለሚፈታተኗችሁ ሁል ጊዜ እኔን በመፍራትና በተቀደሰ ህይወት ተመላለሱ:: ያን ጊዜ ቦታ ስላማያገኝ እናንተን የማጥቃት ሆነ የመጉዳት ስልጣን አይኖረዉም::

የርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት)ጭከና በሚገባ አስተውሉ፤ እርሱ እናንተን መፈታተንና ማጎሳቆል የሚጀምረው ገና ከህፃንነታችሁ ከማህፀን ወጥታችሁ ወደዚህች ስደት ምድር ስትመጡ ነው አቀባበል የሚያደርግላችሁ፤ ገና ሕፃን ሆናችሁ እያለ ወደ ሕሊናቸው (በአካል ደረጃ ወደምትገኘው ረቂቅ ነፍሳችሁ ግንባራችሁ ፊት ለፊት አንጎላችሁ ውስጥ ወደምትገኘው) በመቅረብ የማታስተውለውን ደስታዋንና ሰላሟን ነስቶ ርካታ በማሳጣት ከመጀመሪያው ሐዘንን ያሳያታል፤ ያስለቅሳታል ::

ህጻናት እንደማንኛዉም አዋቂዎች በአዳምና ሔዋን አመጻ (ኃጢአት) ምክንያት በሰዉ ዘሮች የተከሰተባቸዉ ያደፈ ባህርይ የሆኑት አይነ ምድር(ሰገራ)፣ ሽንት፣ መጥፎ ሽታ፣ ንፍጥ የመሳሰሉት እንዲሁም የጎሰቆለ ባህርይ የሆኑት ድካም፣ እንቅልፍ፣ ህመም፣ መራብ፣ መጠማት፣ እዉነተኛ ደስታን ማጣት፣ ማልቀስ፣ መሞት የመሳሰሉት የሚታይባቸዉ ሲሆን፤ከዚህ በተጨማሪ ርኩሳን መናፍስት እንደማንኛዉም ሰዉ ወደ ሕሊናቸዉና አካላቸዉ ስለሚገቡና ስለሚወጡ ማፋሸክ፣ማዛጋት፣ ማስነጠስ፣ ማሳከክ ፣ ማንጠራራት፣ ፈስ፣ የተለያየ በሽታ የመሳሰሉት ይታይባቸዋል:: እናንተ አዋቂዎች ይህን ህይወት፤ ህይወት ነዉ ብላችሁ ተስፋችሁን ምድራዊ አድርጋችሁ በአመጻ ተግባር ትመላለሳላችሁ!

የሰዎች ነፍስ ሁሉ አፈጣጠር አንድ ዓይነት፤ በአካል፣ በቅርጽ፣ በመልክ አንድ ዓይነት የሆነች፤ በዚህ በምትገለጽበት ስጋ ብቻ የማወቅ የማስተዋል ደረጃዋ ብቻ የሚለያይ ይኸውም ከማህፀን ፅንስ ጀምሮ ሰው የምትባል፤የጾታ ልዩነት የሌላት ናት :: እኔ ፈጣሪዋ (አስገኝዋ ) በምሰጣት እውቀትና ማስተዋል ብቻ ነገሮችን እያወቀች፣ እየተረዳች፣ እያስተዋለች የምትኖር፤ ማደግ፣ መወፈር፣ መክሳት፣ ማርጀት፣ የሌለባት፤ ከለበሰችው ስጋ አንጻር ብቻ ድካም የሚሰማት፤ ምድራዊ ዘመኗን ስትጨርስ የተገለጸችበት ስጋ እያረጀ ስለሚሄድ እውቀቷና ማስተዋላ የሚቀንስ፤ ሕያው የሆነች ፍጥረት ናት::

እናንተ ግን ሕያዋን ሆናችሁ ሳላችሁ፤ ራሳችሁን ደማዊት ነፍስ እንዳላቸው እንደ እንስሳ ቆጠራችሁ:: ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣኋችሁን ረስታችሁ ማንነታችሁን ዘንግታችሁ ገና ከህፃንነታችሁ ጀምሮ በሐዘንና በለቅሶ አቀባበል የሚያደርግላችሁን ጨካኙን ሰይጣንን አመለካችሁ፤ የእርሱን ፈቃድ በመፈጸም አስቆጣችሁኝ፤ ራሳችሁን ከምድራዊ ህይወታችሁ ጉስቁልና በተጨማሪ ለመከራና ስቃይ ዳረጋችሁ፤ ምህረትና ይቅርታን እንዳታገኙ ደግሞ ሕሊናችሁን አደነደናችሁ::

ርኩሳን መናፍስት ከሕሊናችሁ (ከነፍሳችሁ) ሁል ጊዜ የማይለዩ መሆኑን የምታውቁት በሚያፋሽካችሁ፣ በሚያዛጋችሁ፣ በሚያስነጥሳችሁ፣ በሚያንጠራራችሁ ሁኔታ ነው። ይኸውም እነዚህ ርኩሳን መናፍስት ሁል ጊዜ እናንተን ለመፈታተን፤ ደስታንና እርካታን ለማሳጣት ለማድከም በሕሊናችሁ ውስጥ ይመላለሳሉ።በአካላችሁም ወስጥ ይገባሉ ፤ይወጣሉ፤ ይህ ስጋችሁ ለእነርሱ እንደ ወንፊት ክፍት ነዉ። በዚህም ምክንያት ከሕሊናችሁ ሲወጡ በአፋችሁ በኩል በማፋሽክ ፤ ከሆዳችሁ ሲወጡ በግሳት፤ከመተንፈሻችሁ ሲወጡ በሳልና በአክታ፤ ከሕሊናችሁ ሲወጡ በአፍንጫችሁ በኩል በማስነጠስና በንፍጥ፤ በአካላችሁ መገጣጠምያ በኩል ሲወጡ በማንጠራራት፤ በቆዳችሁ በኩል ሲወጡ በማሳከክና በመጥፎ ጠረን፤ከሆዳችሁ እዳሪ ውስጥ የሚገቡት ደግሞ የሚወጡት በፈስ መልክ በፊንጥጣቸው በኩል ፤ለሎች ደግሞ ከአይነ ምድራችሁና ከሽንታችሁ ጋር ይወጣሉ። የኔ፤ቅዱስ መንፈስ በሚመጣባቸው ጊዜ ደግሞ ተቃጥለው ከሕሊናችሁ ብን ብለው ይወጣሉ ። ተቃጥለው በእንባ መልክ በዓይናችሁ በኩል ይወጣሉ።

«ተጫጫነኝ፤ደበተኝ፣ ድብርት ያዘኝ፣ሕሊናዬ ሰላም አጣ፣ ተጨነቅኩ፣ እርካታን አጣሁ » እያላችሁ የምትናገሩት፤ እነዚህ ክፉ መናፍስት ሕሊናችሁ ውስጥ በመመላለስ ነፍሳችሁን ሲያስጨንቁና ሲፈታተኑ ነው። የእነርሱ ዕረፍትና የእናንተ ነፍስ ዕረፍት ያላት፤ የርኩሳን መናፍስት ርኩስ መንፈስ ሃይላቸው አሽንፏችሁ በምታንቀላፉበት ጊዜ ብቻ ነው። በእንቅልፋችሁም ጊዜ በተለያየ ሁኔታ እየተገለጹ ነፍሳችሁን ያስጨንቋታል ።

ታድያ የዚህች ምድራዊ ህይወታችሁ ህይወት ሆነና ነዉ በዚህች ምድር መቆየት የምትፈልጉት!? ካደፈና ከጎሰቆለ ባህርይችው በተጨማሪ፤ በሰይጣናት ቀን ከሌሊት እየተፈተናችሁ፤ እየተሰቃያችሁ፤ ስለምን ከሞት ይልቅ የህይወትን መንገድ ይዛችሁ እንደቃሌ በመሆን ፈተናና መከራ የሌለበትን ፤ሁል ጊዜ ደስታና እርካታ ብቻ የሚገኝባትን ፤ ሕያው ሆናችሁ እንደ ቅዱሳን መላእክት (ቅዱሳን መናፍስት) የምታመሰግኑበትን ሰማያዊ መንግስቴን አትፈልጉም!? ይህ ምድራዊ ህይወት ሆነና ነው እርስ በርስ የምትጣሉት? የምትጨካከኑት? የምትወነጃጀሉት? የምትገዳደሉት? የምትነቃቀፉት? የምትተቻቹት? በሐሰት የምትመላለሱት? በክህደት የምትኖሩት? ርኩሰትን የምትፈፅሙት? በአጠቃላይ በበደልና በኃጢአት የምትወድቁት?

እረ ተዉ እናንተ ሰዎች፤ ማንነታችሁን በሚገባ አስተውሉ፤ የሰይጣናትን ጭከና ተረዱ፤ እኔ ያደረግኩላችሁን አስተውሉ፤ እኔ ምን በደልኳችሁ? በዚህች ምድርም ቢሆን የምትበሉትን የምትጠጡትን ሰጠዋችሁ። ብታምኑኝም ባታምኑኝም አድሎ ሳላደርግ እንደ ቅን ሓሳባችሁና መልካም ተግባራችሁ ብቻ ሒሊናችሁ ሰላምንና እርካታን እንድታገኙ ፈቀድኩ። እናንተ ግን ቅን ሐሳብ ከመያዝና መልካም ተግባር ከመስራት ይልቅ ክፋትና ተንኮል፣ ቂምና በቀል በመያዝ፤ በትዕቢትና በአመጻ ህይወት እየተመላለሳችሁ ሰላማችሁንና እርካታችሁን ታርቃላችሁ ። እውነተኛን ደስታ ግን ከዚህች ምድር አታገኙም፤ እናንተ ደስታ የምትሏት የሒሊና እርካታችሁን ነው። እርካታ እንዲህ ደስ የምታሰኛችሁ ከሆነማ ስለምን እውነተኛዋን ደስታ ለማግኘት አትተጉም? ስለ ምን እሷን ለማግኘት አትናፍቁም? ለተመረጡ አካሄዳቸውን ፍጹም ከኔ ጋር ላደረጉ ለሰከንድና ለደቂቃት ብቻ እውነተኛውን ደስታ በመጠኑም ቢሆን አሳውቃችኋለሁ፤ ይህም የበለጠ እንዲናፍቋትና በእምነትና በቅድስና ህይወታቸው እስከ መጨረሻ እንዲጸኑ ነው ።

ምን ያላደርግኩላችሁ ነገር አለ? በምድራዊ ህይወታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ከመስጠት በተጨማሪ ነብያትን እያስነሳሁ የህይወትን መንገድ ገልጽኩላችሁ፤ ከዛ በተጨማሪ ማስተዋሉ ካላችሁ እጅግ የሚከብደውን ሊሆን የማይችለውን ነገር ግን የሆነውን፤ ከአእምሯችሁ በላይ የሆነውን በሰማይ ያሉ

ሠራዊቶቼን (እጅግ ብዙ በጣም እጅግ ብዙ ከቁጥር በላይ የሆኑ መላእክትን) ያስገረመ፤ ባደረጋችሁት የአመጻ ድርጊት ደግሞ እጅግ ያሳዘነና ያስቆጣ ታላቅ ውለታ አድርጌላችኋለሁ ::

ይኸውም አምላካዊ ባህርዬን ዝቅ አድርጌ ይህን ደካማና ጎስቆላ ሥጋችሁን ገንዘብ አድርጌ ልክ እንደ እናተው ሰው ሆንኩላችሁ:: ሁሉን ባለጠጋ የማደርግ፤ ሁሉ ነገር በኔ ለኔ የሆነ፤ እንደ ችግረኛ ድሃ ሰው ባልጠፋ ቦታ በከብቶች በረት ውስጥ ተወለድኩ፤ ሄርድስ ሕፃናትን ሲገል አቅምና ሃይል እንደሌለው ሰዉ ከእናቴ ድንግል ማርያም፣ ከአሳዳጊዬ ዮሴፍና ሰሎሜ ጋር በመሆን ወደ ግብፅ ተሰደድኩ፤ ተንከራተትኩ፤ ከዚያም ተመልሼ በገሊላ ናዝሬት እንደ ሰው ጥቂት በጥቂቱ አደኩ፤ተመላለስኩ፤ ዘመን የማይቆጠርልኝ በለበስኩት ስጋ ዘመን ተቆጥሮልኝ በሰላሳ (30) ዓመቴ ለህዝቡ የህይወትን ቃል አስታማርኩ፤ ግን እናንተ የህይወትን ቃል አልቀበል አላችሁ::

በዚህም አላበቃችሁም፤ በእውነት እየኖርኩ ስለ እውነት እየመሰከርኩ እንደ ሐሰተኛና ወንጀለኛ እኔን እውነተኛ ፈራጅ ዳኛውን በምድራዊ ዳኛ ፊት አቆማችሁኝ፤ በሐሰት ወንጀላችሁኝ፤ ገረፋችሁኝ፤ ዘበታችሁብኝ፤ ተፋችሁብኝ፤ ሰደባችሁኝ፤በጥፊ መታችሁኝ፤ የብርሃን አክሊል የማድል አምላክ የሾህ አክሊል አደረጋችሁብኝ፤ መስቀሉን አሸከማችሁኝ እንደ አቅመ ቢስ አዳፋችሁኝ፤ ያም አልበቃ ብሏችሁ በችንካር እጆቼንና እግሮቼን በመስቀል ላይ መታችሁኝ፤ ሰቀላችሁኝ፤ የእናንተ ጭካኔ ምኑ ይነገራል! በመስቀል ላይ ሁኜ ሞቴን (ነፍስ ከስጋዬ መለየትን ስጠባበቅ) ተጠማሁ ብላችሁ እንኳን ሳትራሩልኝ መራራ ሀሞትን አቀረባችሁልኝ፤ አላዘናችሁልኝም::

«ሞተ» መባል የማይገባኝ አልፋና ያሜጋ መጀመሪውና መጨረሻው፣ ያልኖርኩበት ጊዜ የሌለ ፣የማልኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ የአብረሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ሞተ ተባልኩ፤ ነገር ግን ሕያው አምላክ ነኝና እናንተ ሰዎች ሞታችሁ እንደማትቀሩ ለማሳየት በሶስተኛው ቀን በተገለጽኩበት ስጋዬ መልሼ ተዋህጄው ተነሳው፤ ለሐዋርያትና ለደቀመዛሙርቴ ተገልጽኩ፤ በአርባኛዉ ቀን ወደ ሰማያት አረገ::በአምሳኛዉ ቀን የመንፈስ ቅዱስን ፀጋ አደልኩ፤ ያኔ ተስፋቸዉን ምድራዊ አድርገዉ የነበሩ ደቀመዛሙርቴ ሐሳባቸዉ፣ ንግግራቸዉ፣ ተግባራቸዉ ፍጹም ሰማያዊ ሆነ:: በመጨረሻም በፍርድ ቀን እንዲሁ በስጋ እንደምታውቁኝ ተገልጬ ለእያንዳንዱ እንደ ስራውና እምነቱ እፈርድለታለሁ፤ እፈርድበታለሁ::

እናንተ ሰዎች ታድያ ምን ያላደረኩላችሁ ነገር አለ!? ቸርነቴንና ፍቅሬን እስከዚህ ድረስ ነበር የገለጽኩላችሁ:: እናንተ ግን ክዳችሁ አስካዳችሁ፣ በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ዕለት ዕለት ታስቆጡኛ ላችሁ:: እንደ እናንተ አመጻና ጭካኔ ቢሆን ይህች ዓለም ወደ አለመኖር ማለፍ ነበረባት፣ እናንተም ነጻነታችሁ ተገድቦ ትኖሩ ነበር:: ግን የኔ ባህርይ እንደ እናንተ አይደለምና በትዕግስት ቁጥራችሁ ከርኩሳን መናፍስት ቁጥር እኩል እስከሚሆን እየጠበኩ ነው :: ያኔ ሁሉ ነገር ያበቃል፣ ርኩሰትና አመጻ ይቆማል፣ በማንኛውም ቦታ ማንም ፍጡር በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶ የሚሠራዉ የአመጽና የርኩሰት ተግባር አይኖርም ፣ እያንዳንዱ በሰራው ስራና በእምነቱ ተፈርዶለትና ተፈርዶበት እንደ ፍርዴ ይኖራል::

ሰይጣንንም ከእንግዲህ በደንብ እወቁት፤ በሕሊናችሁ እያደረ ሐሳባችሁን የሚሰርቅና የሚያዘናጋ እሱ ነው:: ከተወለዳችሁበት ቀን አንስቶ እስከ ዕለተ ሞታችሁ ድረስ በተግባራችሁም፣ በንግግራችሁም፣ በምታስቡት ሓሳብ ሳይቀር ከእናንተ የማይለይ፤ ያደረጋችሁትንና የተናገራችሁትን ብቻ ሳይሆን ያሰባችሁትን የሚያውቅና የሚሰማ ዋንኛ ከሳሻችሁ ነው :: ለዚህም ነው ስለምትሰሩት ስራና ስለምትናገሩት ቃል ብቻ ሳይሆን ንሰሐ መግባት ያለባችሁ፤ ስለምታስቡት ክፉና ርኩሰት ሐሳብ ጭምር ልትጸጸቱና እኔንም በውስጥ ሕሊናችሁ ይቅርታ ልትጠይቁኝ ይገባል:: በሕሊናችሁ ስትጸጸቱና እኔንም ይቅርታ ስትጠይቁ እርሱ ጠላታችሁ ሰይጣን ያዳምጣልና ክስም አይኖረውም::

በተግባርና በንግግር ስለምትፈጽሙት በደልና ኃጢኣት ግን በምድር ላይ የማሰር ሆነ የመፍታት ሙሉ ስልጣን የሰጠዋቸው ካህናት አባቶች ስላሉ፤ ኃጢኣታችሁን እየተናዘዛችሁና ቀኖናችሁን እየፈጸማችሁ፤ በደላችሁና ኃጢኣታችሁ በምትቀበሉት ቅዱስ ስጋና ክብር ደሙ አማካይነት ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ይደመሰሳል :: ጠላታችሁ ሰይጣንም በእናንተ ላይ ክስ አይኖረውም ::

እኔ በፍጡሬ ላይ አድሎ የማደርግ አይደለሁም:: ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት)በነጻ ሕሊናቸው ተመርተው ስለካዱኝና ስለአመጹብኝ ብቻ ከሰማያት አውጥቼ በዚህች ምድር በጉስቁልና ህይወት እንዲኖሩ፤ ከዓለም ዕልፈት በኋላ ደግሞ በዚህች ምድር ላይም እያሉ ስለአመጹብኝና እናንተንም ከገነት ክብራችሁ ሰላሳሳቷችሁ በገሃነም እሳት የባሰ የምቀጣቸው ከሆነ፤ እናንተ የሰው ልጆች ትልቅ ውለታ ውዬላችሁ በበደልና በኃጢአት የምትኖሩ ከሆነ፤ እንዴት አድርጌ አልቀጣችሁ! እጅግ እቀጣችኋለሁ:: ስለዚህ ስላለፈው ኃጢአታችሁ ንስሐ ግቡ :: ከእንግዲህ በኋላ በኃጢአት ህይወት አትመላለሱ ::

በአመጻ ደረጃ እናንተ ሰዎች ከሰይጣናት የምትብሱ ናችሁ::ይኸዉም ሰይጣናት በአመጻና በትዕቢት እንዲሁም እናንተን ከመፈታተን ዉጭ እርስ በእርሰ የማይጣሉ፣ የማይገዳደሉ፣ የማይጨካከኑ፣ የማይሰራረቁ፣ የማይመቀኛኙ፣ የማይከፋፈሉ፣ እናንተን ለማጥቃት ህብረትና አንድነት ያላቸዉ ናቸዉ:: እናንተ ግን በተግባራችሁ፣ በንግግራችሁ፣ በሐሳባችሁ ከመርከሳችሁና ከአመጻ ስራችሁ በተጨማሪ እርስ በእርስ የምትጣሉ፣ የምትገዳደሉ፣ የምትጨካከኑ፣ የምትሰራረቁ፣ የምትመቀኛኙ የምትከፋፈሉ፣ለመልካም ነገር ህብረትና አንድነት የሌላችሁ ናችዉ::

ሰይጣናት የእምነት ጽናታችሁንና መልካም ተግባራችሁን እንዲሁም እያሰባችሁት ያለውን ሐሳብ ስለሚያውቁ፤ ሌት ተቀን እናንተን የሚጥሉበትንና የሚያሰናክሉበትን መንገድ ሁል ጊዜ ስለሚያዘጋጁ፤ ህሊናችሁን ለትዕቢትና ለአመጻ፣ ለክፋትና ለተንኮል፣ ለርኩሰት ሐሳብ፣ ለገንዘብ ጥቅምና ለስልጣን፣ ለክብርና ለዝና አሳልፋችሁ እንዳትሰጡ:: ሰይጣናት በእርግጠኝነት የማያውቁት ከምታስቡት ሐሳብ ውጭ ያለውን የወደፊት ተግባር፣ ንግግር፣ ሐሳብ ጭምር ነው :: ሐዋርያ ተብሎ የነበረ ይሁዳ፣ ምሁር አንደበተ ርቱዕ የተባለ አርዮስ፣ ጳጳስ የተባለ ንስጥሮስ፣ መንኩሴ የተባለ ሉተር ወዘተ.. ወደ ክህደትና ጥፋት የሄዱት፤ ሕሊናቸውን ለክፋትና ለተንኮል፣ ለአመጻና ለትዕቢት፣ ለገንዘብና ለስልጣን አሳልፈው ስለሰጡ ነው:: ስለዚህ በስጋ ሞት እስከምትጠሩ ድረስ በእምነታችሁና በመልካም ተግባራችሁ እንዲሁም በቅድስናና በጽድቅ ሥራችሁ እስከመጨረሻዉ መጽናት ይኖርባችኋል::

ሰይጣናት ለማንም ሰዉ የማይራሩ፤ ከህፃን እስከ አዋቂ ድረስ በመንፈሳዊ ህይወቱ ከደከመ እስከ ቅድስና ደረጃ ከደረሰ ሰዉ ጭምር የሚፈታተኑ፤ከሆነላቸዉ የሚጥሉ ጨካኞች ናቸዉ:: ለዚህም ነዉ በብልታችሁ ዉስጥ በመመላለስና በማስቀንዘር ዝሙትን እንድትፈጽሙ የሚፈታተኗችሁና እንድትወድቁ በማድረግ ከኔ የሚያጣሏችሁ:: ለሰከንድና ለተወሰነ ደቂቃ ፈተናዉን መቋቋም አቅቷችሁ ራሳችሁን ለዝሙት፣ ርኩሰት ለሆነዉ ግብረ ሰዶምና ለማይገባ የስጋ ፍትወት ባህርይና ጠባይ ትዳርጋላችሁ:: ስለዚህ ማንም ሰዉ ራሱን ሳያመጻድቅ በትህትና በመመላለስ ህይወቱን በቅድስና መምራት ይኖርበታል::

እናንተ የሰይጣናት ማደሪያና ተላላኪ የሆናችሁ ጠንቋዮች፣ መተተኞችና ድግምተኞች፣ አስማተኞች፣ሟርተኞች፤ የእርሱ የዲያብሎስ ባሪያ በመሆናችሁ እናንተን የሚንከባከባችሁ ይመስላችኋልን ? የቁም ስቃይ ያሳያችኋል፤ ያሳብዳችኋል፤ መከራና ችግር ያፈራርቅባችኋል፤ ሰላምና እርካታ ያሳጣችኋል:: ከዚህ ቅርፊት ስጋችሁ ተለይታችሁ ስትመጡ ደግሞ በሲኦልና በገሃነም እሳት የባሰውን ስቃይና መከራ ትቀበላላችሁ :: በእናንተ የሚላኩ ሰይጣናት ቀርቶ በራሳቸው ወደ

ሰዎች ሕሊና የሚገቡ፣ የሚወጡ ሰይጣናት እንኳን ካለ እኔ ፈቃድ ማንንም አንዳች ሊያደርጉ ሆነ ሊጎዱ አይችሉም:: ነገር ግን በሚከናወነው ነገር ሰይጣናትም ሆኑ ሰዎች በራሳቸው ስልጣን ጉዳት ያደረሱ ይመስላቸዋል ::

እናንተ በተለያየ ሱስ በሲጃራ፣ በጫት፣ በሺሻ፣ በሀሽሽ፣ በአደንዛዥ ዕፅ... ወዘተ የተጠመዳችሁና በመጠጥ በስካር ዉስጥ ያላችሁ ፤በመጀመሪያ ዲያብሎስ በሕሊናችሁ እንዲነግስ ለምን ፈቀዳችሁለት? ለምንስ ማደሪያዉ ሆናችሁ? በሱስና በስካር የሚጫወትባችሁ ሕሊናችሁን እንደሚፈልገው መምራት ስለቻለና እናንተም በርኩሰት ተግባር ተባባሪዎቹ ስለሆናችሁ ነው:: እናንተ ናችሁ ታድያ ህዝብን መምራትና ማስተዳደር የምትችሉት? ራሳችሁን እንኳን መግዛት ያልቻላችሁ፤ ሕሊናችሁን ዲያብሎስ እንደልቡ የሚያሽከረክረው፤ እንዴት የኔን ፈቃድ ልትፈጽሙና ልታስፈጽሙ ትችላላችሁ? በምንም ሁኔታ ሕሊናው ዲያብሎስ (ሰይጣናት) የተቆጣጠሩት ሰው መልካም የሆነውን የኔን ፈቃድ ሊፈጽም ሆነ ሊያስፈጽም አይችልም ::

ሕሊናቸውን (ነፍሳቸውን ) እኔ የምቆጣጠረውና የቅዱስ መንፈሴ ማደሪያ የሆኑት ሰዎች ብቻ ናቸው የኔን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ :: እነዚህም ሕሊናቸው ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት ፣ ከቅናት፣ ከትዕቢት፣ ከአመጻ፣ ከርኩሰት የራቀ፤ ቀና የሚያስቡና መልካም የሚሰሩ እውነተኛ ሰዎች ናቸው:: ሕሊናቸው ከርኩሰትና ከኃጢአት ሲርቅ፤ በረድኤት እቀርባቸዋለሁ፤ የተለያየ ፀጋ አድላቸዋለሁ:: እንኳን የሚታየውን ቀርቶ የተሰወረውን ምስጢር እግልጽላቸዋለሁ፤ ማስተዋልና ጥበብን እሰጣቸዋለሁ፤ እንዲሁ ድምፅ በሌለው ቋንቋ አነጋግራቸዋለሁ::

እናንተ የአዳምና የሔዋን ዘሮች መሆናችሁን ያልተረዳችሁ፤ በዘረኝነት ፣ በጎጠኝነት ህይወት ያላችሁ፤እርስ በእርስ በነገድ፣ በዘር፣ በቋንቋ የተለያያችሁ፤ እስቲ ወደ ኋላ ትውልዳችሁን ቁጠሩ? ከአባታችሁ ከኖህ ትዘላላችሁ ወይ? ከካም፣ ከሴም፣ከያፌት ከአንድ ወንድማማች የተወለዳችሁ አይደላችሁምን? ታድያ ለምን እርስ በእርስ ትጣላላችሁ?ትከፋፈላላችሁ? ትለያያላችሁ? ከዚያም አልፎ በጥላቻና በቂም በቀል ትፈላለጋላችሁ:: ይህም አልበቃ ብሏችሁ ራሳችሁን በማመጻደቅ ሌላውን ትንቃላችሁ፤ ታንቋሽሻላችሁ፤ ለመሆኑ ክርስትና የሚለው ቋንቋ ገብቷችኋልን? ለማነው እኔ መከራ ተቀብዬ በመስቀል ላይ የተሰቀልኩት? ለማነው ክርስትናን የመሰረትኩት? ለማነው የህይወት ቃል የተናገርኩት? ለሁላችሁ ለአዳምና ሔዋን ዘሮች አይደለምን! ?

እንግዲህ ታላቅ ለመባል ከፈለጋችሁ አካሄዳችሁን ከኔ ጋር አድርጉ ፈቃዴንም ፈጽሙ:: ከዚያ ውጪ በኃጢአትና በርኩሰት የምትመላለሱ ከሆነ ሁላችሁም ታናሾችና ተራ ወራዳ ኃጢአተኛ ሰዎች ናችሁ :: ለዚህም ነው በዘመነ ስጋዌ «አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል:: ወንድሙን ጨርቃም የሚለው የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል:: ደንቆሮ የሚለው ሁሉ <u>የገሃነም እሳት</u> ፍርድ ይገባዋል» በማለት ያስተማርኩት::

እንኳን በዘራችሁና በጎሳችሁ ተመጻድቃችሁ ሌላውን ማንቋሸሽና ማሳነስ ቀርቶ በተፈጥሮ አካለ ስንኩል (አካል ጉዳተኛ) የሆነውን በአካለ ስንኩልነቱ ብትሰድቡት ምድራዊ ፍርድ ብቻ አይደለም አሁን ያላስተዋላችሁትና ከቁም ነገር ያልቆጠራችሁት የገሃነም እሳት ፍርድ ይጠብቃችኋል:: እንግዲህ ፍርዴ ምን ያህል ጥብቅ እንደሆነ ተረዱ:: ሁላችሁም በኔ ፊት እኩል ናችሁ:: አባትነቴን ፈልጋችሁ በሚገባ ካከበራችሁኝና ካመለካችሁኝ ልጆቼ ትሆናላችሁ፤ ካላከበራችሁኝና በሚገባ ካላመለካችሁኝ ደግሞ እንደ ርኩሳን መናፍስት ጠላቶቼ አማጽያን ትሆናላችሁ፤ በመጨረሻም ከእነርሱ ጋር ገሃነም እሳት ውስጥ ትኖራላችሁ::

በእናንተ ዕይታ ታላላቅ ሰዎች የምትሏቸው የሀገር መሪዎች፣ ባለሀብቶች፣ ምሁራን፣ ታዋቂ የመድረክ ሰዎች  ልጅ መባል ምን ያህል ስሜት ይሰጣችኋል? የእነዚህ መጨረሻ ህይወታቸው የማይታወቅ የፍጡር ልጅ መባል እንዲህ የተለየ ስሜት የሚሰጣችሁ ከሆነ፤ የእኔ፣ የሁሉ ፈጣሪ የሆንኩት፤ የፈለኩትን ሁሉ ማድረግ የምችል የአምላካችሁ ልጅ መባልን ስለምን አትፈልጉም!?እናንተ ግን ክብር አይወድላችሁምና በስጋ ዓይናችሁ ለምታዩት ነገር ብቻ የምትገዙና ቦታ የምትሰጡ ናችሁ ::

እናንተ ይህች ዓለም የምትሏትን ምድር እንደ ትልቅ ተመልክታችሁ በምታዩት ነገር የምታደንቁና ግራ የገባችሁ፤ ፍልስፍናችሁ የተገደበ ከዚህች ምድር የማይወጣ ነው:: እናንተ የተለያየ ስያሜ የምትሰጧቸዉ ፕላኔቶች በዚህችዉ ሚጢጢዋ ምድር ዉስጥ የሚገኙ ሲሆን ፤ ይህም የኔ ፈቃድ ብቻ ሲሆን ነዉ በዚህች ምድር ዉስጥ የሚገኙትን ነገሮች ማወቅ የምትችሉት:: ይህች ምድር ለኔ፤ በመሬት ላይ ያለውን የውሃ አካል ስፋት በሳይንሱ አውቃችኋል፤ ከመሬት ብዙውን ሥፍራ ሸፍናል፤ አንዲት ብናኝ አፈር ውሃ አካል ላይ ስታስቀምጡ ያላቸውን የመጠን ልዩነት አስተዋላችሁ? የአንድ አፈር ብናኝ እና ውሃ የሞላበት የመሬት አካል ስንት ስንተኛ እጅ ነው? (ያለው ሬሾ) ስንት እንደሚሆን ንገሩን እስቲ? በዚህች በጠባቡ አእምሮቻችሁ ልታሰሉት ትችላላችሁን? አእምሮችሁ  ውስን ቁጥር ብቻ ነው የምታውቁት ከካትሪሊየን ከዝያም ብታልፉ ትንሽ ቁጥር ነው የምታውቁት፤ ታድያ ይህች ምድር ከኔ መንግስትና ግዛት ስትነጻጻር ከላይ ለንጽጽር ከቀረበላችሁ የአፈር ብናኝና የመሬት ዉሀ አካል እጅግ በጣም እጅግ ያነሰች ናት::ምክንያቱም የኔ ግዛት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ (ኢንፊኒቲ) ነዉ::

እንኳን ይህች ምድር ቀርታ ዓለም፣ ሰማያት፣ ማረፍያው ቦታ፣ ሲያል ተጠቃለው እግዚአብሄር በአምላካዊ ባህርይው በሚገለጽበት ከአማናዊ ህዋ ጋር  ሲነጻጸር ያለው መጠን ፤ በዚህች ምድር ውስጥ አራት ትንንሽ ፊኛዎች ተነፍተው በአየር ላይ ቢሆኑና ከዚህ ምድር ስፋት ጋር ቢነጻጸር የእነርሱ መጠን ለምድር (ለዓለም) ስፋት መጠን ቢካፈል የሚመጣው ክፋይ መጠን (ሬሾ) ስንት ስንተኛ እንደሚሆን በሕሊናችሁ በምታውቁት ቁጥር መጠን መግለጽ እንደማትችሉ ሁሉ ከላይ የተገለጹት ምሳሌያዊ ባህርይ የሆኑ ቦታዎች ተደምረው ለአማናዊ ህዋ  ስፋት መጠን ቢካፈል ሰንት ስንተኛ እንደሚሆን እጅግ በጣም እጅግ ትንሽ በመሆኑ በሰው አእምሮ ደረጃ አይደለም በቅዱሳን መላእክት ደረጃ እንኳን ሊታወቅ አይችልም::  ምክንያቱም አማናዊ ህዋ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው የወሰን ስፋት መጠኑ የማይታወቅ (ኢንፊንተ) የሆነ ነዉ:: የኔ ግዛት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ይህች ዓለምም ወደ አለመኖር ሳሳልፋት ግዛቴ የምትሆን ናት ፤ አሁን ግን እናንተና ሰይጣናት የምትኖሩበት፣ የምትቀጡበት፣ የምትጠሩበት ግዛት ናት::

የእናንተ እውቀትና ፍልስፍና ሊገልጽ የሚችለው እናተ ዓለም በምትሏት በዚህች  ሚጢጢዋ ምድር ላይ ያለውን ነገር ብቻ ነው:: ይህንንም የምታውቁት እኔ ስፈቅድ ብቻ ነው:: የእናንተ የእውቀት ደረጃ ከዚህች ምድር አያልፍም:: መንፈሳዊ    ጸጋ የበዛላቸው ሰዎች ግን ይህችን ምድር ብቻ አይደለም በዓለም ውስጥ ስላለችው፣ ከዓለም ውጭ ስላሉት ሲያልና ማረፍያቦታ፣ ሰማያት እንዲሁም አማናዊ ህዋ ያውቃሉ፤ ያስተውላሉ፤ ከዚያም አልፎ በሰማያት ያለውን ምስጢር ይመለከታሉ:: ይህንን ምስጢር የምገልጽ እኔ ብቸኛ አምላክ ነኝ::

እናንተ ራሳችሁን እንደ ትልቅ እየቆጠራችሁ ብዙ ነን ፤  እልፍ አዕላፍ ነን የምትሉ፤ ከአዳም ጀምሮ እስካሁን ያላችሁት ሰዎች ቁጥር ብትደመሩ እንኳን በሰማያት ካሉት ቅዱሳን መላእክት ቁጥር አንድ መቶኛ አትሆኑም:: በኔ ዘንድ ቁጥራችሁ ከአንድ የማይበልጥ ነው:: የዚህች ምድር አጠቃላይ ዘመናችሁ ካለፉት ጊዜያት ጭምር በኔ ዘንድ ከአይን ቅጽበት ያነሰ ጊዜ (የማይክሮ ሰከንድ ጊዜ) ያህል

እንኳን አይሆንም፡፡ ዓለም ሳይፈጠር የማይቆጠርበት ጊዜ የነበረ፣ የሌለሁበት ጊዜ የሌለ ነውና፣ እንኳን በስጋ ህይወት የምትኖሩበት እጅግ ትንሽ ዘመን ቀርቶ እንደእናተ ክህደትና የሐሰት ትምህርት በሚሊዮን በቢሊዮን የሚቆጠር ዕድሜ እንኳን ቢኖራችሁ በኔ ዘንድ ከአይን ቅጽበት ያነሰ ጊዜ (የማይክሮ ሰከንድ) ጊዜ አይሆንም ፡፡ ስለዚህ ጥበባችሁና እውቀታችሁን እኔን በመፍራት ለሰው ዘሮች የሚጠቅም መልካም ስራ ለመስራት አውሉት እንጂ የክህደት ፍልስፍና የአመጽ ተግባር መፈጸምያ አታደርጉት፣ እኔን በመፍራትና በእውነት በማምለክ ብትመላለሱ ኖሮ የሰው ዘርን የሚጨርስና የሚያጠፋ መሳሪያ ባልሰራችሁ ነበር፡፡

እናንተ የቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (የኢቮልሺን) አማኞች፣ ሰዉ የተገኘዉ ከተፈጥሮ ነዉ፣ «የቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ አማካይነት ከእንስሳ ነዉ» በማለት ህልዉናዬን በመካድና በማስካድ ላይ ያላችሁ፣ ማፈሪያና ያበደ አእምሮ (ሕሊና) የያዛችሁ፣የእብደታችሁን ዋጋ በዚህች ምድር ላይም እከፍላችኋለሁ፡፡ የዘራችሁትን የክህደትና የአመጻ ፍሬ ታጭዳላችሁ፡፡

እናንተ የሰዎችን ባህርይና ጠባይ ያልተረዳችሁ ሰዎች፣ በዚህች ምድር እጅግ የተለያየ ፀባይ ያላቸው ሰዎች ሲኖሩ ለኔ እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ የንሰሐ ሕሊና የሌላቸው ሶስት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡እነዚህ ሰዎች ከዲያብሎስ ወይንም ከርኩሳን መናፍስት (ከሰይጣናት)የማይለዩ ናቸው፡፡

አንደኛው ሰው ትዕቢት ነው፣ እነዚህ የፈርኦን ወንድምና እህቶች፣ ፈርኦንን ይመራ የነበረ ዲያብሎስ የሚመራቸው ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ነጻ ህሊና ቢኖራቸውም ውስጣቸው በትዕቢት የተሞላ ስለሆነ እንኳን ሰዎችን ሰምተው ከሕሊናቸው ሊጸጸቱ ቀርቶ እኔ አምላካቸው ተገልጬ «ይህን አታድርጉ፣ ይህ ስህተት ነው፣ ከስህተታችሁ ተመለሱ፣ ይህን ብታደርጉ መከራና ችግር ይደርስባችኋል» ብላቸው፣ የማይቀበሉ፣ ቢቀበሉም ተመልሰው ወደ ጥፋት ህይወትና ወደ ሞት የሚመለሱ ሰዎች ናቸው፡፡

ሁለተኛው ሰው ክፋት ነው፣ እነዚህ ሰዎች የአስቆርቱ የይሁዳ ወንድሞችና እህቶች፣ ይሁዳ ይመራዉ የነበረ ዲያብሎስ የሚመራቸው ናቸው፣ እነዚህም ነጻ ሕሊና ቢኖራቸውም ውስጣቸው በክፋትና በተንኮል የተሞላ ስለሆነ እንኳን ሰዎችን ሰምተው ሊለወጡ ቀርቶ እኔ አምላካቸው ተገልጬ በመሀከላቸው በመመላለስ ባስተምር ተአምርና ፈውስ ባደርግ ከማወቅና ከማየት በስተቀር አስተውለው ወደ ንስሐ የማይመለሱ ሰዎች ናቸው፡፡

ሦስተኛው ሰው አመጻ ነዉ፣ እንዚህ ሰዎች የአርዮስ ወንድሞችና እህቶች፣ አርዮስን ይመራ የነበረ ዲያቢሎስ የሚመራቸው ናቸው፡፡ እነዚህም ነጻ ሕሊና ቢኖራቸውም ውስጣቸው ለአመጻ የተነሳሳ ስለሆነ፣ የነበረ እውነትን ቢያውቋትም ማስተዋል ስለሌላቸው ከእውነት ተሰናክለው በራሳቸው ሐሳብና ፍልስፍና በፈጠሩት ክህደት ውስጥ የሚመላለሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት ሰዎች የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ናቸው ፡፡

ከነዚህ ሦስት ሰዎች ውጭ ያሉ በተለያየ ኃጢአት ቢወድቁ እንኳን ፣ በነጻ ሕሊናቸው ተመርተው ንሰሐ ሊገቡና አካሄዳቸውን ከእግዚአብሄር ጋር ማድረግ የሚችሉ የንሰሐ ሕሊና (የንሰሐ ልብ) የሚያገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች መምህራን በሚገባ ሊያስተምሯቸውና እውነትን ሊያስዉቋቸው ይገባል፡፡ ወደ እኔ ለመመለስ አያስቸግሩኝም ለታላቅ ክብርና ለማያልፈው ሰማያዊ መንግስት ላበቃቸው እችላለሁ፡፡

እናንተ አእምሮ ሕፃናት (በስጋችሁ ትልቅ መስላችሁ በአስተሳሰባችሁ እንደ ህጻን የሆናችሁ) ሰዎች፣ ይህን ልክስክስ ጠባያችሁን አርቁ፣ ራሳችሁን ግዙ፣ ነገሮችን በማመዛዘንና በማገናዘብ ተመላለሱ፣ እንደስሜታችሁ አትነዱ፣ ግብታዊ አትሁኑ፣ በእርጋታና በጽናት ሕይወት ኑሩ፡፡ የጽናት

ፀጋ እንድታገኙ በጸሎት፣ በጾም፣ እንዲሁም ቃሌን በመስማት እየተጋችሁ በቅን ሐሳብና በመልካም ተግባር ተመላለሱ ::

እናንተ አእምሮ ቀላሎች (ህሊናችሁን የምትሸጡ)፤ ከነፈሰው ጋር የምትነፍሱ፤ እንደ ቦይ ውሃ ወደ ወሰዷችሁ የምትነዱ፤ የአመጻ ልጆችን ተከትላችሁ በደልና ኃጢአት የምትፈጽሙና የምታስፈጽሙ ሰዎች፤ ይህን የረከሰ ጠባያችሁን አርቁ፤ ስለእውነት ጸንታችሁ ቁሙ እንጂ ለጊዜዊ ጥቅም፣ ስልጣን፣ ክብር፣ ዝና ብላችሁ ሕሊናችሁን አትሸጡ፣ ሁሉ ይቀራል፣ ሁሉ ይሻራል:: እናንተም በጸሎት፣ በጾም፣ ቃሌን በመስማት እየተጋችሁ በቅን ሐሳብና በመልካም ተግባር ተመላለሱ ::

እናንተ አእምሮ አዋቂዎች (የተለያይ የእውቀት ጸጋ ያላችሁ) ሰዎች፤ እውነትን ተቀብላችሁና በእውነት ፀንታችሁ ለህዝባችሁና ለሀገራችሁ የሚጠቅም ነገር ብቻ በመስራት እኔን በመፍራትና በማምለክ ኑሩ:: የዚህ አለም እዉቀት፣ ጥበብ፣ ባለጠግነት፣ ክብር፣ ስልጣን፣ ዝና፣ ድሎትና ምቾት ፍሬ እንዳታፈሩ እንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ሁሉን በመናቅ ተመላለሱ፤ በትህትና ራሳችሁን በኔ ፊት ዝቅ አድርጋችሁ ኑሩ ::

እናንተ አእምሮ ጽኑአን (ላመናችሁበት ነገር መስዋዕት ከመሆን የማትመለሱ)ሰዎች፤ ከእንግዲህ ፅናታችሁ ስለ እውነት ስለ እኔ ብቻ ይሁን፤ ያለፈው እንደ ሥጋ ፈቃዳችሁ የተመላለሳችሁበት ዘመን ይብቃ፤ በስጋችሁም፣በነፍሳችሁም ለምትጠቀሙበት ህይወት ብቻ ትጉ:: እናንተን ለአገልግሎት እፈልጋችኋለሁና በስጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ስትቀመጡ እስከ ህይወታችሁ ፍፃሜ ድረስ በእውነት በማገልገልና በቅን ሐሳብ በመልካም ተግባር ብቻ ኑሩ :: እናንተ ስቃይ፣ መከራ፣ እስራት፣ ግድያ፣ ስቅላት፣ መቃጠል፣ ችግር ቢመጣባችሁ ሕሊናችሁን የማትሸጡ፤ ላመናችሁበት የምትጸኑ ጽኑዓን፤ ራሳችሁን መካድ የምትችሉ በመሆናችሁ በማስቀምጣችሁ ወንበር ላይ ሁል ጊዜ ቅንና እውነተኛ ፍርድ ብቻ ፍረዱ::

የሰው ዘሮች በሙሉ፤ ሰይጣናት መቼም ይሁን መቼ በየትኛውም ቅድስና ደረጃ ላይ ድረሱ፤ ነፍሳችሁ ከስጋችሁ እስክትለይ ድረስ እናንተን ለማሰናከል፣ ለመፈታተን፣ ለማጎሳቆል ተስፋ የማይቆርጡ ጠላታችሁና ከሳሻችሁ ስለሆኑ እስከ ምድራዊ ህይወታችሁ ፍጻሜ ድረስ በቅድስናና ንጽህና ህይወት ጸንታችሁ ኑሩ:: በመንፈሳዊ ህይወታችሁም ደግሞ እንደተሰጣችሁ ፀጋ ትጉ፤ ካለ ፀጋችሁ ከአለም ጋር አትታገሉ፤ እንደተሰጣችሁ ፀጋ እኔን በመፍራት ህይወታችሁን ምሩ::

እናንተ በእውነተኛው አገልግሎት ያላችሁ እውነትን አውቆ አልቀበልም፤ አልኖርበትም የሚላችሁን ሰው ጸልዩለት እንጂ ዘመናችሁን ሁሉ ብታስተምሩት ወደ እውነት ስለማይመለስ ጊዜአችሁን በእርሱ አታጥፉ:: ይልቁን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በስጋ ፈቃዳቸው ተሸንፈው በስህተት ጎዳና የተጓዙትንና የሚጓዙትን በሚገባ አስተምሯችሁ፤ እናንተም በህይወት በመስበክ እንደ ቃሉ ሆናችሁ በመገኘት ሰዎችን ወደ እውነተኛው በረት አስገቡ፤ የኔ የሆኑትን ሁሉ የንስሐ ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ ወደ እውነት ይመለሳሉ::

እናንተ በጦርነት፣ በመግደል፣ በማስገደል የተስፋፋችሁ የክህደት እምነት የተከተላችሁ፤ ለመሆኑ እኔ ብፈልግ በአምላካዊ ስልጣኔ ሁሉም የሰው ዘሮች በግዳጅ እንዲያምኑኝና እንዲያመልኩኝ ማደረግ የሚያቅተኝ ይመስላችኋልን? እናንተ በጉልበታችሁ አስገድዳችሁ ማሳመን ከቻላችሁ፤ ሃያል የሆንኩ ሁሉን ማድረግ የምችል አስገድጄ እንዲያምኑኝና እንዲያመልኩኝ ማደረግ የሚሳነኝ ይመስላችኋል? ማስተዋል የተሳናችሁ፤ የምታምኑትን በሚገባ ያልመረመራችሁ፤ «ሰውን መግደል ያጸድቃል» የሚል እምነት ያለው እንዴት የህይወት መንገድ ሊሆን ይችላል? በጦርነትና በግዳጅ የሚስፋፋ እምነት እንዴት ከእግዚአብሄር ሊሆን ይችላል? «አንድ ወንድ ለአንድ ሴት» ብዬ በሐዲስ ዘመን ያጸናዋትን

ጋብቻ « አንድ ወንድ ብዙ ሴቶችን ማግባት ይችላል » ብሎ አመንዝራነትን የሚያስፋፉ እምነት እንዴት ሰዎችን ለጽድቅ ያበቃል!?

ከእንግዲህ አስተውሉ፤ የሞት መንገድን ከህይወት መንገድ ለይታችሁ እወቁ፤ እኔ እግዚአብሄር በነጻነት የምገዛና ሰዎች በነጻ ሕሊናቸው ተመርተው እውነት እንዲቀበሉ ነው ቀድሞ ነብያትን ያስነሳሁት፤ እኔም ስጋ ለብሼ የተገለጽኩት፤ ሐዋርያት ደቀ መዛሙርትን ያሰማራሁት፤ በዚህ ምክንያት ነብያቶቼ ሆኑ ሐዋርያቶቼ በዓለም ሲሰማሩ ስለእውነት ተገረፉ፣ ተሰቃዩ ፣ ታሰሩ፣ ተገደሉ ፣ተቃጠሉ፣ በአጠቃላይ የተለያየ መከራና ስቃይ ከሰዎች ደረሰባቸው እንጂ ማንንም ሰው እየገደሉ፣ እያሰቃዩ ፣ እያስገደዱ፣ መከራ እያደረሱ አላሳመኑም፤ አልሰበኩም ።

እውነተኛ እምነት (ሃይማኖት) ፤ ሰዎች ለምድራዊ ህይወታቸው ጥቅም፣ ስልጣን፣ ክብር፣ ዝና፣ ብልጽግና ብለው የሚቀበሉት ሳይሆን ፤ በምድራዊ ህይወታቸውም በረከትን አግኝተው ለመባረክና ከሁሉ በላይ ግን የማታልፈውን ሰማያዊ መንግስት ለመውረስ ነው። ስለእውነት መከራ፣ ችግር፣ እስራት፣ ስቃይ፣ ግድያ ቢመጣባችሁ እስከ ስጋዊ ህይወታችሁ ፍጻሜ ድረስ በእምነታችሁ ጸንታችሁ ራሳችሁን ለሰማዕትነት አዘጋጁ እንጂ፤ በግድያ፣ በማሰቃየት፣ በአመጻ ህይወት ውስጥ አትመላለሱ።

መልዕክተኛ በሆኑት ነብያቶቼ፣ሐዋርያት፣ሰማዕታት ላይ የማያምኑ ሰዎችና እንደቃሌ የማይኖሩ አስመሳይ አገልጋዮች መከራ ሲያደርሱባቸው፣ ሲያሰቃያቸው፣ ሲገሉአቸው፣ ሲያስሯዋቸው፣ ሲያንገላቷቸው ዝም የምለው መበቀል አቅቶኝ ይመስላችኋልን!? እነዚህ አገልጋዮቼ ለታላቅ ክብር እንዲበቁ ለማድረግና የብርሃን አክሊል ላድላቸው ነው እንጂ፤ ግፈኛ ሰዎችን የቁም ስቃያቸውንና በመቅሰፍትም ወዲያው ላጠፋቸው እችላለሁ። ነገር ግን የግፈኞች ፅዋ ሞልታ እስክትፈስ ታግሼ ታግሼ ባላሰቡትና ባልጠበቁት መንገድ ተበቅያቸዋለሁ፤ አሁንም እበቀላቸዋለሁ። በዚህች ምድር ላይ ሆነ በሚመጣው ዓለም ከእውነተኛ ፍርዴ ማንም ሊያመልጥ አይችልም » ይላል አዶናይ፣ አሌሻዳይ፣ ፀባኦት በመባል የሚታወቀው የመጥምቁ ዮሐንስ፣ የወንጌላዊዉ ዮሐንስ፣ የቅዱስማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ጴጥሮስ ፣ጳዉሎስ አምላክ።

## ምዕራፍ አራት

« እናንተ ኢየሱስ ክርስቶስን በነብይነት፣ በአማላጅነትና በፍጡር ደረጃ የምትቀበሉ፤ በውኑ የእግዚአብሄርን ቃል ማስተዋል በእናንተ ዘንድ አለን? አንዳች የለም። ቢኖርማ እርሱ ከእግዚአብሄር የሆነ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሄር ያነሰ እውነተኛ የእግዚአብሄር መልእክተኛ ሰው ሆነ ሌላ ፍጡር፤ ራሱን ከእግዚአብሄር ጋር የሚያስተካክል ማን ደፋር ነው? «እኔና እግዚአብሄር አንድ ነን» የሚል ማን ደፋር ነው? «እኔ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ» የሚል የትኛው የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነው? «እኔን አያችሁ ማለት እግዚአብሄርን አያችሁ ማለት ነው» ብሎ የሚያስተምር የትኛው የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነው? የእግዚአብሄርን ስም ሳይጠራ በራሱ ስልጣን ሊያድን፣ ሊፈውስ፣ ይቅር ሊል የሚችለው፤ በአጠቃላይ የእግዚአብሄር መልእክተኛ የሆነ ፍጡር ማነዉ ደፋር ራሱን ከእግዚአብሄር ጋር የሚያስተካክለው!?

ታላቁ የእምነት አባታችሁ አብርሃም እንኳን፤ የእግዚአብሄርን ክብርና የራስን ማንነት ተረድቶና አስተዉሎ «እኔ አፈርና አመድ ነኝ» ያለው፤ ታላቁ ንጉሥ እንደ ልቤ የተባለው ዳዊት«እኔ ትል የሞተ ውሻ ነኝ » ያለው፤ ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ «እኔ ጭንጋፍ ጥራጊ ነኝ» ያለው፤ ታድያ በእምነታቸው ታላቅ የተባሉ እግዚአብሄር ቅድስና ማእረግ የሰጣቸው አባቶች፤ ምንም እንኳን አካሄዳቸው ከእግዚአብሄር ጋር ቢሆንም የአምላካቸውን ቅድስና ክብር የራሳቸውን ደካማነትና ማንነት በሚገባ ስለተረዱና መሪያቸው መንፈስ ቅዱስ ሰለሆነ፤ የበዛላቸውን ጸጋ ቦታ ሳይሰጡት፤ ራሳቸውን በእግዚአብሄር ፊት አዋርደዋል፤ ዝቅ ዝቅ አድርገዋል ፡፡

ታላቁ ነብይ ሙሴ ፤ ምንም እንኳን አካሄዱን ከእግዚአብሄር ጋር ያደረገ እግዚአብሄርም ከፍ ከፍ ያደረገው ቅዱስ አገልጋይ ብዙ ተአምራትን በእግዚአብሄር ስም ያደረገ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ሰዓት በእስራኤል ልጆች መካከል በምድረ በዳ የእግዚአብሄርን ስም ሳይጠራ በራሱ ስልጣን ውሃ አውጥቶ በመስጠቱ ተገስጿል፤ ተስፋ የተሰጣቸውን የከነዓንን ምድር በርቀት ተመለከታት እንጂ አልገባባትም። እግዚአብሄር በአምልኮቱ ቀነዒ ነውና ፍጡር ሆነ የእርሱ መልእክተኛ እንኳን ራሱን ከእግዚአብሄር ጋር የሚያስተካክለውን ቀርቶ በሚገባ የማያከብረውን ይገስጻል፤ ይቀጣል፤ ያዋርዳል።

እንግዲህ እናንተ ማስተዋል ያጣችሁ የአዳምና የሔዋን ዘሮች፤ እኔ አምላካዊ ባህርዬን ዝቅ አድርጌ ሰው ሆኜ በዚህች ምድር ላይ በምመላለስበትና በማስተምርበት ወቀት በዘመኑ ለነበሩ የተናገርኩትን ሕያው ቃል የኔን መከራ በማሰብ በሐዘን የኖረው እጅግ የምወደው ደቀመዝሙሬ ዮሐንስ በወንጌሉ ላይ እንደጻፈላችሁ « እኔ ና አብ አንድ ነን፣ እኔን ያየ አብን አየ፣ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በኔ አለ፣ ማንኛውም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ፣ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ሕያዋን ትሆናላችሁ፣ ትዕዛዜን በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ፣ ራሴን እገልጽለታለሁ፤ ስለ እናንተ አብን እንደለምን የምላችሁ አይደለሁም።» እያለ ያስተማረውና የተናገረው ማነው? እኔ አይደለሁምን። ታድያ ፍጡር፣ ነብይ ፣ የእግዚአብሄር መልእክተኛ አማላጅ ሆኖ ራሱን ከእግዚአብሄር ጋር አንድ የሚያደርግ አለን! ? ከላይ የተነገሩትን አባባሎች ደፍሮ የሚናገር የእግዚአብሄር መልእክተኛ አለን ? እግዚአብሄር በባህርይው ለአምላክነቱ ቀናዒ የሆነ እንጂ፤ የሚደፋፈረውን ፍጡር ሆነ ነብይ ወይም አማላጅ ዝም የሚል ይመስላችኋልን !? እኔ ግን በባህርይ፣ በህልውና፣ በአገዛዝ፣ በስልጣን፣ በመፍጠር፣ ከአብ ጋር ፍጹም አንድ የሆንኩ ፤የማንበላለጥ፣ የማንቀዳደም፣ የነበርን፣ ያለን ፣ ሕያው ሆነን የምንኖር ስለሆነ፤ አምላካችሁና ፈጣሪያችሁ በመሆኔ፤ ከላይ ያሉትን ትምህርቶች ሰጥቻለሁ። እናንተ ግን ማስተዋል የጎደላችሁ ስለሆነ፤ የምትሰናከሉበትን ቃላት እየመረጣችሁ በሞትና በክህደት ህይወት ትመላለሳላችሁ።

ይህው ምርጡ ደቀመዝሙር ዮሐንስ በራዕይ መፅሐፉ የጻፈላችሁን አስተውሉ «ያለውና የነበረው የሚመጣው ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ» ይላል ። እንዲህም አለ «አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲዖል መክፈቻ አለኝ ።» እንዲህ ብለህ ጻፍ «ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» ታድያ ማነው ፍጡር፣ ነብይ ፣ አማላጅ ሆኖ ራሱን «ፊተኛ ውና መጨረሻው፣ አልፋና ዖሜጋ፣ የነበረው ሕያውም የሆነው» እያለ የእግዚአብሄርን ስምና ክብር የሚይዝ አለ ወይ? እንዲህ ሲል እግዚአብሄር ዝም ይለዋል ወይ? ከእግዚአብሄር እንደሆነ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል ወይ? እኔ ግን እግዚአብሄር ስለሆንኩ ከላይ የተባሉትን ተናገርኩ። እናንተ ግን በቅን ሐሳብና በመልካም ህይወት ሆናችሁ እውነትን ስላልፈለጋችሁ፤ እግዚአብሄር መሆኔን ኣላስተዋላችሁም። ከዚያም አልፋችሁ ክዳችሁኝ ታስክዱኛላችሁ፤ ሰድባችሁ ታሰድቡኛላችሁ፤ ተጠራጥራችሁኝ እንዲጠራጠሩኝ ታደርጋላችሁ፤ ታድያ እንዴት እጅግ የባሰ ፍርድ አትቀበሉም!? በደንብ ትቀበላላችሁ ።

እናንት በቅዱሳን መጽሐፍ ላይ የተጻፈዉን የማታስተዉሉ ክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ብትሆኑም የዋሃን እንዳይሰናከሉ፤ እኔም እንደፍጡር ምዕራፍና ቁጥር እየተቀስኩ ላስረዳችሁ፤ «ሰዎች ሁሉ አብን እንዲያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድ ሁሉ ለወልድ ሰጠሁ እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም።» ዮሐ.5:22-23፣ ማነው ፍጡር ሆነ፤ የእግዚአብሄር መልእክተኛ አማላጅ እንደ እግዚአብሄር አክብሩኝ የሚል? «አብን ያየ ማንም የለም ከእግዚአብሄር ከሆነ በቀር እርሱ አብን አይቷል። እውነት እላችኋለሁ በኔ የሚያምን የዘላለም ህይወት አለው።» ዮሐ.6:46-47 ።ማነው ፍጡር ሆኖ እግዚአብሄርን እንደ እግዚአብሄርነቱ በአማናዊ ባህርይው ያየው?

«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የህይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» ዮሐ.8:12፣ የትኛው ፍጡር ወይንም የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነው እንደዚህ በድፍረት ሊናገር የሚችለው ?

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል ነፍሴም ስለበጎች አኖራለሁ። ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱም ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ **አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ**።» ዮሐ.10: 14-16፣ ማነው ፍጡር ሆኖ ወይንም ከእግዚአብሄር ያነሰ ሆኖ እግዚአብሄርን እንደ አምላካዊ ባህርይው አውቀዋለሁ ብሎ በእርግጠኝነት ስለሚሆነው ነገር መናገር የሚችል? እኔ ግን እግዚአብሄር ነኝና በእርግጠኝነት ተናገርኩ። እንግዲህ በጎቼ የሆናችሁ ወደ እውነተኛዉ ቤቴ ትመጣላችሁ፤ በአንድ እረኛም ትጠበቃላችሁ።

«እኔና አብ አንድ ነን።» ዮሐ.10:30፣ የትኛውም ፍጡር ወይንም የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነዉ እኔና እግዚአብሄር አንድ ነን የሚል። ፍጡር ሆኖ ከእግዚአብሄር የሆነ ይህን የድፍረት ቃል ቢናገር የደቂቃ እድሜ እግዚአብሄር የሚሰጠዉ ይመስላችኋልን!? አይሰጠዉም፤ያዋርደዋል፤ ያጠፋዋል እንጂ። እኔ ግን ከኔ በላይ ማንም ስለሌለ ፈጣሪ እግዚአብሄር ስለሆንኩ በድፍረት ይህን አልኩ።

«እኔ የአባቴን ስራ ባላደርግ አትመኑኝ ባደርገው ግን፣ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።» ዮሐ.10:37-38፣ ራሱ እግዚአብሄር ካልሆነ በስተቀር ማነው እንዲህ ደፍሮ ሊናገር የሚችለው ?

«ኢየሱስም - እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም:: እኔንስ ብታውቁ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር:: ከአሁን ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለ ::

ፊልጶስ - ጌታ ሆይ አብን አሳየና ይበቃናል አለው:: ኢየሱስም አለው - አንተ ፊልጶስ፣ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል እንዴትስ አንተ - አብን አሳየኝ ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለው አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አልተናገርሁ፤ ነገር ግን በኔ የሚኖረው አብ እርሱ ስራውን ይሰራል:: እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለራሱ ሰለ ስራው እመኑኝ ::

እውነት እውነት እላችኋለሁ በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ስራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፣ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ:: ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ::» ዮሐ.14:6-14፣ እናንተ ማስተዋል የጎደላችሁ፤«ኢየሱስ ነብይ ነዉ፣ አማላጅ ነዉ፣ ፍጡር ነዉ» እያላችሁ የምትሰድቡኝ፤ ከእግዚአብሄርነቴ ያሳነሳችሁኝ፤ ነገረ መስቀሌን ከንቱ ያደረጋችሁ፤ ማነው ፍጡር ከእግዚአብሄር ያነሰ ሆኖ ይህን ቃል ሊናገር የሚችል? እኔ ራሴ እግዚአብሄር ስለሆንኩ በድፍረት የተናገርኩት ከኔ በላይ አለቃ የኔ ፈጣሪ የለምና፤ እኔው ነኝ የነበረው፣ ያለው፣ ሕያው ሆኖ የሚኖረው አምላክ ::

«ይህን በምሳሌ ነግሬአችኋለሁ፤ ነገር ግን ስለ አብ ለእናንተ በግልጥ የምናገርበት እንጂ ከዛ ወዲያ በምሳሌ የማልናገርበት ሰዓት ይመጣል :: በዚያም ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለእናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ እናንተ ስለወደዳችሁኝ ከእግዚአብሄር ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና :: ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ ::» ዮሐ.16:25-28፣ ያለው እኔ አይደለሁምን? ታድያ እናንተ እኔ ሁሉን አድራጊ ሆኜ ሳለ ከእግዚአብሄርነቴ አሳንሳችሁኝ አማላጅ ነው እያላችሁ የምትሰድቡኝ፤ የምታስክዱኝ፤ በውኑ እናንተ ክርስቲያን የሚለውን ስም ስለያዛችሁ ከኔ የሆናችሁ ይመስላችኋልን? እናንተ የዲያብሎስ ናችሁ:: እርሱ እኔን ለማስካድና ለማስቆጣት በፈጠረላችሁ «ኢየሱስ፣ ክርስቲያን» የሚል ስያሜ እንድትጠቀሙ እያደረገ ከህይወት መንገድ ወደ ሞት፣ ከእምነት ወደ ክህደት የወሰዳችሁ ናችሁ ::

«ያለውና የነበረው የሚመጣው ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ያሜጋ እኔ ነኝ ይላል::» ዮሐ.ራዕይ1:8፣ «ባየሁት ጊዜ እንደሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ ስር በታች ወደቅሁ :: ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህ አለኝ - አትፍራ፣ ፊተኛውና መጨረሻው ህያውም እኔ ነኝ፣ሞቼም ነበርሁ እነሆም ፣ ከዘለዓለም እስከ ዘላለም ድረስ ህያው ነኝ፣ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ:: እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ::» ዮሐ.ራዕይ 1:17-19 ብዬ እጅግ ለምወደው ደቀ መዝሙሬ ዮሐንስ የተናገርኩት እኔ አይደለሁምን? እኔ አልፋና ያሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ ፈጣሪ እግዚአብሄር ባልሆን ኖሮ፤ እንዲህ ብዬ እናገራለሁኝ? ሰው ባልሆን ኖሮ ሞቼም ነበርሁ ብዬ ይህንን ቋንቋ እጠቀም ነበርን? ለእናንተ ስል ነው ባህርዬን ብቻ ዝቅ አድርጌ ካለሁበት ቦታ ሁሉ ሳልጎል፤ አምላክነቴ ሳይለወጥ፤ ክብሬ ሳይቀነስ ሰው የሆንኩት ::

«በሰምሬኔስም ወደለው ቤተ ክርስትያን መላእክ እንዲህ ብለህ ፃፍ - ሞቶ የነበረው ህያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» ዮሐ.ራዕይ 2:8 ብሎ የተናገረው እኔው እግዚአብሄር አይደለሁምን? እኔ ሞቼ ነበር ብዬ ስናገር ያላፈርኩ፤ እናንተ ግን እግዚአብሄር ሰው ሆነ፣ መከራ ተቀበለ፣ ተሰደበ፣ ተገረፈ፣ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሶስተኛው ቀን ከሙታን

ተለይቶ ተነሳ ፣ ከዚያም ወደ ቀደመው ክብሩ ተመለሰ፣ አረገ ለማለት ይከብዳችኃል፤ ታፍሩበታላችሁ:: ተጠራጥራችሁ ታጠራጥራላችሁ:: እናንተ በውኑ ከእኔ ትበልጣላችሁን? የማንስ መልእክተኞች ናችሁ? የሚያጠራጥራችሁ የዲያብሎስ ናችሁ::

« በትያጥሮንም ወዳለው ወደ ቤተክርስትያን መላአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ - እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሄር ልጅ እንዲህ ይላል» ዮሐ.ራዕይ 2:18 ብሎ የተናገርው እኔ የእግዚአብሄር ልጅ የሰው ልጅ የተባልኩት አምላካችሁ ፈጣሪያችሁ ጌታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኑኤል መድኃኔአለም አይደለሁምን? ስለምን በእግዚአብሔርነቴ ትጠራጠራላችሁ ? ስለ አብ ሆነ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማወቅ የምትችሉት በመጀመሪያ እኔን እንደ እግዚአብሄርነቴ ስታውቁኝና ስታምኑብኝ ብቻ ነው! ያኔ እኔ ወልድ ቃል የተባልኩትን ፣ አብን ፣ መንፈስ ቅዱስን በሚገባ ታውቃላችሁ፤ መጀመሪያ እኔን ሳታውቁ አብንም፣ መንፈስ ቅዱስንም በአጠቃላይ እውነት የተባላችሁን በምንም ዓይነት ልታውቁ አትችሉም:: እኔ ብቻ ነኝ የእውነት ምስጢር የምገልጽ፤ በዚህች ምድር ሁኑ በሌላ ዓለም ሁኑ ቤትም ስፍራ ሁኑ ሁሉን የምቆጣጠር፤ የማውቅ የሁሉ ፈጣሪና አስገኚ እኔ ብቻ ነኝ:: ከኔ በላይ እኔን የሚያዝ እኔን የፈጠረ ማንም የለም:: የነበረ ያለሁ ህያው ሆኜ የምኖር አልፋና ዖሜጋ እኔ ብቻ ነኝ::

ከዚህ በተጨማሪ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ እንዳይገባችሁና እንዳትሰናከሉ ይኸው እጅግ ለምወደው ደቀመዝሙር ለዮሐንስ የገለጽኩለትን ምስጢር በወንጌሉ መጀመሪያ ላያ «በመጀመሪያ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበር፣ ቃልም እግዚአብሄር ነበር:: ይህ በመጀመሪያዉ በእግዚአብሄር ዘንድ ነበር:: ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንካ ያለ እርሱ አልሆነም :: በእርሱ ህይወት ነበረች፣ ህይወትም የሰው ብርሃን ነበረች::» ዮሐ.1:1-5 ና «ቃል ስጋ ሆነ ጸጋንና እዉነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለሁ ክብር የሆነዉን ክብሩን አየን::» ዮሐ.1:14-15 ብሎ የጻፈላቸሁ፤ ከኔ ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ፣ መጀመሪያውም መጨረሻውም የሁሉ አስገኝ እንደሆንኩ እንድታዉቁና እነደ እግዚአብሄርነቴ እንድታመልኩኝ ነበር:: ይሁንና ውስጣችሁ አመጻናትዕቢት፣ ክፋትናተንኮል ስለሞላባችሁ ወደ እውነት ማወቅ ልትመጡ አልቻላችሁም::

እናንተ በእውነተኛ እምነት ውስጥ ሆናችሁ ነገር ግን ተጠራጣሪዎች የሆናችሁ፤ በጎቼ እንዲጠራጠሩ በማድረግ በሁለት ልብ ያላችሁ፤ እኔ ስናገር ያላፈርኩትን «ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ህያው ነኝ» እንዳላልኩ «ሞቶ የነበረው ህያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» እንዳላልኩ፤ እናንተ ምንድናችሁና ነው የኔን መከራ መቀበል፣ መሰቀል፣ መሞትና መነሳት ለመመስከር መድፈር ያቃታችሁ? እንኳን እኔ፤ እናንተም እኮ አትሞቱም፤ ነገር ግን ቋንቋችሁ ስለሆነ ነፍስ ከስጋ ስትለይ «ሞተ» ስለምትሉ፤ ይህንኑ ቋንቋችሁን ተጠቅሜ« ሞቼም ነበርሁ ሞቶ የነበረው» እያልኩ ስናገር እንደ እናተ ፍጡር ወይስ ከእግዚአብሄር ያነስኩ መልእክተኛ ተላላኪ አድርጋችሁ ቆጠራችሁኝን? ወይስ ለኔ ቀንታችሁ እንዴት እግዚአብሄር ተሰቀለ፣ ሞተ እንላለን እያላችሁ ጥብቅና ቆማችሁልኝ ነውን? አስመሳይ ሸንጋዮች፤ በእምነታችሁ ባዶ የሆናችሁ፤ ፍሬ የማታፈሩ የወንጌል እንቅፋቶች ናችሁ:: እናንተም ወደ መንግስቴ አትገቡም ሌላውም እውነትን አውቆ ሰማያዊ መንግስቴን ወርሶ ከኔ ጋር እንዳይኖር ማሰናከያ ሆናችሁ:: የባሰ ፍርድ ይጠብቃችኋል::

እናንተ በተለያየ መልክ እንዲህ የወቀስኳችሁ፤ እነማን እንደሆናችሁ አላወቃችሁምን? እናንተ «ነብይ ነዉ» ብላችሁ በስሜ የምትነግዱ የካዳችሁኝ በእስልምና «እምነት» ዉስጥ ያላችሁ፤ « አማላጅ ነዉ» ብላችሁ በስሜ የምትነግዱ የካዳችሁኝና ዕለት ዕለት የምትሰድቡኝ እጅግ ያስቆጣችሁኝ የፕሮቴስታንት የተለያየ ክፍልፋይ «እምነት» ዉስጥ ያላችሁ፤ በእዉነተኛዋ ሃይማኖት በኦርቶዶክስ

ተዋህዶ ስም የምትነግዱ ተሐድሶዎችና በመናፍቃን መንፈስ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዉስጥ የምትመላለሱ ተተራጣሪዎች ናችሁ:: እናንተ ሁላችሁ በሐዲስ ኪዳን እናምናለን ብላችሁ በስሜ የምትነግዱ አመጸኞች ስለሆናችሁ፤ ከሌሎች ከማያምኑብኝ የበለጠ የባሰ ፍርድ ይጠብቃችኋል::

እናንተ የአዳምና የሔዋን ዘሮች ሰዎች ሁሉ፤ የከሀዲዎችን፣ የመናፍቃንን ፣ የአመጸኞችን መንገድ አትከተሉ:: እውነት የሆነውን የህይወት መንገድ ምረጡ:: የእግዚአብሄርን አንድነትና ሦስትነት (ምስጢረ ሥላሴ ) ፣ የእግዚአብሄር ሰው መሆን ምስጢር (ምስጢረ ስጋዌ)፣ ዘላለማዊ ህይወት (ትንሳኤ ሙታን)፣ ስለጥምቀት፣ ስለ እውነተኛው የአምላክ ስጋና ደም (መለኮት የተዋሀደው ስጋና ደም) ፣ ስለ ንስሐ፣ ስለ ቅድስና ህይወት፣ስለ ትሩፋት ስራ በአጠቃላይ ከእግዚአብሄር ስለሆነ እውነት በተመለከተ እውነትን ይዛ ከጸናችሁ ሀገር፤ በእውነተኛ እምነት የሚያመልኩ የዋህ ህዝብ ካሉበት፤ ራሳቸውን ክደው መስቀሉን ተሸክመው የዚህችን ዓለም ክብርና ብልጽግና ንቀው በዋሻና በየገዳማቱ ሌት ተቀን በጸሎትና በምስጋና የሚተጉ የተመረጡ ጻድቃን ካሉበት፤ ሌት ተቀን በማህሌት፣ በሰዓታት፣ በኪዳን ፣ በቅዳሴ ፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት የሚተጉ ካህናትና ምዕመናን ካሉባት፤ ራሳቸውን ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሰውተው ብሉያትና ሐዲሳትን (መጽሐፍ ቅዱስን) ፣ ዝማሬን፣ ቅኔዉን ፣አቋቋሙን፣ በአጠቃላይ የተለያዩ ምስጋናዎችንና ትምህርት በትጋት የሚሰጡ ሊቃውንትና መምህራን ከሞሉባት፤ ሰማያዊ ዜማና ቋንቋ ተስጥቷት በሰማዊያን መላእክት ስርዓት ምስጋናን የሚያቀርቡ አገልጋዮች ካሉባት፣ ደም ሳያፈሱና ምንም ሳይጠራጠሩ ክርስትናን የተቀበሉ፣«ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸዉ» ብዬ በዘመነ ስጋዌ የመሰከርኩላቸዉ ህዝቦች የሚኖሩባት፣ ቀድሞ በህገ ልቦናና በህግ ኦሪት እኔን በመፍራት ይመላለሱ የነበሩ ህዝቦች ካሉባት፣በሰሜን በደቡብ በምስራቅ በምዕራብ በመሃል አገር በአጠቃላይ በአራቱም ማዕዘን ሁል ጊዜ «መንግስተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ » እያለች የምታዉጅ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ካለችበት፤ የአደራ እናታችሁ የመዳኛችሁ ምክንያት እመቤታችሁ ቅድስት ድንግል ማርያም እጅግ የምትፈቀርበትና የምትከበርበት፤ምርጥ ባለሟሎቼ ቅዱሳን መላእክት፣ ነብያት ፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን በተለየ ሁኔታ የሚከበሩባት፤ አሁን በእናንተ ዘንድ በአመጻ ልጆች የክፋትና የተንኮል፣ የርኩሰትና ክህደት ተግባር ምክንያት በድህነቷ፣ በጦርነት ፣ በረሃብ፣ በችግር፣ በበሽታና በስደት የምትታወቅ፤ በእናንተ ዘንድ ተራ የሆነች ሀገር፤ነገር ግን በሰማያዊ ሠራዊት የምትጠበቅ የምስጢር ሀገሬ ከሆነች፤ እምነቷም እኔ የመሰረትኩት፣ ሐዋርያት የሰበኩት፣ አበው ሐዋርያት ያስፋፉት፣ ሰማዕታት የተጋደሉላት፣ ሊቃውንት መምህራንና ጻድቃን ያጸኑት፣ **እውነተኛውን ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ይዛ ካለች ሀገር ከኢትዮጵያ ተማሩ**፤ እምነቷንም ተከተሉ:: በረከቷና እውቀቷ ከራሷ አልፎ ለዓለም የሚተርፍ ነው ::

እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮች አፈጣጠራችሁ ታላቅ መሆኑን፤ የቀደመ ክብራችሁና ፀጋችሁ እንደ ቅዱሳን መላእክት የነበረውን፣ አካሄዳችሁን ከኔ ጋር የምታደርጉ ከሆነ ደግሞ እጅግ ታላቅ ተሰፋና ለታላቅ ለተቀደሰ ክብር የምትበቁ፤ ነገር ግን ማንነታችሁና ተስፋችሁን ያላወቃችሁና ያላስተዋላችሁ፤ ተስፋችሁን ምድራዊ አድርጋችሁ ሌት ተቀን ለዚህ ለቅርፊት ስጋችሁ ብቻ የምትተጉ፤ በቅን ሐሳብና በመልካም ህይወት ብቻ መኖር ሲገባችሁ በክፋት፣ በተንኮል፣ በትዕቢት፣ በአመጻ፣ በዝሙት፣ በጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ በጥላቻ፣ በዘረኝነት ፣ በጎጠኝነት ፣ በዘፋኝነት ፣ በዳኪርተኝነት ፣ በቂም በቀል፣ በጠብና ክርክር ፣ በክህደትና በመናፍቅነት፣ በስርቆትና በግድያ፣ በሱስ፣ በአጠቃላይ በርኩስ መንፈስ ፍሬ ረክሳችሁ ያላችሁ፤ በስጋም በነፍስም የምትጠቀሙበትን ፍቅርን፣ ትህትናን፣ ቸርነትን ፣ ቅንነትን ፣ የዋህነትን ፣ ታማኝነትን ፣ ትጋትን፣ እምነትን ፣ በአጠቃላይ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑትን ይዛችሁ መኖር ሲገባችሁ ፤ ሕሊናችሁን ለዲያብሎስ

ማደሪያ ያደረጋችሁ፤ የእግዚአብሄር ልጅነት ማእረግ ተሰቷችሁ ልጅነትን ያልፈለጋችሁ፤ ክብርን ያልወደዳችሁ፤ ምድራዊ ክብራችሁን ልንገራችሁ ::

ይህ የለበሳችሁት ስጋ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ የተላበሰ፤ ሌት ተቀን በርኩሳን መናፍስት የምትፈተኑ፤ የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚዎች ከሆናችሁ ሌት ተቀን የሚቀጠቅጣችሁና የሚያሰቃያችሁ፤ ይህ የምታመልኩትና የምታስመልኩት ገላችሁ የሚሸትና በኋላም አፈር ውስጥ ገብቶ የምስጥ መብል የሚሆን ፤ ይህን ያደፈ ባህርያችሁን የሚትጸየፉትን ዓይነ ምድር (ሰገራ)ና ሽንት በሆዳችሁ ይዛችሁ የምትዞሩ፤ ይህ የምታመልኩትና የምታስመልኩት ስጋችሁ ጽዳት በጎደለው ጊዜ በቁማችሁ የምትሸቱ፤ ካለ እርካታ ሌት ተቀን ተሯሩጣችሁ በስርቆት፣ በማጭበርበር፣ በመስገብገብ፣ በስስት፣ በግፍ፣ በጭቆና፣ በዘመድ ባዝማድ፣ በብልጣ ብልጥነት፣ ያከማቻቻችሁት የአመጻ ገንዘብንና ንብረት እንዲሁ ማን እንደሚጠቀምበት ለማታውቁት አስረክባችሁ ባዶአችሁን በኔ ፊት ለፍርድ የምትቆሙ፤ ይህ በምኞትና በሐሳብ ሌት ተቀን የምትተጉለት ስልጣን፣ ክብር፣ ዝና፣ እውቀት ሁሉ የሚሻር፤ የማይጸና፤በምድራዊ ህይወታችሁ ፍጻሜም ያ ሁሉ ክብራችሁ ቀርቶ ሬሳ የምትባሉ፣ አቅማችሁ ተራ የሆነ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ስትያዙ ጭብጥ የማትሞሉ፤ በትዕቢትና በእብሪት ስትናገሩና ስትደነፉ ሁሉን ማድረግ የምትችሉ የሚመስላችሁ፤ ብይዛችሁ የምትጨፈለቁ ብለቃችሀ የምትበታተኑ ወራዶች፤ በአጠቃላይ ክብርን የናቃችሁ ያቃለላችሁ፤ በእውነት አንኖርም ብላችሁ ያመጻችሁ ከዳተኞች ናችሁ ::

እኔ ግን ወድጃችሁና አክብሬያችሁ የአምላክነት ባህርዬ ክብሬ ሳይገድበኝ መለኮታዊ ባህርዬን ዝቅ አድርጌ ይህን ደካማና ጎስቋላ ስጋችሁን ተዋህድኩ፤ አከበርኩት፤ ከፍ አደረኩት፤ ለሕያውነት ህይወት እንዲሆናችሁ ቅዱስ ሥጋዬን ቀርሼ ክቡር ደሜን አፍስሼ ሰጠዋችሁ:: እናንተ ግን አቃለላችሁት፤ አንበላም አንጠጣም አላችሁ::

በዚህች ምደር መመላለስና ማስተማር የማይገባኝ ፈጣሪያችሁ፤ የእናንተን ፍጡር የሆነ ስጋ ለብሼ በመካከላችሁ ተመላለስኩ፤ ወጣሁ ወረድኩ፤ መምህራንን የምሾም ነብያትን የማስነሳ እኔው ራሴ መምህራችሁና ነብያችሁ ሆንኩ፤ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ በሚገባ አስተማርኳችሁ፤ ህይወትና ትንሳኤ ምን እንደሆነ አስረዳዋችሁ፤ የመፈወስ፣ተዓምራት የማድረግ፣ትንቢት የመናገር፣ የማሰርና የመፍታት ሁሉን የማድረግ ስልጣን ሰጠዋችሁ:: ስለ እውነት ፈተና ቢመጣባችሁ፣ ብትሰደዱ፣ ብትሰደቡ፣ ብትገረፉ፣ ብትሰቃዩ፣ብትዋረዱ፣ብትሰቀሉ፣ብትሰየፉ፣ብትቃጠሉ፣ ብትገደሉ፣ በጽናትና በአኮቴት እንድትቀበሉ ሁሉን ሆኜ ሁሉ ተደርጎብኝ አርአያ ምሳሌ ሆንኳችሁ::

እስቲ ንገሩኝ ሁሉን ማድረግ የሚችል፤ የነበረ፣ ያለ፣ ሕያው ሆኖ የሚኖር፣ ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፣ ከፈለገም ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፣ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው ፣ሁሉ በእርሱ ለእርሱ የሆነ ፣ ያለእርሱ ፈቃድ ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፣ ሁሉን አዋቂ፣ አዶናይ ኤልሻዳይ ያህዌህ ጸባኦት በመባል የሚታወቅ፣ የአብርሃምና የይሳሐቅ የያዕቆብ የሙሴ የዳዊት የኤርምያስ የዳንኤል የኤልሳ የኤልያስ የነብያት አምላክ የሆነው እግዚአብሄር፤ ሊሰደብ፣ ሊገረፍ፣ ሊዘበትበት፣ ሊወነጀል ፣ ሊሰቃይ፣ ሊሰቀል፣ ሊገደል ይገባው ነበር ወይ!? እናንተ ግን ይህንን ሁሉ አደረጋችሁብኝ! ታድያ እንደ ክፋትና አመጻ ተግባራችሁ ገሃነመ እሳት አይደለ ሌላ የባሰ ነገር ፈጥሬ ብቀጣችሁና ባሰቃያችሁ አያንሳችሁምን!? የባሰ ፍርድና መከራ መቀበል የለባችሁምን ?

እኔ ሰው የሆንኩት እናንተን ከሞት ወደ ህይወት ለማምጣት፤ በአዳምና በዘሮቹ ላይ የፈረድኩትን የሲዖል ፍርድ ለመሻር፤ በንጽህናና በቅድስና ህይወት እንድትመሩ፤ በማያልፈው መንግስቴ ሕያው ሆናችሁ እንድትኖሩ ለማድረግ፤ በኃጢአት የወደቃችሁ ንስሐ በመግባትና በመጸጸት ይቅርታ

እንድታገኙ፤ በደላችሁንና ኃጢአታችሁ ቅዱስ የሆነው ስጋዬን ስትበሉ ክቡር ደሜን ስትጠጡ ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ለመደምሰስ አይደለም ወይ ሰው የሆንኩት?

እናንተ ግን በጥምቀት ከእኔ ልጅነትን አግኝታችሁ በቅዱስ ስጋዬና በክቡር ደሜ ታትማችሁ መክበርን አልፈለጋችሁም፤ ክብር አልወደዳችሁም፤ ከህይወት ይልቅ ሞትን መረጣችሁ፤ ከቅድስና ይልቅ ርኩሰትን ፈለጋችሁ፤ ከማመን ይልቅ ክህደትንና መናፍቅነትን መረጣችሁ፤ ታላቅነት የሆነውን ትህትና ትታችሁ ውርደት የሆነውን ትዕቢትን መረጣችሁ፤ ከመታዘዝ ይልቅ አመጻን ተከተላችሁ፤ ከበረከት ይልቅ መርገምን ፣ በጽናትና በትጋት ከመኖር ይልቅ ስንፍናን መረጣችሁ፤ እኔ አምላክ ስሆን ትህትናን ለማስተማር የፍጡሮቼን የሐዋርያትን እግር አጠብኩ፤ እናንተ ግን ራሳችሁን አስመለካችሁ:: እንግዲህ እንደ ምርጫችሁ የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ:: እኔ ላደርግላችሁ የሚገባኝን ሁሉ ክብሬን ሳልፈልግ ተራ ቦታ በሆነው በከብቶች በረት ውስጥ ከመወለድ ጀምሮ እንደ አቅመ ቢስ ተሰድጄ፣ ተንከራትቼ፣ መከራ ተቀብዬ፣ ተሰቅዬ፣ ሞቼላችሁ ትንሳኤን አሳይቻችኋለው:: የምላችሁን ብትቀበሉ በቃሌ ብትኖሩ ጥቅሙ ለእናንተ ነው ለኔ አንዳች የምትጨምሩልኝ የምትቀንሱብኝ ነገር የለም:: ነገር ግን የከፈልኩላችሁን ዋጋ ከንቱ በማስቀረታችሁ ከሌሎቹ በበለጠ ሁኔታ በፍርድ ቀን ፍዳችሁን ትቀበላላችሁ::

እናንተ በድፍረት ኃጢአት የምተመላለሱ፤ እንኳን ለምትሰሩት ኃጢአት ቀርቶ ለምትናገሩት ጠማማ ንግግርና ርኩስ ስድባችሁ መልስ ትሰጡበታላችሁ:: እናንተ ሰዎች ድርጊታችሁን፣ ንግግራችሁን፣ ስድባችሁን ትረሱ ይሆናል፤ እኔ ዘንድ ግን የህጻንነት እድሜያችሁን ጨርሳችሁ ሕሊናችሁ ማወቅና ማስተዋል ከጀመረች ጀምሮ የፈጸማችሁት፣ ንስሐ ያልገባችሁበት በደለና ኃጢአት፣ ጠማማ ንግግርና ርኩስ ስድባችሁ እነዲሁም በሕሊናችሁ ያልተጸጸታችሁበት ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ ከስጋችሁ በስጋ ሞት ስትለይ ነፍሳችሁ ያደረጋችሁትን ማንኛዉም ኃጢአት በምድራዊ ህይወቷ የረሳችዉን ሁሉ ትዝ እያላት እስከ ፍርድ ቀን ድረሰ በጭንቀትና በስጋት እንዲሁም በዉስጣዊ መከራ ትሰቃያለች:: ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ እንደ ኃጢአት ደረጃዋ በገሃነም እሳት ዉስጥ ለሕያዉነት ዘመን የመጨረሻ ስቃይና የመከራ ቅጣቷን ትቀበላለች:: በዚህ ምድር ላይም ለሰራችሁት በደልና ኃጢአት የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ ከፍርዴ ማንም ፍጡር አያመልጥም:: ፍርዴ የሚለዋወጥና አድሎ ያለበት አይምሰላችሁ፤ በሐዲስ ዘመን ላላችሁ ፍርዱ ይብስባችኋል፤ ምክንያቱም ነገረ መስቀሌን አቅላችኋል ሰዉ የሆንኩበትን ምስጢር ከንቱ አድርጋችኋልና::

እናንተ ሰዎች ከኔ ዘንድ የሚላኩ ልዩ መልእክተኞቼ የምትለዩበት መንገዶች የሚከተሉት ናቸዉ:

1. የራሱን ክብር የማይፈልግና እኔን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነዉ::
2. ራሱን ከኔ ጋር ማስተካከል ቀርቶ ራሱን በፊቴ የሚያዋርድና ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ፤ ምክንያቱም የእኔን ከሕሊና በላይ የሆነዉን ባህርዬንና የራሱን ተራነት በሚገባ ያስተዉላልና ነዉ::
3. ስለ እዉነት የሚመሰክር፣ በእዉነት የሚኖር፣ ስለ እዉነት ራሱን የካደ ስለ እዉነት ማንኛዉም አይነት መከራና ችግር ቢመጣበት ሁሉን በጽናት የሚታገስ፣ እስከ መሰዋዕትነት የሚደርስ ነዉ::

4. « እንዲህ ይሆናል» ብሎ ከተናገረ ያለዉ የሚሆንለት የሚፈጸምለት ነዉ፡፡
5. በኔ ዘንድ ምህረትን ሆነ መአትን ቢጠይቅ እነደ ነብዩ ኤልያስ የሚከናወንለት ነዉ፡፡
6. በሰማያዉያን ሰራዊት ስለሚጠበቅ ማንም ፍጡር በራሱ ስልጣንና ሃይል ሊጎዳዉ ሆነ ሊያጠቃዉ የማይችል ነዉ፡፡
7. እኔን እንደ እግዚአብሄርነቴ ብቻ የሚያመልከኝ «አማለጅ ነዉ፣ ነብይ ነዉ ፣ፍጡር ነዉ» የማይለኝ በእግዚአብሄርነቴ ምንም ጥርጣሬ በዉስጡ የሌለ ነዉ፡፡
8. በኔ ስም፣ በሥላሴ ስም ፣በእመቤታችሁ ድንግል ማርያም ስም፣ በቅዱሳን መላእክት ስም፣ በጻድቃን በሰማዕታት በነብያት በሐዋርያት ስም፣ እንደ ተሰጠዉ ጸጋ የመፈወስና ተአምራትን የማድረግ ስልጣን ያለዉ ነዉ፡፡
9. የእናቴ የአደራ እናታችሁ የእመቤታችሁ ድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር ያለዉ ነዉ፡፡
10. ለምርጥ ባለሟሎቼና ወዳጆቼ ለቅዱሳን መላእክትና ለቅዱሳን ሰዎች ልዩ አክብሮት ያለዉ ነዉ፡፡

እለተምጽአቴን በተመለከት ማንም ሰዉ እንዳያሳስታችሁ፤ ቀኒቷና ሰአቷ በኔ ዘንድ ብቻ የምትታወቀዉ ያችም እለት የእናንተ የሰዉ ዘሮች በገነት፣ በሲኦል፣ በማረፊያ ቦታ፣ በሰማያትና በዚህች ምድር ዉስጥ ያላችሁት ነፍሳት ቁጥር በዚህች ምድር ዉስጥ (በአለም ዉስጥ) ካሉት ርኩሳን መናፍስት ቁጥር ጋር እኩል ሲሆን ነዉ፡፡ ያን ጊዜ በዚህች ምድር ዉስጥ የሚታዩትም የማይታዩትም ምሳሌያዊ ፍጥረቶች ሁሉ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፤ በዚያን ዘመን የሚኖሩ ከህጻን እስከ አዋቂ በማህጸን ዉሰጥ ካሉት ጭምር ከዚህ ክብር ከጎደለዉ ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ ከተላበሰዉ ቅርፊት ስጋቸዉ በመቅሰፍት ሞትና በምህረት ሞት ተለይተዉ ምሳሌያዊ ባህርይ በመልበስ ከዚህ አለም ዉጭ ወዳለችዉ ማረፊያ ቦታ ለፍርድ ይቀርባሉ፤ በዚህች ምድር ዉስጥ (በአለም ዉስጥ) ያሉት ርኩሳን መናፍስትም ማረፊያ ቦታ ላይ ለፍርድ ይቀርባሉ፤ በዚህች አለም ዉሰጥ በገነት ዉስጥ ያሉት ጻድቃን የመጨረሻዉን የእኔ ፍርድ ለመታዘብ በማረፊያ ቦታ ይገኛሉ፤ ከዚህ ዓለም ዉጭ ባለችዉ ሲዖል ዉሰጥ የሚገኙ ኃጢአን ሰዎች የመጨረሻ ፍርዳቸዉን ለመቀበል በማረፊያ ቦታ ይገኛሉ፤ በሰማያት የሚገኙ እጅግ ብዙ በጣም እጅግ ብዙ ከሰዉ አእምሮ ቁጥር በላይ የሆኑ ቅዱሳን መላእክት እኔን አምላካዉን ፈጣሪያቸዉን አጅበዉ ፍርዴን ለማየት በማረፊያ ቦታ ይገኛሉ፤ በዚያን ጊዜ ዓለምም ሲዖልም ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፤ አምስተኛዉ ቦታ ምሳሌያዊ ባህርይ የሆነዉ ገሃነም እሳት ካለመኖር ወደ መኖር ይመጣል፤ በማረፊያ ቦታ የሚገኙት ርኩሳን መናፍስትና ኃጢአተኛ ሰዎች (ኃጢአተኛነፍሳት) የመጨረሻ ፍርዳቸዉን ተቀብለዉ ወደ ገሃነም እሳት፣ እሳቱ ወደ ማይጠፋ ትሉ ወደ ማያንቀላፋ የመቀጫ ቦታ ይገባሉ፡፡ የተፈረደላቸዉ ጻድቃን ደግሞ እንደ ቅዱሳን መላእክት ሆነዉ ወደ ሰማያት ዉስጥ ይገባሉ፡፡ ስለዚህ ክርስቶስ፣ ኢየሱስ፣ አምላክ ፣ እግዚአብሄር በዚህ መንደር፣ በዚህ ከተማ፣ በዚህ ሀገር ተገለጠ፣ ይታያል ቢሏችሁ

ማንንም እንዳትቀበሉ፤ እንዳታምኑ፤ እነደዚያ የሚላችሁ እርሱ ሐሰተኛ የሆነ ከዲያብሎስ ነዉ።እኔ ለሁሉም ሕያዉ ፍጥረት የምታየዉ በመጨረሻዉ ፍርድ ቀን በእለተ መጽአት በማረፊያ ቦታ ላይ ብቻ ነዉ።

ከእንግዲህ ለአለም ፍፃሜ የሚቀሯችሁ ሶስት ዋንኛ ትንቢቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡

1.አለም ብትመከር፣ ብትገሰጽ፣ እጇን እንድትሰጥ ብትጠየቅ፣አሻፈረኝ ዲያብሎስ ይበልጥብኛል ብላለች።እናንተ የአዳምና የሔዋን ዘሮች ወደ እኔ በንስሐ አልመለስም ብላችኋል፤ ከእኔ የሆነዉን እዉነት አልቀበልም ብላችኋል፤ እያንዳንዱ ሀገር የዘራዉን ያጭዳል፤የአመጻዉን ፍዳ ይቀበላል። ይህም የመጨረሻ ፍርዴ ሩቅ አይምሰላችሁ፤በደጃችሁ ቆሟል። እኔን ከመፍራትና ከማወቅ ስለራቃችሁ ማስተዋሉን አላገኛችሁም እንጂ ደጃችሁን አልፌ ከቤታችሁ ነኝ።

2. የአመጻ ስራና የአመጻ ልጆችን ከዚህች ምድር ካጸዳዉ በኋላ በኔ የተመረጠዉ የእናቴ የአደራ እናታችዉ የእመቤታችሁ ምርጥ ባለሟል ለሆነዉ ለኢትዮጵያዊዉ ሰዉ ይህችን የተቀደሰች ሀገርና አለምን በእጁ አሳልፌ እሰጠዋለሁ።ፈቃዴን ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል። ፈቃዴ ሲፈጸም ይህችን ሀገርና ዓለምን በምህረት እጎበኛለሁ፤መልካም ዘመንን አመጣለሁ።

3.በመልካም ዘመን መጨረሻ አንድ ቀን አሁን የሚደረገዉን ማጥሪያና ማበጠሪያ ኃይሉን እንዲሁም መልካሙን ዘመን የሚዘነጋ ትዉልድ በዓለም ይወለዳል።በዚያን ጊዜ ዋናዉ የአመጻ ልጅ (ሐሰተኛዉ መሲህ) (ሐሰተኛዉ ክርስቶስ) (ሐሰተኛዉ አምላክ) ይነሳል፤በሃይልና በድንቃድንቅ ተአምራት ለዓለም ይገለጣል። ለሶስት አመት ተኩል(ለአርባ ሁለት ወራት) ብቻ ባለ ጊዜ ሆኖ በእኔ የሚያምኑትን ይፈታተናል፣ ያጠቃል፣ ያሰናክላል። ትዕቢት የተባሉት የፈርኦን ወንድምና እህቶች፣ ክፋት የተባሉት የይሁዳ ወንድምና እህቶች፣ አመጻ የተባሉት የአርዮስ ወንድምና እህቶች የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች በዋናነት ተከታዮቹና አጫፋሪዎቹ ይሆናሉ። ቁጣዉን በመፍራት አእምሮ ህጻናትና አእምሮቀላሎች ይከተሉታል። አእምሮ አዋቂዎች ይሰናከሉበታል። ቁጣዉንና ድንቃድንቅ ተአምራቱን በመመልከት አእምሮ ጽኑአን ይፈተኑበታል።

በሶስት አመት ተኩል ዉስጥ በእምነቱ የጸና እርሱ ለሰማያዊ መንግስት የተመረጠ ሰዉ ነዉ። የዋናዉ የአመጻና አመጻ ልጆች ባለ ጊዜነት ስሽር ዓለም እንዳልነበረች ትሆናለች። የአመጻ ልጆች በመቅሰፍትና በስቃይ ሞት፣ የተመረጡ ሰዎች ደግሞ በምህረት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ። በዚህች ምድር ዉስጥ ሆነ በዓለም ዉስጥ በአይን የሚታዩት፣ የማይታዩት ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ። የዓለም ፍፃሜ በዚህ መልክ ይጠናቀቃል።» ይላል አልፋና ዖሜጋ እግዚአብሄር፤ የቅዱስ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሩፋኤል፣ ኡራኤል፣ ፋኑኤል፣ ራጉኤል አምላክ።

# ክፍል ሦስት

## ለኢትዮጵያ ህዝብ የተላለፈ የእግዚአብሄር ግሳጼና ቃል

## ምዕራፍ አንድ

«እናንተ በስጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ የማን ፈቃድ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ ነው? ለመሆኑ በእናንተ ኃይልና እውቀት በዚህ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ይመስላችኋልን? በውኑ የእናንተ መሳሪያና ወታደሮቻችሁ ከቀድሞው ስርዓት መሪዎች መሳሪያና ወታደሮች በልጠው ድል ያደረጋችሁ ይመስላችኋልን? እውነቱ ግን ነገስታትን የማፈራርቅ፣ የምሾም የምሽር፣ ከፍ ከፍ የማደረግ የማዋርድ እኔ ነኝ። ያለፈው መሪና ግብረ አበሮቹ የአመጻና የግፍ ጽዋቸው ሞልቶ ስለፈሰሰ ነው እነሱን ሽሬ ወደ ወንበር ያመጣኋችሁ ።

እናንተም በተቀመጣችሁበት ወንበር ህዝቡን በሚገባ መምራት፣ ከክህደት ወደ እምነት፣ ከጥላቻ ወደ መፈቃቀር፣ ከመለያየት ወደ አንድነት፣ ከርኩሰት ወደ ቅድስና፣ ከጣዖትና ባዕድ አምልኮ ወደ አምልኮተ እግዚአብሄር፣ ከጠማማነት ወደ መልካምነት፣ ከክፋት ወደ ደግነት፣ ከተንኮል ወደ ቀናነት፣ ከሌብነት ወደ ጨዋነት፣ ከራስ ወዳድነት ወደ ወገን (ኢትዮጵያዉያንን ሁሉ) ወዳድነት፣ ገንዘብንና ስልጣንን ከማምለክ ወደ እኔን ማምለክ፣ በትዕቢትና አመጻ ህይወት ከመመላለስ ወደ ትህትናና ታዛዥነት መመለስ ሲገባቸው ተቃራኒውን ፈጽማችኋል ።

ይህም አልበቃ ብሏችሁ ህዝቡን በጎሳ፣ በቋንቋ ከፋፍላችሁ እርስ በእርሱ እንዳይተማመን፣ ጥላቻንና መለያየትን ፈጥራችኋል፤ በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድናችሁ ህዝቡን በረሀብና በችግር እየቀጣችሁ ራሳችሁን አበልጽጋችኋል፤ ኢትዮጵያዊነቱንም ገዝግዛችኋል፤ እውነተኛውን ሃይማኖት በክህደት እንዲሸፈን አድርጋችኋል፤ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የፈለጋችሁትን እያስቀመጣችሁ ሊመራችሁና ሊገስጻችሁ የሚገባውን እንደፈለጋችሁ እያሽከረከራችሁ የአመጽ ስራ ተባባሪ አደረጋችሁ፤ ኢትዮጵያውያን ወንድማማቾችና እህትማማቾች እንዲለያዩ እንዲገነጠሉ አደረጋችሁ፤ ከዚያም አልፎ እርስ በእርስ በጦርነት እንዲፋጁ አደረጋችሁ፤ እናንተ ግን በተደላደለ ወንበር ላይ ተቀምጣችሁ ምስኪኑ ወገናችሁ ደሙ በከንቱ እንዲፈስ አደረጋችሁ፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ በሀገሩ በነፃነት ተዟዙሮ እንዳይሰራ እንዳይኖር «ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ክልል ነው፣ ይህንን ቋንቋ ካልተናገርክ የስራ ድርሻ የለህም።» እያላችሁ አድሎና በደል ፈጸማችሁ፣ በኢትዮጵያዊነቱ ያመነውንና ኢትዮጵያውያን ሁሉ ወገኖቼ ናቸው ብሎ ያመነውን አሰራችሁ፣ ገደላችሁ፣ አሳደዳችሁ፣ ወነጀላችሁ፤ እረ የእናንተ ተግባር ምኑ ተነግሮ ያልቃል ። በአጠቃላይ የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው ዲያብሎስ የሚያዛችሁን ተግባር ፈጸማችሁ፤ አስፈጸማችሁ ።

እረ ለመሆኑ ኢትዮጵያን ታውቋታላችሁ ወይ? ያሳለፈችው ታሪክ ምንድን ነው? የቀደሙት አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ ምን ሰርተው እንዳለፉ ታውቃላችሁ? ይህች ሀገር በማን እንድምትጠበቅ ታውቃላችሁ? ለእርሷ ጥብቅና የሚቆሙላት እነማን እንደሆኑ ታውቃላችሁ? አታውቁም። አውቃችሁስ ቢሆን ኖሮ በዚህ ተግባር አታልፉም ነበር። የክፉ ተግባር ፈጻሚ አትሆኑም ነበር።

እረ ለመሆኑ በጎሳና በቋንቋ የከፋፈላችሁት ሀገር ከዛሬ መቶ ዓመት፣ አምስት መቶ ዓመት፣ አንድ ሺህ ዓመት፣ ሁለት ሺህ ዓመት፣ ... ወዘተ አሁን ሰው የሚኖርበት አካባቢ ሰው ይኖርበት ነበርን? ማን ነበር ያን ጊዜ? በደንና በአራዊት የተሞላ አልነበረምን? ታድያ ከየት አምጥታችሁ ነው «ይህ ያንተ ክልልና መንግስት፣ ይህ ያንተ የጎጥ ወሰንና ድንበር ነው» ብላችሁ የከፋና የከረፋ ሐሳብ ፈጥራችሁ አንድ የሆነዉን የኢትዮጵያን ህዝብ የከፋፈላችሁት? ይህስ ለመከፋፈያና የራሳችሁን መሰሪ ተግባር ለመፈጸም የተጠቀማችሁበት የቋንቋ ክፍፍል ፣ ቋንቋዉ ራሱ የዛሬ

አምስት መቶ፣ አነድ ሺህ፣ ሁለት ሺህ  አመት ነበረ ወይ? ለመሆኑ የሰዎች ቋንቋ የተለያየበት ምክንያት ታዉቃላችዉ?

ካላወቃችሁ እንግዲህ እወቁት፤ ሰዎች በትዕቢት:በክፋት በአመጻ ተሞልተዉ እኔን ሲገዳደሩ ነዉ በኃጢአታችሁ  ምክንያት ቋንቋቸዉን የደበላለኩና በአራቱም ማዕዘን የበታተንኳቸዉ::የጽድቅ ዋጋ እንዳልሆነ አወቃችሁን? አሁን ደግሞ በምህረት ዘመን ሰዎች ወደ አንድ ቋንቋ እንዲመጡ፣ እንዲግባቡ ፣ እንዲዋሃዱ፣ አንድ እንዲሆኑ በማደርግበት ጊዜ እናንተ ደግሞ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚዎች ናችሁና የኔን ተቃራኒ ተግባር ትፈጽማላችሁ!

በዉኑ በዚህ የሚቀጥል ይመስላችኋልን? ይህን የተመረጠ ህዝብ እየሸነገላችሁ፣ እያታለላችሁ፣ ሕሊናዉን እንዲሸጥ እያደረጋችሁ፣  ለጥቅምና ለስልጣን ራሱን እንዲክድ እያደረጋችሁ የምትኖሩ ይመስላችኋልን? በቃ የእናንተም የአመጻና የርኩሰት ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ነዉ:: የዘራችሁትን የክፋት፣ የተንኮል፣ የዘረኝነት፣ የጥላቻ፣ የመለያየት፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያችሁን ታጭዳላችሁ:: ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ:: በቅንነትና በእዉነት ለሚመላለሱ፣ የኔን ፈቃድ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለድንግል ማርያም ምርጥ ባለሚሎች ስጋዊዉንም፣ መንፈሳዊዉንም ወንበር አሳልፌ እሰጣለሁ:: የጽድቅ ፍሬ ያፈሩበታል:: በረሃብ፣ በችግር፣ በልመና፣ በጦርነት፣ በጉስቁልና በዓለም ዘንድ እንድትታወቅ ያደረጋችኋትን «ሀገረ እግዚአብሄር» የተባለች ምስጢር አገሬ፣ የቅድስት ድንግል ማርያም አስራት ሀገር፣ የቀደመ ክብሯ ይመለሳል:: ከራሷ አልፋ ለዓለም ብርሃን ትሆናለች::ልጆቿን በአራቱም ማዕዘን ትሾማለች::በጎቼን በመልካም ህይወት ታኖራለች::

እናንተ ግን « ህዝቡን በቋንቋ፣ በጎሳ፣ በክልል ከፋፍለናል ከእንግዲህ  በኋላ ወደ አንድነት እንምጣ ብሎ ሀገራዊ ራዕይ ይዞ የሚነሳ አካል ቢመጣ ህዝቡ እርስ በእርስ ስለሚተላለቅ ማንም አይቀበላቸዉም፤ከተቀበሏቸዉ ደግሞ እንገነጠላለን፤ እናስገነጥላለን » ብላችዉ የዚህች ሀገር መጥፋት፣  የህዝቡን መተላለቅ ስሜት ሳይሰጣችሁ፣ ተስፋችሁ ምድራዊ የሆነ፣ ተግባራችሁና ሐሳባችሁ ተንኮልና ክፋት የሞላዉ የአመጻ ልጆች፤እናንተ እንደምትመኙትና እንደምታስቡት ይህች ሀገር ለጥፋትና ለዉድቀት አትዳረግም:: በቅዱሳን ጸሎት የምትጠበቅ፣ በሰማያዊ ሰራዊት የተከበበች፣ ባለ አስራቷም ሁሌ በፊቴ የምትቆምላት ስለሆነ ሊያጠፏት የሚነሱ ሁሉ ይጠፋሉ ::

ለመሆኑ ምን የሀገር ፍቅር አላችሁና ነዉ ስለ ሰንደቅ አላማ የምታወሩት? ሰንደቅ አላማ «ጨርቅ ነዉ » ብላችሁ እንዳላጥላላችሁ፣ የእዉነተኛዋን የኢትዮጵያ መለያ ሰንደቅ አላማ ፍቅር ለመቀነስ ይህችን ሀገር በቋንቋ:በጎሳ ከፋፍላችሁ «የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ሰንደቅ አላማ ፣የዚህ ጎሳ ክልል ሰንደቅ አላማ » በማለት ማንም ኢትዮጵያዊ ያላደረገዉን የተንኮልና የክፋት ተግባር ፈጽማችኋል::ከዚህ አልፎ ደግሞ እዉነተኛዉን  ሰንደቅ አላማ ከፍ ከፍ ያደረገ በወንጀል እንዲቀጣ፣  ሆዳቸዉ አምላካቸዉ ከሆነና ሕሊናቸዉን ከሸጡ ከአእምሮ ህጻናትና ከአእምሮ ቀላሎች ከግብረ አበሮቻችሁ ጋር በመሆን አጽድቃችኋል::ዲያብሎስ ያዘጋጀላችሁን የኮከብ አርማ በእዉነተኛዉ ሰንደቅ አላማ ላይ በማድረግ የአንዲት ሰንደቅ አላማና የአንዲት ሀገር ፍቅር ለመቀነስ፤ ኢትዮጵያዊ ወኔን ለመስለብ፤ ከንቱ የሆነ መጠበብ ተጠባችኋል::ነገር ግን ክፉ ተግባራችሁና ሐሳባችሁ ከንቱ ሆኖ ይቀራል:: እዉነተኛዋና ብቸኛዋ ሰንደቅ አላማ ከፍ ከፍ ይላል::

እናንተ በእዉነተኛዉ መንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ፤ ማንን እያገለገላችሁ ነዉ? ለመሆኑ የምታመልኩት ማንን ነዉ? ለመሆኑ ምዕመናንን  ታዉቃላችሁ? ክርስትና በምን መልክ ለአሁን ዘመን ተላልፋ እንደመጣች ታዉቃላችሁን? አታዉቁም:: ብታዉቁም አላስተዋላችሁም:: ብታስተዉሉም የስጋ ምኞታችሁና ፍላጎታችሁ አሸንፏችሁ እኔን ባለመፍራት ሕሊናችሁን ሸጣችኋል:: የድፍረት በደል ፈጽማችኋል:: በጎቼ እረኛ የሌላቸዉ ሆነዉ ተቅበዝብዘዋል፤ ትዕዛዜንና

ሕጌን ሽራችኋል፤ ምዕመናን በትዕዛዜና በስርአቴ እንዳይመላለሱ ማሰናከያና እንቅፋት ሆናችኋል። የራሳችሁ በደልና ኃጢአት አልበቃ ብሏችሁ እዉነተኛ አገልጋዮችን አሰራችሁ፤ አሳደዳችሁ፤ ገደላችሁ፤ አንከራተታችሁ፤ ወነጀላችሁ።

ክርስትናን መስራች የሆንኩ አምላክ ፤ አምላካዊ ባህርዬን ዝቅ ያደረኩት፤ከእናቴ ከእናታችሁ ከእመቤታችሁ ከድንግል ማርያም ስጋ ተዋህጄ ሰዉ ስሆን ፣ከመወለዴ ጀምሮ እስከ እርገቴ ድረስ የዚህ አለም ክብርና ጥቅም ፈልጌአለሁን? ስወለድ እንደ ተራ ደሀ ሰዉ በከብቶች በረት ዉስጥ፣ ከዚያም እንደ አቅመ ቢስ ሄሮድስን ሽሽቼ ወደ ግብፅ ተሰደድኩ፣እንደ ችግረኛ በረሃብና በጥም በረሃ ለበረሃ ተንከራተትኩ፣ከኃጢአት በቀር ፍጡር የሚያደርገዉን አደረኩ፣ዘመን የማይቆጠርልኝ ስጋ በመልበሴ ዘመን ተቆጥሮልኝ ሰላሳ አመት ሲሞላኝ ማስተማር ጀመርኩ፣ የማስተምረዉን በተግባር እየፈጸምኩ አሳየሁ። ትምህርቴና ተግባሬ አላማዉ ሰዎች ሁሉ ንስሐ እንዲገቡ፣ ከኃጢአት ተግባር ወደ ፅድቅ እንዲመለሱ፣ በቅድስና ህይወት ተመላልሰዉ ከሞት በኋላ ያለዉን ህይወት ተስፋ አድርገዉ ራሳቸዉን ለሰማያዊ መንግስት እንዲያዘጋጁ ነበር።

በመጨረሻም ፈቃዴ ስለሆነ፤ልክ እንደናንተዉ በእዉነተኛዉ የሙሴ ወንበር ላይ የተቀመጡት የአይሁድ ካህናት፣ፀሐፍት ፈሪሳዉያን «የእግዚአብሄር አገልጋዮች ነን፤ ለሕጉና ለትዕዛዙ ቀናኢ ነን፤ ለስርአቱና ለፍርዱ ጥብቅና እንቆማለን፤» የሚሉ፤ ነገር ግን በአንደበታቸዉ እንጂ በተግባር የማይፈጽሙ፤ ባዶ ቀፎ የሆኑ፤ ዉስጣቸዉ ተንኮልና አመጻ፣ትዕቢትና ቅናት የሞላባቸዉ ፍጡሮቼ፤ እኔዉ አምላካቸዉንና ፈጣሪያቸዉን ካለ በደሌ እንደበደለኛ፣ ካለ ወንጀሌ እንደወንጀለኛ፣ካለ ኃጢአቴ እንደ ኃጢአተኛ ወንጅለዉኝ፤ የሐሰት ምስክር አዘጋጅተዉ፣እዉነተኛዉ ፈራጅ የሆንኩትን በኔ ላይ የሞት ፍርድ አስፈረዱብኝ፤ ሰደቡኝ፤ ተፉብኝ፤ ገረፉኝ፤ ዘበቱኝብ፤ አንገላቱኝ፤ እንደ ዋና ወንጀለኛ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉኝ። ታድያ ሁሉን ማድረግ ስችል በትዕግስትና በአኮቴት ነዉ ይህን ከሕሊናችሁ በላይ የሆነዉን መከራ የተቀበልኩት።

ታዲያ ይህን ሁሉ ያደረኩት የሰዉ ዘር ሁሉ እንዲድኑበት ክርስትናን ለመመስረት ነዉ። እኔ የመሰረትኳት ክርስትና የተስፋፋችሁ በቀላሉ አልነበረም።ሐዋርያቶቼና ደቀመዛሙርቴ የእኔ ፈለግ ተከትለዉ የዚህ አለም ስልጣን፣ ጥቅም፣ ክብር፣ ዝና ሳያሸንፋቸዉ ስለ እዉነት ተደበደቡ፣ ተገረፉ፣ ተሰደዱ፣ ተቃጠሉ፣ ተሰቀሉ፣ ለአራዊት ተጣሉ በአጠቃላይ የተለያየ መከራ ደረሰባቸዉ፤ እዉነትን ግን ለአበዉ ሐዋርያት አስተላለፉ።

አበዉ ሐዋርያትም እንዲሁ የተለያየ መከራ ተቀብለዉ ለሰማዕታት አስተላለፉ። ሰማዕታትም የተለያየ ጸዋትዎ መከራ በመቀበል ለአበዉ ሊቃዉንት ለመምህራን አስተላለፉ።እስከ አምስተኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ አንዲት ሃይማኖት የነበረችዉ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፤  ልክ እንደናንተዉ ለስጋ ፈቃዳቸዉ ያደሩ፤  እንደ ሰጋዊ አስተሳሰባቸዉ ህዝብን ለሚመሩ መሪዎች ሕሊናቸዉን የሸጡ፤ የሃይማኖት መሪዎች የተባሉ ባህርዬን ለሁለት ከፈሉ። እኔ  እግዚአብሄር ፍጹም አምላክ  ፍጹም ሰዉ ሆኛለሁ። ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ሆኜ ነዉ ሰዉ የሆንኩት። ታዲያ ሁለት ባህርይ ብሎ መፈላሰፉ ኬት መጣ?እነዚህ ለሁለት የከፈሏት በእዉነተኛዉ ወንበር ላይ የተቀመጡ ልክ እንደ እናንተ ክርስትና ያለፈችበትን መከራ የዘነጉ፤ ለስጋዊ ሰልጣን፣ክብር፣ዝና፣ ጥቅም ቦታ የሰጡ፤በዘመድ አዝማድ የተተበተቡ ስለሆነ እንዴት ስለ እዉነት ይቁሙ!?

የሃይማኖት አባቶች ስለ እዉነት በአንድነት ቆመዉ ክርስትናን በአራቱም ማዕዘን ሊያስፋፉና ሰዎችን ከሞት ወደ ህይወት መመለስ፤ከክህደት ወደ እምነት ማምጣት ሲገባቸዉ እርስ በእርስ እየተከፋፈሉና እየተወጋገዙ ክርስትናን አዳከሟት፤አቀጨጫት።

በዚህ ምክንያት በስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ማለቂያ ላይ በራሱ ምኞትና ሐሳብ ተነሳስቶ ለፈጣሪ የቀና መስሎት ሕሊናዉን ለዲያብሎስ ማደሪያ ያደረገ ሐሰተኛ ነብይ፤ ክህደትን አስፋፋ፤ ክርስትናን ለማጥፋት ዘመቻ አደረገ:: እኔ አልፋና ዖሜጋ እግዚአብሄር የሁሉ ፈጣሪ የሆንኩትን «ኢየሱስ ነብይ ነዉ፤እኔም ከፈጣሪ የተላኩ ነብይ ነኝ » አለ በድፍረት::በዚህ ክህደት ምክንያት ትዉልዱ ለአንድ ሺህ አራት መቶ ዘመን በላይ በሞት ህይወት ዉስጥ እንዲመላለሱ አደረገ::

በአስራ አንደኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ሁለት ባህርይ ብለዉ ከከፈሉኝ ወገኖች (ኦርቶዶክስ) ከተባሉት «መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም ነዉ የሰረጸዉ » በማለት ተከፋፍለዉ ከኦርቶዶክስ ካቶሊክ ተፈጠረ:: ወደ መጀመሪያዋ ሃይማኖት «አንድ አካል፤ አንድ ባህርይ » ከምትለዉ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ብቻ ነዉ የሚሰርጸዉ ብላ ከምታምነዉ ወደ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መመለስ ሲገባቸዉ ሌላ ፍልስፍና ፈጠሩ ::

ታዲያ ይህ መከፋፈል በእዉነት ስለ እኔ በመቅናትና እዉነትን ለህዝብ(ለምዕመን) ለማሳወቅ ሳይሆን ለስልጣን፣ለክብር፣ ለጥቅም፣ ለዝና ነበር:: ይህም ክፍፍል ክርስትናን አዳከማት፤አቀጨጫት እንጂ የሰዉ ዘሮች ወደ እዉነት እንዲመጡ አላደረገም::

የዚህች ክርስትና ፈተናዋ አልበቃ ብሎ በአስራ ስድስተኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ላይ የካቶሊክ ተከታይ የነበረዉ መነኩሴ ሐሰተኛ ወንጌላዊ፤ የስጋ ፈቃዱና ምኞቱ አሸንፎት ዉስጡ አመጻ የሞላበት ነበርና ለፕሮቴስታንት የክህደት እምነት መሰረት ጣለ:: እኔ የሁሉ ፈራጅ ዳኛ የሆንኩትን ፣ ከኔ በላይ ማንም የሌለዉን፣ ፈጣሪ አምላክ የሆንኩትን «አማላጅ »ነዉ በማለት አስካደኝ፤ አሰደበኝ:: ከዚያም አልፎ የእናቴን የእመቤታችሁን የድንግል ማርያምን ክብር አዋረደ፤ አቀለለ:: የቅዱሳንን ምልጃና ክብር አዋረደ፤ አቀለለ :: በዚህ ክህደትና መናፍቅነት ምክንያት ትዉልዱ ለአምስት መቶ ዘመን በላይ በሞት ህይወት ዉስጥ እንዲመላለሱ አደረገ::

እንግዲህ የክህደቱና የመናፍቅነቱ ዘመን ይበቃችኋል:: ነጻ ሕሊና የምታመዛዝኑበትና የምታስቡበት ተሰቷችሁ ነበር::ነገር ግን በቅን ሐሳብና በመልካም ህይወት ተመላልሳችሁ እዉነትን ስላልፈለጋችሁ ድኅነትን ከሚሰጠዉ እዉነተኛ ሃይማኖትና ቅድስት ቤተክርስቲያን ተለይታችኋል ::አሁን ግን በሐሰት የተሞላዉ የክህደትና የመናፍቅነት እምነት ተሸሮ እዉነት ትገለጻለች:: የሐሰት መንፈሳዊ ወንበራችሁ ይሻራል:: በእዉነተኛ ወንበር ይተካል:: ሞትና የጨለማ መንገድ ይቀራል:: የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋህዶ ሃይማኖት የሁሉ መሪ ትሆናለች::

እናንተ በእዉነተኛዉ ወንበር ላይ ሆናችሁ በቀጥተኛዋ ተዋህዶ ሃይማኖት በቅድስት ቤተክርስትያን ስም የነገዳችሁ፤ ያስመሰላችሁ ከላይ እስከ ታች ያላችሁ አስመሳይ አገልጋዮች፤ በጎቼን በሚገባ አልጠበቃችሁም፤አላገለገላችሁምና ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ:: በቅንነትና በእዉነት ለሚያገለግሉ ለምርጥ ባለሟሎቼ ለድንግል ማርያም ምርጥ ልጆች ወንበራችሁ ትሰጣለች:: እናንተም የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ::

እናንተ በቅድስት ቤተክርስትያን ስም የምትነግዱ፤ስለ ሃይማኖቷ ሆነ ስለ ቤተክርስትያን ፍቅር ሳይኖራችሁ ዉስጣችሁ ጥርጥር ሞልቶ ሕሊናችሁ በትዕቢትና አመጽ እያለ ቤተክርስትያንን እናገለግላለን በማለት የእናንተ አመጻ መንፈስ የሚመራቸዉ አባቶቻችሁ ፈቅደዉላችሁ መንፈሳዊዉን መድረክ የዳንኪራና የዘፈን መድረክ ያደረጋችሁ፤ ከመናፍቃን ጋር አንድ ለማድረግ የቤተ ክርስቲያንን አስተምሮት፣ ቋንቋ፣ ዜማ፣ ስርአት፣ ትዉፊት በመለወጥ ላይ ያላችሁ አስመሳይ አገልጋዮች፤ በመጀመሪያ ከማገልገላችሁ በፊት ህይወታችሁን ወደ መንፈሳዊነት አትለዉጡም ነበር? በአመጻና በትዕቢት ህይወት ፍሬ የምታፈሩ ይመስላችኋልን? ምዕመናን ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ካልተመለሱ፤ንስሐ ገብተዉ እኔ የተዋህድኩትን ቅዱስ ስጋዬን ክቡር ደሜን ካልበሉና ካልጠጡ

ለነፍሳቸዉ የሚጠቅም ምን  ነገር ሰጣችኋቸዉ!? ወይስ በስጋዊ ህይወት የዉሸቱን ደስታ ለማግኘት ዘፈኑና ዳንኪራዉን እንደሚጠቀሙ፤ ልክ ይህንኑ ዘፈንና ዳንኪራ «በመንፈሳዊ» መልክ ለዉጠዉ ቅዱስ ቃሉን መጫወቻ በማድረግ እለት እለት እግጅ እንደሚያስቆጡኝ እጅጉን እንደተጸየፍኳቸዉ መናፍቃን እጅጉን ልታስቆጡኝ ነዉ ጥረታችሁ? እናንተም ትጠራላችሁ፤ ትበጠራላችሁ፡፡

አንተ ዘመናዊዉ ጠንቋይ፤የሰዎችን ስሜቴና ተግባር እየተከተልክ በቃሌ የምትነግድ ሐሰተኛ ሰባኪ፤ስንቱን የዋሃን በጎቼን አሳሳትክ ፤አሰናከልክ ፤ ስንቱን እረኛ ነኝ ብሎ በእዉነተኛ ወንበር የተቀመጠዉን አሳሳትክ !? እኔ ሳላናግርህ «እግዚአብሄር የሚያናግረኝን ቃል አንድ ሳላስቀር እናገራችኋለሁ » እያልክ በስሜ የምትነግድ አመጽና ትዕቢት የሞላብህ፤ በየትኛዉ ቅድስና ህይወትህ ነዉ እኔ አንተን የማናግር? ቀደም ሲል የምዕመንን ልቦና ተረድተህ  « የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች» ብለህ አባቶችህን እንዳላዋረድክ አሁን ደግሞ ገበናህ ሲጋለጥ የአባቶችህን ሐዉልት በክብር አስመርቀህ አስመለክ፡፡ ያዉ ሁለታችሁም በአመጻ መንፈስ የምትመሩ ስለሆነ በስተመጨረሻ ለጥፋት ህብረትና አንድነት ብትፈጥሩ ምንም አያስገርምም! በበላይ የሚመራችሁ ዲያብሎስ  ከነሰራዊቱ ህብረትና አንድነት ፈጥሮ ለአመጻ ስራ ቢሰለፍም ከእኔ የሆነዉን መቋቋም ሆነ ማሸነፍ ስለማይችል እናንተም ከቤቴ ትጠረጋላችሁ፤ትዋረዳላችሁ፡፡

አንተ ትንሹ የአመጽ ልጅ ባማረዉ አንደበትህ ምዕመናን እንዲህ የምታሰናክል ከሆነ፤ ሐሰተኛዉ መሲህ (ሐሰተኛዉ ክርስቶስ)( ሐሰተኛዉ አምላክ) በአለም ፍጻሜ መጨረሻ ዘመን ለጥቂት አመታት በዮሐንስ ራዕይ እንደተገለጸዉ ለተወሰኑ እጅግ ጥቂት ቀናት ባለ ጊዜ ሆኖ ባማረ አንደበት ብቻ አይደለም በሃይሉና በድንቃ ድንቅ ተአምራት ሲገለጥ ስንቱን ሰዉ ያሳስት ይሆን!?  ስንቱን የተመረጡ በጎችና እረኞችን ያሰናክል ይሆን!?

እንግዲህ ስብከቶቻችሁ መናፍቅ መናፍቅ የሸተተ፣ መዝሙራችሁ ዘፈን ዘፈን ያለ፣ምስጋናችሁ ዳንኪራና ጭፈራ የመሰለ፣በአጠቃላይ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነትና ስርአት ዉጭ የሆነ፤ እንክርዳዳችሁን ከእዉነተኛዉ አገልግሎት አዉጡ፡፡ እናንተ ባለማወቅ ከአመጻ ልጆች ጋር የተሰለፋችሁ ፣ የአመጻ ልጆች አላማቸዉ የሃይማኖታችሁንና የቤተ ክርስቲያናችሁን ፍቅር ሊሸረሽሩ፤እንደቀደሙት በቤተ ክርስቲያኒቱ እንክርዳድ እንደዘሩት ቅባት፣ ጸጋ፣ ተሐድሶ ምዕመናን ወደ ክህደትና ጥርጥር ለመዉሰድ ነዉ፡፡ ስለ እምነት ሆነ ስለ ምግባር ደንታ ቢስ እንድትሆኑ ለማድረግ፣ በመጨረሻም ወደ ሞት መንገድ ሊወስዳችሁ ነዉ ዲያብሎስ በበላይ ሆኖ እነዚህ የአመጻ ልጆችን ያሰማራዉ፡፡እናንተ በአላማ ለጥፋት የተሰማራችሁ እንክርዳድ ናችሁና ቦታ የላችሁም፡፡ ትበጠራላችሁ፤ ከስንዴዉ ትለያላችሁ ፡፡

እናንተ መንፈሳዊ አገልግሎትን እንደ ስራ መስክ ቆጥራችሁ በዝሙት፣ በስርቆት፣ በርኩሰት፣ በመተትና በጥንቆላ፣ በአስማት፣ በዘፋኝነት፣ በስካር፣ በትዕቢትና በአመጻ ያላችሁ አስመሳይ አገልጋዮች፤ ማንን እያታለላችሁ ነዉ? የክርስትና ህይወት ገብቷችኋል ወይ? ስለምን ፍርዱ እነደ አለማዉያኑ እንዲቀልላችሁ ከማስመሰል አገልግሎት ወታችሁ በስጋ መኖሩ አይሻላችሁምን? በቃሌ ነግዳችኋል፤ ቤተ መቅደሴን አርክሳችኋልኋና  እናንተ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ፡፡ ዝም ስል የሌለሁ መሰላችሁን? ከአናታችሁ ጀምሮ እስከ እግራችሁ ድረስ በለምጽ አንድጃችሁ በህዝብ ፊት ማዋረድ አቅቶኝ ይመስላችኋልን? ይህን ባደርግ ስንት አገልጋይ ከቅጣቱ ይድናል? ከዚህ ቅርፊት ስጋችሁ ስትለዩም ከኔ ፍርድ አታመልጡም፤ፍዳችሁን ትቀበላላችሁ፡፡

እናንተ በእዉቀት ብቻ የምታገለግሉ መንፈሳዊነት የሌላችሁ፤ በኔስም፣ በእናቴ በድንግል ማርያም ስም፣ በቅዱሳን መላእክት ስም፣ በነብያት በሐዋርያት በሰማዕታት በጻድቃን ስም የምትነግዱ፤ ምዕመናንን «ጸድቃችኋል፣ ቅዱሳን ናችሁ»  እያላችሁ የምትሸነግሉ፤ ከትዕዛዜና ከስርአቴ ወተዉ

በዘልማድ እንዲመላለሱ ያደረጋችሁ፤ በኃጢአት ህይወት እንዲጸኑ ያደረጋችሁ፤ስለ በጎች ነፍስ መዳን ደንታ የሌላችሁ፤ የክርስትና የወንጌል እንቅፋት የሆናችሁ፤ የእናንተ ሆድ ከሞላ፣ ጥቅማችሁ ከተጠበቀ፣ ምዕመናን እምነታቸዉን አወቁ አላወቁ ደንታ የሌላችሁ፤ትዕዛዜ ተጠበቀ አልተጠበቀ ግድ የማይላችሁ፣ በአጠቃላይ እናንተም በዘልማድ የምትመላለሱ፣ ሌላዉንም በዘልማድ እንዲመላላሱ የምታደርጉ፣የበጎቼ ጠባቂ የምትመስሉ አስመሳዮች፣እናንተም ወደ መንግስቴ አትገቡም። ሌላዉም እንዳይገባ እንቅፋት ሆናችኋልና ቦታዉን ለእዉነተኛ ለበጎች እረኛ ትለቃላችሁ ።

እናንተ በድፍረት ርኩሰትን በቤቴና በቅጥሬ ዉስጥ የምትፈጽሙ፤ በዉኑ ከኔ እይታ የምትሰወሩ ይመስላችኋልን? እጅግ አስቆጥታችሁኛልና ከሁሉ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ።

እናንተ ቤተ መቅደሴን እንደራሳችሁ ቤት የምትመለከቱ፣ እኔን ባወቃችሁ መጠን ልታከብሩኝና በእዉነት ልታመልኩኝ ሲገባችሁ እጅግ ተደፋፈራችሁኝ። ትህትና ትግስት ፍቅር የሚባል የላችሁም በትዕቢትና በአመጻ ህይወት ትመላለሳላችሁ። እኔም እጅግ ተጸይፌያችኋለዉ ቤቴን ሳጠራ እናንተም ትጠረጋላችሁ።

እናንተ በቤቴና በቅጥሬ ለአምልኮት መታችሁ የራሳችሁን ስራ የምትሰሩ በአለም ሳላችሁ ያለዉ ወሬያችሁ ሳያንስ በቤቴ የሆነ ያልሆነዉን የምታወሩ፣ እንኳን የምትናገሩትን ቀርቶ የምታስቡትን ጠማማ ሐሳብ ሳይቀር በሰማያዊ መዝገብ እንደምመዘግበዉና ስለ ጠማማ ንግግራችሁና ሐሳብ እንደምትጠየቁበት አታዉቁምን? ቤቴን እንደ ጊዜ ማሳለፊያ ከማየታችሁ በተጨማሪ በጸሎት፣ በምስጋና የተጸመዱትን የምትረብሹ፣ ፍርዱ እንዲቀልላችሁ በዚያዉ በቤታችሁ ሆናችሁ የአለሙን ሐሳብና ወሬ ማሰብና ማዉራት አይሻላችሁም ነበር? ስለምን ቤቴን ታቀላላችሁ? እናንተም የምትደፋፈሩኝ ያለ ቅጣት አትታለፉም።

እናንተ በቤቴና በቅጥሬ ለአምልኮት የምትመጡና ደጅ የምትጠኑ፤ የስጋችሁን ጉዳይ በየመስሪያ ቤቱ በጥንቃቄ፣ በትህትና፣ በአክብሮት፣ በዝግጅት አቅርባችሁ ስታስፈጽሙ፤ በኔ በእዉነተኛዉ ባለስልጣን ቤት ግን ትህትና በጎደለዉ፣ እኔን መፍራት በሌለዉ ህይወት በመመላለስ ትገባላችሁ ትወጣላችሁ። ታዲያ በምን መልኩ ላስተናግዳችሁ? ትህትናን፣ ፍቅርን፣ እዉነተኛነትን፣ ትግስትን፣ ይቅር ባይነተን ተላበሱ።

ዉስጣቸዉ ስለእዉነት የሚቃጠሉ፤ ስለ በጎቼ መቅበዝበዝ እረኛ ማጣት የሚያዝኑ ፤ለወንጌል መስፋፋት የሚተጉ፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እምነቷን፣ ስርአቷን፣ ትዉፊቷን ጠብቀዉ ለቀጣይ ትዉልድ ለማስተላለፍ ገንዘባቸዉን እዉቀታቸዉን ጊዜያቸዉን በመሰዋት ሌት ተቀ የሚተጉ፤ ቤተክርስቲያንን ለእናትነቷ እነጂ የሚፈልጓት በስሟ የማይነግዱባት፤ እኔ ያከበርኳቸዉን ሐዋርያትን፣ ነብያትን፣ ፃድቃንን፣ ሰማዕታትን፣ ባጠቃላይ የቅዱሳንን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘክሩ፤ እናቴንና እናታችሁን እመቤታችሁን ድንግል ማርያምን ከፍ ከፍ የሚያደርጉና ቅድስናዋን የሚመሰክሩ፤ በዚህ መንፈሳዊ ሆነ ስጋዊ ወንበር ላይ ተቀምጠዉ ለጊዜዊ ስልጣን ክብር፣ ዝና፣ ጥቅም፣ሰዎች ሁሉ ሕሊናቸዉ ሸጠዉ እውነቱት ሐሰት፣ ሐሰቱን እውነት፣ እምነቱን ክህደት፣ ክህደቱት እምነት፣ ጠማማዉን ቀና፣ ቀናዉን ጠማማ፣ መልካሙን መጥፎ፣ መጥፎዉን መልካም፣ ብርሃኑን ጭለማ፣ ጭለማዉን ብርሃን፣ ቅዱሱን ርኩስ፣ ርኩሱን ቅዱስ፣ ትዕቢቱን ትሁት፣ ትሁቱን ትዕቢት፣ እዉነተኛዉን አስመሳይ፣ አስመሳዩን እዉነተኛ፣ ከሀዲዉንና መናፍቁን አማኝ፣ እዉነተኛ አማኙን ከሀዲ፣ ማህበረ ሰይጣንን ማህበረቅዱሳን፣ ማህበረ ቅዱሳንን ማህበረ ሰይጣን በሚባልበት ዘመን፤ ከነፈሰዉ ጋር ያልነፈሱ፤ ሕሊናቸዉን ያልሸጡ፤ በቅድስት ቤተክርስቲያን ላይ እምነቷን፣

ስርአቷን፣ ዜማዋን ለመለወጥና ለማሻሻል በተነሱት የአመፃ ልጆች ላይ በፅናት የጥፋት ተግባራቸዉን በማጋለጥ የተንኮል ተግባራቸዉን የገቱ፤ አሁንም የአመጻ ልጆች በዋንኛ የሃይማኖት መሪዎች ተደግፈዉ በተለያየ መንገድ በቅድስት ቤተክርስቲያን የሚያደርሱትን ጥፋት በፅናት ተግባራቸዉን የሚቃወሙና ለማስቆም የሚታገሉ፤ በአጠቃላይ የኔን ፈቃድ የሚፈፅሙና የሚያስፈፅሙ፤ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ የሆነ የሚቆጣጠራቸዉም እርሱ የሆነ፤ ባላቸዉ አቅም ሁሉ ቤተክርስቲያንን፣ ገዳማትን፣ የአብነት ትምህርት ቤቶችን የሚረዱና እገዛ የሚያደርጉ፤ አለም ግን ያላወቃቸዉ፤ ለዚህ ትዉልድ ያስነሳዋቸዉ የኔ ባለሟሎች የድንግል ማርያም ምርጥ ልጆች አሉና፤ እናንተ በአመጻ በስጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ሁሉ ወንበራችሁ ተላልፎ ይሰጣል፤ እናንተም ዉርደታችሁን ትከናነባላችሁ::እነርሱ በዚህ በፈታኝ ዘመን ታምነዋልና ምንምእንኳን እናንተ የእነሱን መጥፋት ብትመኙም ከኔ የሆነዉን ልታሸንፉ አትችሉምና ከፍ ከፍ አደርጋቸዋለሁ፤ አገልግሎታቸዉንም እጅግ በጣም እጅግ አሰፋዋለሁ ::

እናንተ ምዕመናን እንግዲህ በስሜት የተጓዛችሁበት ዘመን ይብቃ፤ ክርስትና በግብታዊነትና በስሜት የምትመላለሱበት አይደለም:: ከሀዲዉም፣ መናፍቁም፣ አስመሳይ አገልጋዩም፣ ተኩላዉም እንደሚላችሁ አትጓዙ ::ለዚህ ለስጋ ህይወታችሁ ጊዜ ሰታችሁ ገንዘባችሁን አዉጥታችሁ እንደምትማሩ ሁሉ ለነፍሳችሁ የሚጠቅማችሁን ለስጋችሁም ዋጋ ያለዉን መሰረታዊ የሃይማኖት ትምህርት ተማሩ፣ ማንን እነደምታመልኩ ተስፋችሁ ምን እንደሆነ በሚገባ እወቁ:: የቅድስት ቤተክርስቲያንን ስርአት ተረዱ:: የድንግል ማርያምን የቅዱሳንን ክብር አስተዉሉ::

እናንተ በእዉነተኛዉ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ያላችሁ የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች፣ የቅድስት ቤተክርስቲያን ልጆች፣ በየከተማዉ አገልግሎት እንደምትሰጡ ሁሉ በገጠርና በአራቱም ማዕዘን የዋህና ቅኖች በጎች አሉኝና ከተወለዱበት ቋንቋ ዉጭ ሌላ ቋንቋ የማይሰሙ አሉና በሚሰሙት ቋንቋ የህይወት መንገደ የሆነችዉን ቀጥተኛዋን ተዋህዶ ሃይማኖት እምነቷን በሚገባ አስተምሯቸዉ፤ እነደ እግዚአብሄር ቃል የፅድቅ ስራ እንዲሰሩ፣ ከኃጢአታቸዉ በንስሐ እንዲመለሱ አድርጉ:: በአጠቃላይ በዘልማድ ሳይሆን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እምነቷን ስርአቷን አዉቀዉ እንዲኖሩ አድርጉ:: እንደቀደሙት ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናት ግመሉን እንደሚዉጡ ትንኝን እንደሚያጠሩ እነሱ የማይሸከሙትንና የማያደርጉትን ሸክምና ስርአት በአማኞች ላይ እንደሚጭኑ በነዚህ በጎች ላይ አንዳች የከበደ ሸክም እንዳትጭኑ፤ ሸክሜ ቀሊል ቀንበሬ ልዝብ ነዉና:: በመጀመሪያ መሰረታዊ የሃይማኖት ትምህርት አስተምሯቸዉ፤ ከዚያም የሥላሴን ልጅነትን እንዲያገኙ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸዉ፤ ቅዱስ ስጋዉን ክቡር ደሙን ይቀበሉ፤ ወደ ኃጢአት ተግባር እንዳይመለሱ የህይወትን ቃል ይማሩ፤ ቃሉን ሲያስተዉሉና ፀጋዉ ሲበዛላቸዉ ያኔ እናንተ ከምትፈጽሙት መንፈሳዊ ተጋድሎና ትሩፋት ስራ በላይ ሊሰሩ ይችላሉና::

ፍፁምነት ሆነ ቅድስና ደረጃ ላይ የሚደረሰዉ ቀስ በቀስ መንፈሳዊ ህይወትን በማጠናከር ስለሆነ ጸጋን የሚገኝበትን የተለያየ የትሩፋት ስራ በአንዴ እንዲፈጽሙ አታስገድዱ፤ነገር ግን ማንኛዉም ሰዉ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከትዕቢት፣ ከአመጻ፣ ከርኩሰት፣ ከዝሙት፣ ከዘፋኝነት፣ ከዳንኪራ፣ ከጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ ከዘረኝነት ፣ ከጎጠኝነት ፣ ከጥላቻ፣ ከቂም በቀል፣ ከግድያ፣ ከስርቆት፣ በአጠቃላይ ሰዎችን ከሚያረክሱ ከመንግስተ ሰማያት ከሚለዩ የርኩስ መንፈስ ፍሬ ከሆኑት በህይወታቸዉ ዘመን ሁሉ እንዲለዩ እንዲርቁ አድርጉ::እነዚህ በዲያብሎስ ርኩስ መንፈስ መሪነት የሚከናወኑ ኃጢአት ተግባር ማናችሁም ብትሆኑ ካልተለያችሁ የኔን መንግስት መዉረስ አትችሉም::ከገሃነም ፍርድም አታመልጡም::» ይላል የቅድስት አርሴማ፣ ክርስቶስ ሰምራ፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ መርቆርዮስ፣ ፖሊካርፐስ፣ ስጢፋኖስ፣ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ዲዮስቆሮስ፣ አትናቴዎስ፣

ባስልዮስ፣ ቄርሎስ፣ አፍሬም፣ ሕርያቆስ፣ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ አቡነ አረጋዊ፣ አቡነ ገብረ ክርስቶስ የቅዱስ ያሬድ፣ ላሊበላ፣ የአቡነ ኢየሱስ ሞዐ፣ የአቡነ ዜና ማርቆስ፣ የአቡነ ተክለሃይማኖት፣ የአቡነ ሳሙኤል፣ የታላቁ አባት የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የመሳሰሉት ቅዱሳን ሰዎች አምላክ፡፡

## *ምዕራፍ ሁለት*

*« የቀደሙት ኢትዮጵያዉያን አባቶቻችሁ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ ሌላዉ አለም ለስጋዉ የሚመች ስርአት ሲያዘጋጅ፤ ለነፍሳችሁ የምትጠቀሙበትን የጾም ሰርአት አዘጋጁላችሁ፡፡ሌላዉ አለም ምንም ትኩረት ያልሰጠዉን የአደራ እናታችሁን የእመቤታችሁን የድንግል ማርያምን ሞቷን፣ ትንሳኤዋንና እርገቷን ለማሰብ ጸጋን የምታገኙበትን የፍልሰታን ጾም አዘጋጁላችሁ ፡፡ እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ ሌላዉ ዓለም ቦታ ያልሰጠዉን በነፍሳችሁ የምትጠቀሙበትን ነገረ መስቀሉን የምታስቡበትን የመስቀልን በዐል፣ ሰዉ ሆኜ መጠመቄን ለማሰብ የጥምቀትን በዐል ስርአት አዘጋጁላችሁ፡፡ የአሁኖቹ መሪዎቻችሁ ደግሞ በተቃራኒዉ በዲያብሎስ መንፈስ ተመርተዉ መደዴ ኑሮ እንድትኖሩ፣ የአህዛብን አኗኗር ስርአት ዘረጉላችሁ፤ በየወንዛወነዙ ባዕድ አምልኮ እንድትፈጽሙ ርኩሰትን አዘጋጁላችሁ፤ የአህዛብን ልማድ(ባህል) አስፋፉላችሁ፡፡*

*የቀደሙት ኢትዮጵያዉያን አባቶቻችሁ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ ስጋዊዉንና መንፈሳዊዉን ህይወታችሁን በአንድ ላይ የምትመሩበትን እግዚአብሄር መፍራት ያለበትን ስርአት አዘጋጁላችሁ፡፡ በዘር በነገድ በጎሳ በቋንቋ ሳትለያዩና ሳትከፋፈሉ በፍቅርና በአንድነት እንድትኖሩ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንድትሆኑ አደረጉ፡፡ የአመጸ ልጆች ደግሞ በተቃራኒዉ እንድትከፋፈሉ፣ በጥላቻ እንድትተያዩ፣ በቂምበቀል ህይወት እንድትመላለሱ፣ ፍቅር እንዳይኖራችሁ፣ አንድ እንዳትሆኑ አደረጉ፡፡*

*የቀደሙት ኢትዮጵያዉያን አባቶቻችሁ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ እዉነተኛ የሀገርና የሃይማኖት ፍቅር እስከ ሰማዕትነት ድረስ አስተማሯችሁ፤ የአሁኖቹ መሪዎቻችሁ ደግሞ ለስልጣናቸዉና ለጥቅማቸዉ ብቻ የማስመሰልና የሽንገላ የሀገር ፍቅር አስተማሯችሁ፡፡ ስልጣናቸዉና ጥቅማቸዉ ካልተጠበቀ ግን እርስ በእርስ እንድትጨራረሱ፣ እንድትገዳደሉ፣ እንድትገነጣጠሉ፣ እንኳን ኢትዮጵያዊ ቀርቶ የኢትዮጵያ ጠላት የማያደርገዉን አሳፋሪ ህገ መንግስት አዘጋጁላችሁ፡፡*

*የቀደሙት ኢትዮጵያዉያን አባቶቻችሁ የራሳዉቸን፣ የቤተሰባቸዉን፣ የህዝባቸዉን፣ የመንደርና የከተማ ስሞችን በእኔ፣ በሥላሴ ፣ በእናቴ በአደራ እናታችሁ በእመቤታችሁ ድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች፣ እንዲሁም ለዚህች ለተቀደሰች ሀገር ታሪክ በሰሩ ስም ሀገር(ዜግነት)፣ ዘር፣ ነገድ ፣ ቋንቋ፣ ጎሳ ልዩነት ሳይገድባቸዉ ይሰይማሉ፤ መታሰቢያ ያደርጋሉ፡፡ የአሁኖቹ የአመጸ ልጆች ደግሞ እንኳን መሰየምና መታሰቢያ ሊያደርጉ ቀርቶ የነበረዉን መታሰቢያ የሚያጠፉ፤ የራሳቸዉን የርኩሰትና የአመጸ መታሰቢያ የሚያደርጉ ጠማማነት የሞላባቸዉ ነዉ፡፡*

*በአጠቃላይ የቀደሙት ኢትዮጵያዉያን አባቶቻችሁ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ በነፍሳችሁና በስጋችሁ የምትጠቀሙበት ስርአት ሰሩላችሁ፡፡ የአመጸ ልጆች ደግሞ በዲያብሎስ መንፈስ ተመርተዉ በነፍሳችሁና በስጋችሁ የማትጠቀሙበት የሞት ስርአት ሰሩላችሁ፡፡ የቀደሙት ለነፍሳችሁና ለስጋችሁ በሚጠቅም ነገር ላይ ጊዜያችሁን እንድታሳልፉ ሲያደርጉ፡፡ በተቃራኒዉ የአመጸ ልጆች ደግሞ ሕሊናችሁ(ነፍሳችሁ) እዉነትን እንዳትሰማና በእዉነት እንዳትኖር ለነፍሳችሁና ለስጋችሁ የማይጠቅማችሁን የዲያብሎስ ማደንዘዣ የሆኑትን ትዕይንቶች፣ ወሬዎች፣ ጨዋታዎች በተለያየ ብዙሀን መገናኛ(ማስ ሚዲያ) እንድትመለከቱና ጊዜያችሁን እንድታባክኑ እንድታጠፉ አደረጉ፡፡ በዚህም ትዉልዱ ደንዝዞ ቀረ፡፡*

*የቀደሙት የሃይማኖት መሪዎቻችሁ ስለእዉነት እየመሰከሩ፣ በእዉነት እየኖሩ፣ ስለእዉነት ራሳቸዉን ክደዉ እዉነተኛ እረኝነታቸዉን አስመሰከሩ፡፡ የአሁኖቹ የሃይማኖት መሪዎቻችሁ ደግሞ ሕሊናቸዉን ሸጡ፤ ለስልጣናቸዉና ለጥቅማቸዉ በመቆም በዲያብሎስ መንፈስ የሚመሩትን*

ስጋዉያንን አወደሱ፤ የአመጻ ስራቸዉ ተባባሪና አስፈጻሚ ሆኑ:: ከዚያም አልፈዉ ከስጋዉያን መሪዎች ብሰዉ በቅርሬት ስጋቸዉ እያሉ እጅግ ያስቆጣኝን የራሳቸዉን ስዕልና ምስል(ሐዉልት) አስቁመዉ ራሳቸዉን ከፍ ከፍ አደረጉ፤ አስመለኩ::

የቀደሙት አባቶቻችሁ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ በስጋችሁ በረከትን በነፍሳችሁ ድኅነትን የምታገኙበትን በወራቶች ዉስጥ ያሉትን ቀናት በኔ፣ በሥላሴ፣ በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች ስም ሰይመዉ መታሰቢያ የምታደርጉበትን ስርአት ሰሩላችሁ:: የአመጻ ልጆች ደግሞ ለነፍሳችሁና ለስጋችሁ የማይጠቅመዉን፣ ራሳችዉንና ስጋዉያንን መጨረሻቸዉ ምን እደሆነ ያልታወቀ የሚያስቡበትንና እግዚአብሔርን የሚያስረሱበትን ስርአት ሰሩላችሁ ::

የቀደሙት ኢትዮጵያዉያን አባቶቻችሁ ነፍሳችሁ የምትጠቀምበትን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ማህሌቱን፣ ሰዐታቱን፣ አቋቋሙን፣ ቅኔዉን፣ ኪዳኑን፣ ቅዳሴዉን ፣ዝማሬዉን፣ በአጠቃላይ ምስጋናዉን በሰማያዊ ዜማ፣ በከበሮ፣ በፀናፅል፣ በመቋሚያ፣ በዋሸንት፣ በበገና፣ በማሲንቆ በክራር እግዚአብሔርን የምታመሰግኑበትን ስርአት አዘጋጁላችሁ:: የአመጻ ልጆች ደግሞ ለዲያብሎስ ስራ ማስፈጸሚያ የሚሆነዉን ዘፈን ፣ ዳንኪራ፣ ጭፈራ፤ በጊታር፣ በኦርጋን ፣ በሳክስፎን ፣በጃስ በመሳሰሉት እንዲታጀብ በማድረግ የአለም የሞት ስርአት አዘጋጁላችሁ::

የቀደሙት አባቶቻችሁ ቅዱሳት መጽሐፍትን ከጥፋት በተጋድሎ ጠበቁ፤ አዋልድ መጽሐፍትን እንድትጠቀሙበት ቅዱሳን ጸጋዉ የበዛላቸዉ በምድራዊ ህይወት ዘመናቸዉ ታላቅ ተጋድሎ የፈጸሙትን ታሪክ፣ ተጋድሏቸዉን፣ በስሜና በቃሌ የተለያየ ተአምራትና ፈዉስ ያደረጉበትን ፣ ለታላቅ ክብር የበቁበትን የሚገልጽና እንድትዘክሯቸዉ፣ መታሰቢያቸዉን እንድታደርጉ የምርጦቼ አገልጋዮች ክብርና ፍቅር እንዲኖራችሁ ገድላትን፣ ሰንክሳር፣ እንዲሁም የእናቴ የአደራ እናታችሁ የእመቤታችሁ ድንግል ማርያም ፍቅርና ክብር እንዲኖራችሁ ተአምሯን ፣ ኑሯዋቸዉ ከዚህች ዓለም ዉጭ የሆኑት ቅዱሳን ባለሟሎቼን መላእክትን እንድታዉቁና ክብርና ፍቅር እንዲኖራችሁ ድርሳናትን ፤ በረከት፣ ጸጋን ፣ እዉቀት የምታገኙበትን የተለያዩ መንፈሳዊ የጸሎት፣ የምስጋና፣ እንዲሁ የእዉቀት መጽሐፍትን አዘጋጁላችሁ:: የአመጻ ልጆች ደግሞ በተቃራኒዉ የኔን እግዚአብሔርነትን እንድትጠራጠሩ፣ የሥላሴን አንድነትና ሶስትነት እንድትክዱ፣ የእመቤታችሁን ድንግል ማርያም ፍቅርና ክብር እንዳይኖራችሁ፣ የቅዱሳን መላእክትና የቅዱሳን ሰዎች ክብርና ፍቅር እንዳይኖራችሁ፣ ኢትዮጵያዊነታችሁን የሚገዘግዝ ከልቦናችሁ የሀገርና የወገን ፍቅር እንዳይኖራችሁ የሚያደርግ፣ ከነዚህ በተጨማሪ ደግሞ ለነፍሳችሁም ለስጋችሁም አንዳች የማይጠቅማችሁን በአጠቃላይ ከእዉነተኛ ዉ የህይወት መንገድ ለይቷችሁ ወደ ሞትና መቀመቅ የሚወስዳችሁን የክህደት፣ የጥርጥር፣ የርኩሰት፣ የጥላቻ፣ የጊዜ ማባከኛና ማጥፊያ የተለያዩ አይነት ጽሑፎችን አዘጋጁላችሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉያን፣ «ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሄር» የተባለችበት ምስጢር ሀገሬ ለምን እንደሆነች ታዉቃላችሁን? የትኛዉ ሀገረ ነዉ ሌሊቱን እንቅልፍ አጥቶ ምስጋና የሚያቀርብ፣ ሌት ተቀን የሚያገለግል ካህናት ያሉበት? የትኛዉ ሀገረ ነዉ አብዛኛዉ የአመቱን ጊዜ ፆም አዉጆ በጸሎትና በጾም የሚመላለስ አገልጋይና ምዕመን ያለበት? የትኛዉ ሀገረ ነዉ እኔን ፍጹም እግዚአብሄር መሆኔን አምኖ እንደ እግዚአብሄርነቴ በእዉነት የሚያመልከኝ ምዕመን ያለበት? የትኛዉ ሀገረ ነዉ በወራቶች ዉስጥ ያሉትን ቀናት በኔ፣ በሥለሴ፣ በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች ስም ሰይሞ ታቦት አዘጋጅቶ መታሰቢያ የሚያደርግና አመታዊ በዐሉን በድምቀት የሚያከብር ህዝብ ያለበት?

የትኛዉ ሀገር ሃይማኖት ነዉ ለመስዋዕት የሚቀርበዉን የተመረጠ ስንዴና ዘቢብ(ወይን) በስርአት አዘጋጅቶ «ህብስቱ ፍፁም መለኮት የተዋሃደዉ የክርስቶስ ስጋ ይሆናል ወይኑም ፍፁም መለኮት

የተዋሃደዉ የክርስቶስ ደም ይሆናል» ብሎ በማመን የሚቀበለዉና የሚያቀብለዉ ? በዚህች በተቀደሰች ሀገር ነዉ ይህ ሁሉ በአግባቡ የሚከናወነዉ::

የትኛዉ ሀገረ ነዉ በእኔ፣ በሥለሴ፣ በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች ስም በተሰየመዉ ቤተ ክርስቲያን በእምነቱ፣ በፀበሉ «እግዚአብሄር ያድነኛል» ብሎ በማመን በስጦታዬ የሚጠቀም የዋህ የማይጠራጠር ህዝብ ያለበት? የትኛዉ ሀገረ ነዉ በኔና በቅዱሳኖቼ ስም የተሰየመዉን ቤቴና ቅጥሬን የሚያከብር፣ጫማዉን አዉልቆ ወደ ቤቴ የሚገባና አምልኮቱን የሚፈጽም፣ክቡር መስቀሌን የሚሳለም፣ የቤቴና የቅጥሬን ህንጻና አጥር ሳይቀር የሚስም እግዚአብሄርን መፍራት ያለበት ህዝብ ያለዉ ?

የትኛዉ ሀገረ ነዉ መነኮሳቱና መናንያኑ ይህችን ዓለም ንቀዉ ይህን ስጋቸዉን ለመቅጣትና ነፍሳቸዉን ለማበልጸግ በየዋሻዉና በየገዳማቱ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉና አዋርደዉ በጾም በጸሎት በስግደት በምስጋና በአጠቃላይ በቅድስና ህይወት የሚተጉ፤ ለሀገራቸዉና ለአለም ህዝብ ሁሉ ምህረትን የሚለምኑባት፤ ፃድቃን ያሉበት ? የትኛዉ ሀገረ ነዉ በቅድስናቸዉ ከእኔ ጋር፣ ከድንግል ማርያም ጋር፣ ከቅዱሳን ጋር የተለየ ግንኙነት ያለቸዉ ፃድቃን ያሉበት? የትኛዉ ሀገረ ነዉ ነፍስን የሚያረካ በሰማያዊ ዜማና ስርአት ምስጋና የሚቀርብበት?

የትኛዉ ሀገረ ነዉ ሰላምታዉ፣ ንግግሩ፣ ምስጋናዉ እኔ እግዚአብሄር የምጠራበትና የምመሰገንበት? የትኛዉ ሀገር ነዉ ለሀገርና ለዓለም ምህረት እንዲደረግ በፀሎትና በምህላ የሚማጸኑ ህዝቦች ያሉበት? የትኛዉ ኢትዮጵያዊ ነዉ የእናቴን የአደራ እናታችሁን የእመቤታችሁን የድንግል ማርያም ፍቅር የሌለዉና ከንግግሩ ከምስጋናዉ የሚለይ? ማንም የለም:: እርሱ ዲያብሎስ ሃይማኖቱንና ኢትዮጵያዉነቱን ከልቡ መንግሎ ካወጣበትና ሕሊናዉን የርኩሳን መናፍስት ማደሪያ ካደረገ ሰዉ በስተቀር:: የትኛዉ ሀገረ ነዉ ባጠቃላይ እኔ እግዚአብሄርን በእዉነት የምመለክበት ሃይማኖት፣ ስርአት፣ ህይወት ይዞ በቅንነት፣ በየዋህነት፣ በትጋት፣ በትህትና እኔን በመፍራት የሚኖርባት የዋህ ህዝብ ያለባት?

የሚያሳዝነዉ ግን የአመጻ ልጆች ተነሱና እኔን ለማስካድ፣ ሃይማኖትን ለማጥፋት፣ ትዕቢትንና አመጽን ለማንገስ፣ ዘፋኝነትንና ዳንኪርተኛነትን ከህጻን እስከ አዋቂ ሕሊና ዉስጥ ለማስረጽ፣ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ጥላቻን፣ ቂም በቀልን ለመዝራት፣ ግፍንና ርኩሰትን ለማስፈጸም ተግተዉ ሰሩ፤ የአመጻም ፍሬ አፈሩ :: እኔ ግን ስለ የዋሁ ህዝብ ስል የእነርሱን የአመጻና የርኩሰትን ተግባርና ሐሳብ አጸዳለሁ:: የዋሁንና ቅኑን ህዝብ በሃይማኖቱ አጸናለሁ፤ ለበረከተና ለድኅነት ዘመን አበቀዋለሁ::

እናንተ በፕሮቴስታንት በተለያየ ክፍልፋይ እምነት መሳይ ክህደት ዉስጥ ያላችሁ፤ ማስተዋል ያጣችሁ፤ ወንጌልን እንሰብካለን እዉነትን እንናገራለን የምትሉ፤ ለመሆኑ ስንት እዉነት፣ ስንት ወንጌል፣ ስንት እግዚአብሄር አለ!? አንድ እዉነት አንድ ወንጌል አንድ እግዚአብሄር ካለ፤ እናንተም አንድ ትሆኑ ነበር:: ነገር ግን እናንተ ከእኔ ስላልሆናችሁ ሕሊናችሁን በበላይ የሚመራችሁ ዲያብሎስ ከፋፈላችሁ፤ ሲፈልግ እኔን «ፍጡር ነዉ» እያስባለ ያስክዳችኋል:: ሲፈልግ እኔን «አማላጅ ነዉ» እያስባለ ያሰድባችኋል:: ሲፈልግ እኔን «እግዚአብሄር ያልሆነ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ ነዉ» እያለ ያጃጅላችኋል:: ሲፈልግ« አብ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚባል የለም ራሱ ወልድ ነዉ በተለያየ ጊዜ የሚገለጽ የነበረዉ »እያለ ከህይወት መንገድ ያወጣችኋል::

ዲያብሎስ በዚህ ሳያበቃ እርሱ የማይዳፈረዉንና የማይናገረዉን፤ እናቴን የአደራ እናታችሁን የመዳኛ ምክንያታችሁን እመቤታችሁን ሁል ጊዜ በፊቴ ለሰዉ ዘሮች ጥብቅና የምትቆምና ምህረትን የምትለምን እስከ አሁን ስለ ሰዉ ልጆች በሐዘን ያለችዉን ድንግል ማርያምን ያሰድባችኋል፤ ስለ

ሰዉ ልጆች ጥብቅና በመቆም ምህረትን የሚለምኑትን ቅዱሳን መላእክትን ያሰድባችኋል፤ እንደ እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮች የሆኑ በተጋድሏቸዉና በቅድስናቸዉ ለክብር ለማዕረግ የበቁ ከዚህች ዉጣ ዉረድ ዓለም ተለይተዉ ወደ እኔ የመጡ የቅድስና ማእረግ የሰጠዋቸዉን፤ ምድር ላይ ላሉ ወገኖቻቸዉ ሁሉ ምህረትን የሚለምኑትን ነብያቶቼን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን ያሰድባችኋል፡፡ እረ ስንቱ ይነገራል የእናንተ አመጻና ክህደት!

እስቲ አስተዉሉ «ፍጡር ነዉ» የሚለዉ «አማላጅ ነዉ» የሚለዉ «አንድ ኢየሱስ(ወልድ) ነዉ» የሚለዉ ሁሉ «ልሳን» የሚባለዉን ይናገራል ፡፡ ነገር ግን ሶስታችሁም እምነታችሁ የማይገናኝ እጅግ የተለያየ ነዉ፡፡ታድያ እንዴት ከእግዚአብሄር የሆነ ልሳን ትናገራላችሁ? ለመሆኑ የማይታወቅ ልሳን አለ ወይ?ነገር ግን የሚያናግራችሁና መጫወቻ ያደረጋችሁ እርሱ ሐሰተኛዉ አመጸኛዉ ዲያብሎስ ነዉ፡፡ እንኳን ወዳችሁ ፈቅዳችሁ ሕሊናችሁን(ነፍሳችሁን) አሳልፋችሁ ሰታችሁት ቀርቶ በእዉነተኛ ዉ እምነት ዉስጥ ሆነዉ ጸጋዉ በዝቶላቸዉ ሰይጣናትን የመቅጣት፣ የመገሰጽ፣ የማዘዝ ስልጣን የተሰጣቸዉን ሰዎች ሳይቀር የሚፈታተንና የሚጥል ክፉ ጠላት ነዉ፡፡ ማንኛዉም የእኔ አገልጋይ የሆነ በህይወት ዘመኑ እኔን በተግባሩ ብቻ አይደለም በሐሳቡ ጭምር በመፍራትና በእዉነት በመገዛት የማይመላለስ ከሆነ ጸጋዉ ይገፈፋል፤ ለማይገባ ባህርይ ተላልፎ ይሰጣል፤ በመጨረሻም የባሰ የመከራና የስቃይ ፍርድ ይቀበላል፡፡

እናንተ በዚህች በተቀደሰች ሀገር እዉነትን ለማጥፋት ክህደትን ለማስፋፋት የተነሳችሁ የአመጽ ልጆች፤ ለመሆኑ የእዉነት ባለቤት ማን እንደሆነ ታዉቃላችሁን? አታዉቁም፡፡ ብታዉቁስ ኖሮ የእዉነትን ባለቤት የሁንኩትን እኔን እግዚአብሄርን ለማጥፋትና ለማሳደድ አትሞክሩም ነበር፡፡ እዉነቱን በሐሰት ስትለዉጡ፣ ሐሰትን ስታነግሱ፣ እዉነትን ስታክፋፉና ስታጥላሉ፣ ዝም ስል አቅቶኝ ወይንም ዘንግቼ ይመስላችኋልን?ሕሊናችሁ በአመጽ፣ በክፋት፣ በተንኮል፣ በትዕቢት ስለተሞላ የእኔን ስራና ባህርይ ማስተዋል ተስኗችኋል፡፡ እኔ ስፈቅድ ብቻ ነዉ ሁሉ በጊዜዉ የሚሆነዉ እንጂ በራሳችሁ አንዳች የማድረግ ሆነ የመሆን ስልጣን የሌላችሁ ተራና ደካማ ፍጡሮች ናችሁ፡፡

ክህደቱም፣አመጻዉም፣ግፉም፣ መናፍቅነቱም፣ ርኩሰቱም፣ በደሉም፣ ኃጢአቱም ሲነግስ ዝም የምለዉ የአመጻና የግፍ ፅዋችሁ ሞልቶ እስከሚፈስ ድረስ ብቻ ነዉ፡፡ አሁን ግን ፅዋችሁ ሞልቶ መፍሰስ ጀምሯል፡፡ብትነገሩ፣ ብትመከሩ አልሰማ ብላችኋልና የአመጽና የግፍ ዘራችሁን ታጭዳላችሁ፡፡ እኔን ለመገዳደርና ለማሸነፍ አትችሉምና እንዳልነበራችሁ ትሆናላችሁ፡፡

በዚህች ሀገር እዉነትን ለማጥፋት «ጉዲት» የተባለች የአመጽ ልጅ ለአርባ ዘመን( አመታት) ቤተ ክርስቲያንን ስታቃጥል፣ ክርስቲያኖችን ስታሳድድ ስትገል ነበረ፡፡ ነገር ግን እዉነትን አላጠፋችም፡፡ እስከአሁን ድረስ ይህች እዉነተኛ ቤተ ክርስቲያን አለች፤ እስከ አለም ፍጻሜም ትኖራለች፡፡«ግራኝ አህመድ» የተባለ የአመጽ ልጅ ለአስራ አምስት አመታት ቤተ ክርስቲያንን ሲያቃጥል፣ ክርስቲያኖችን ሲያሳድድ ሲገል ነበረ፡፡ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ሆነ ክርስቲያኖችን ሊያጠፋ አልቻለም፡፡አሁንም ለሰላሳ ሰባት(37) አመት የአመጻ ልጆች ተነስተዉ ክህደትንና መናፍቅነትን ቢያስፋፉ፤ መድረኮችንና ብዙሀን መገናኛን (ማስሚዲያን) ለዘፈንና ለዳንኪራ ለወሬ ቢያዉሉም፤ ሰዎች ወደ እዉነት እንዳይመጡ በተለያየ መንገድ ሐሰት እንድትነግስ ቢያደርጉም፤ በሰዎች መካከል ጥላቻና መከፋፈል ቢዘሩም፤ እዉነትን ሊያጠፉ ሆነ ሊያሸንፉ አይችሉም፡፡ እዉነት ትነግስና የሐሰት ተግባራቸዉ ገበና ትገልጣለች፤ ባዶ ቀፎ መሆናቸዉን ታሳዉቃለች፤ መንገዳቸዉ ሁሉ የሞት መንገድ ጨለማን የለበሰ የዲያብሎስ ፍሬ መሆኑን ታሳዉቃቸዋለች፡፡ » ይላል ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ የሚፈርድለትና የሚፈርድበት ብቸኛ እዉነተኛ ትክክለኛ ፈራጅ እግዚአብሄር፡፡

# ክፍል አራት
## የጸሐፊዉ መልእክት ለዓለም ሕዝብና ለኢትዮጵያዉያን በሙሉ
## ምዕራፍ አንድ

የተከበራችሁ የአዳምና የሔዋን ዘሮች በሙሉ ከክፍል አንድ እስከ ክፍል ሶስት ያሉትን የእግዚአብሄርን ግሳጼና ቃል እንደምታነቡትና ወደዚህኛዉ ክፍል እንደምትሸጋገሩ ተስፋ አደርጋለሁ ። ያለበለዚያ ቀጥታ ወደዚህ ክፍል ከገባችሁ ልትሰናከሉና እንደ ስጋ አስተሳሰባችሁ የእግዚአብሄርን መልእክት ልታጥላሉና ላትቀበሉ ትችላላችሁ።

ሌላዉ እንድታዉቁት የምፈልገዉ ከእግዚአብሔር የሆነን ማንኛዉንም ነገር ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያጠፋዉ አይችልም። ሙከራ እንኳን ቢያደርግ መከራና ችግር ይደርስበታል እንጂ ሌላ አንዳች የሚፈይደዉ ነገር የለም። እንኳን እኛ ግዙፎቹ ሰዎች ቀርቶ በአይን የማይታዩ ረቂቅ ነገሮች ሁሉ ከእርሱ በወጣ ሃይል የተዋቀሩና በእግዚአብሄር እይታና ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆኑ ካለ እርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን አይቻልም።

ስለዚህ በስጋዊ አይነ ሕሊና ይህን መጽሐፍ ተመልክታችሁ ከእግዚአብሄር የሆነዉን ለማስቀረት ወይንም ለማዘግየት ከንቱ የሆነ ስጋዊ መጠበብ ለማድረግ አታስቡ።እግዚአብሄር ሊያደርግ የወደደዉን በፈለገዉ ጊዜ በፈለገዉ መልኩ ሊያደርግ ይችላልና አንዳች ማሰናከያ እንዳታደርጉ።ማስተዋሉ ካላችሁ በቅዱሳት መጽሐፍት ላይ የተጻፉትን ያለፉትን ታሪኮች አንብባችሁ ተረዱ።የግብፅ ፈርኦን በትዕቢቱ በራሱና በህዝቡ ላይ አስር አይነት መቅሰፍቶች አምጥቷል።በዚያም ትዕቢቱ አልበርድ ስላለ በኤርትራ ባህር ዳግም እንዳይታበይ ከነሰራዊቱ ሰጥሟል። እስራኤላዉያን፤ በድንቃ ድንቅ መቅሰፍትና ተአምር ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣቸዉን የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብን አምላክ እግዚአብሄርን ዘንግተዉ በተለያየ መልክ የተፈታተኑትንና ያስቆጡትን በበረሃ(በመንገዳቸዉ) እንዴት እንደቀጣቸዉና እንዳረገፋቸዉ አስተዉሉ።የመረጣቸዉን ደግሞ በድንቅ ሃይሉ የከነዐንን ሀገር እንዲወርሱ እንዳደረገ በሚገባ ተረዱ።በኖህ ዘመን ኖህና ቤተሰቡ እንዴት እንዳዳነ አመጸኞችን እንዴት እንዳጠፋ አስተዉሉ፤በአብርሃም ዘመን ሎጥንና ቤተሰቡን እንዴት እንዳዳነ ርኩሰትን ፈጻሚዎችን እንዴት እንዳጠፋ በዉስጧ ስዉር አመጽ ያለባትን የሎጥን ሚስት እንዴት አድርጎ እንዳዋረዳት አስተዉሉ። በመሆኑም ከእግዚአብሄር ጋር የሚጣላ፣ ይደቃል፤ ይጠፋል እንጂ የሚቋቋመዉ የሚያሸንፈዉ ምንም አይነት ፍጡር ስለማይኖር ሁሉም የሰዉ ዘር በሙሉ ከእግዚአብሄር የሆነዉን እዉነት ተቀብሎና አምኖ እነደ ቃሉ ሆኖ በመገኘት ራሱን ከሞትና ከጥፋት ሊያድን እንዲሁም ለመልካሙ ዘመንና ለሰማያዊ መንግስት ሊያበቃ ይገባዋል።

እግዚአብሄር የወቀሰንና የገሰጸን ስለ መልካም ስራችን አይደለም፤ ነገር ግን ስለ አመጻችን ስለክህደታችን፣ ስለ ርኩሰታችን በአጠቃላይ ስለ ኃጢአታችን ብቻ ነዉ። ስለዚህ መልካም ተግባራችንን የበለጠ አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል። ከኃጢአታችን ደግሞ ሙሉ በሙሉ መለየት ይኖርብናል።

ይህ መጽሐፍ መጻፍ የተጀመረዉ መስከረም አንድ ሁለት ሺህ ሶስት ፳፻፫ (2003. ዓ.ም.) ነዉ። ጸሐፊዉ ከሳምንታት በፊት «ኢትዮጵያ የአለም ብርሃን» በሚል ርዕስ በሶስት ጊዜ የተጻፈ ጥራዝ መልእክት(አንደኛዉ ህዳር 7/1998ዓ.ም ለአለምና ለኢትዮጵያህዝብ የተላለፈ መልእክት፤ሁለተኛዉ ግንቦት 27/2000 ዓ.ም ለአለምና ለኢትዮጵያ ህዝብ የተላለፈ መልእክት ሶስተኛዉ ደግሞ የመጨረሻ የአፈጻጸም ዉሳኔ መጋቢት 19/2001 ዓ.ም.) ተጽፈዉ የነበሩትን አግኝቶ ያነበበና መልእክቱም በአለም ህዝብና በኢትዮጵያ የሚደርሰዉን ከእግዚአብሄር ተገልጾለት የጻፈ ሰዉ እንዳለና ይህም ሰዉ

ለኢትዮጵያና ለአለም ህዝብ ታላቅ ስራ የሚሰራ የእግዚአብሄር ምርጥ ባለሟልና የተቀባ መሆኑን ተገንዝቧል:: ከመልእክቱም ኢትዮጵያ በምህረት የምትጎበኝበትና ዓለም ደግሞ በአመጻዋ ምክንያት የምትቀጣበት ዘመን በደጅ መድረሱን አዉቋል:: እረኛዉ አንድ መንጋዉ አንድ የሚሆንበት ዘመን መድረሱን ተገንዝቧል:: የሚያሳዝነዉ ግን የአለም ህዝብ ሆነ መሪዎች የዘመኑ የጥፋት ዉሃ (የተለያዩ መቅሰፍቶች) ደጃፋቸዉን አልፎ ቤታቸዉ ዉስጥ መግባቱን አላወቁም፤ ለማወቅም ፈቃደኛ አይደሉም:: የጸሐፊዉ ምኞትና የሚመክረዉ ሰዎች ሁሉ በመልእክቱ እንደተገለጸዉ ከጥፋት እንዲድኑና እንዲተርፉ ወደ መርከቢቱ(ወደ እዉነተኛዉ የእግዚአብሄር ቤት በዚህ መጽሐፍ ወደተገለጸችሁ ሃይማኖት) በመግባት ለእግዚአብሄር እጅ እንዲሰጡና ለመልካሙ ዘመን እንዲደርሱ ነዉ::

የአዳምና የሔዋን ዘሮች በሙሉ፤ ባለማወቅና ባለማስተዋል ሁላችንም የዚህች አለም ገዥ ለሆነዉ ለዲያብሎስ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ተንበርክከናል::ፈቃዱንም ፈጽመናል:: እግዚአብሄርን ረስተናል:: ስለዚህ በክፍል ሁለትና ሶስት እግዚአብሄር የገሰጸንና የወቀሰን እጅግ ያንሰናል፤ በመሆኑም ነገረ መስቀሉን ከንቱ ያደረግን ወራዶችና ኃጢአተኞች መሆናችንን ከሕሊናችን ልናምንና «ምን ማድረግ አለብን?» ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል::

ጸሐፊዉ እንደእናንተዉ ተገስጿል፤በምድራዊ ህይወቱም ዘመን እንደእናንተዉ በኃጢአት ወድቋል ከእናንተም በላይ ኃጢአት ፈጽሟል፤ ምክንያቱም ሰማያዊ ምስጢር አዉቆና አስተዉሎ እስከመጨረሻዉ በቅድስና ህይወት መኖር ሲገባዉ ወደ ትፋቱ ተመልሷልና:: ነገር ግን ንስሐ ገብቷል፤ የክርስቶስን ቅዱስ ስጋ ክቡር ደሙን ተቀብሏል:: ስለዚህ በተለያየ ኃጢአት የወደቅን ሰዎች ንስሐ ልንገባና እዉነትን ልንቀበል ይገባናል:: ምክንያቱም በስጋችንም በነፍሳችንም ተጠቃሚዎች እኛዉ ሰዎች ነን:: በተቃረኒዉ ንስሐ ባንገባና እዉነትን ባንቀበል በምድራዊ ህይታችንም፣ ከዓለም እልፈት በኋላም የምንጎዳዉ እኛዉ ነን እንጂ የእግዚአብሄርን ዉለታ ከንቱ ከማድረግና የባሰ ፍርድ ከመቀበል ዉጭ በእግዚአብሄር ላይ የምንጨምረዉ ሆነ የምንቀንሰዉ አንዳች ነገር የለም::

በመሆኑም ያለፈዉ ዘመን በክፋት፤ በተንኮል፤ በምቀኝነት፤ በክፉ ቅናት፤ በትዕቢት፤ በአመጻ፤ በዝሙት፤ በርኩሰት፤ በጣዖትና በባዕድ አምልኮት፤ በጥንቆላ፤ በመተት፤ በአስማት፤ በሟርት፤ በግድያ፤በስርቆት፤በማታለል፤ በመዋሸት፤ በማስመሰል፤ በክህደት፤ በመናፍቅነት፤ በስንፍና፤ በጥላቻ፤ በቂም በቀል፤ በዘረኝነት፤ በጎጠኝነት፤ በዘፋኝነት፤በዳንኪርተኛነት፤ በአጠቃላይ የዲያብሎስ ፍሬ ከሆኑት ከእግዚአብሄር መንግስት ከሚለዩን ተግባራት ሁሉ እንለይ:: ህይወታችንንም በንስሐ፣ በቅን ሐሳብና በመልካም ተግባር እንምራ::

ሁላችንም ማለት ይቻላል እንደ ኃጢአት የምንቆጥረዉ በአካላችን የምንፈጽመዉን ዝሙት፣ ስርቆት፣ ግድያ፣ ጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ ጥንቆላ፣ መተት፣ አስማት፣ የመሳሰሉት ብቻ ይመስለናል::ነገር ግን እግዚአብሄር እንደተናገረን ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ክፉ ቅናት፣ ትዕቢት፣ አመጻ፣ ዘፋኝነት፣ ዳንኪርተኛነት፣ ርኩሰት የመሳሰሉት ሁሉ ከእግዚአብሄር መንግስት የሚለዩን ናቸዉ::በመሆኑም ሁላችንም በአካላችን ከምንፈጽመዉ ኃጢአት በተጨማሪ በዉስጣዊ አካላችን (በሕሊናችን) ከምንረክስበት ኃጢአት ሁሉ መለየት ይኖርብናል::

ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ፈጣሪያችን እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስ በአሁን በኛ ዘመን ተወልዶ ቢሆን ኖሮ አሁን ካለን የክፋት፣ የተንኮል፣ የአመጻ ተግባር ቀድሞ ከነበሩት ሰዎች በባሰ ሁኔታ በሐሰት የምንወነጅለዉና የምንቃወመዉ ሰዎች ነን:: በዚያን ዘመን በእርሱ ባለማመናቸዉ ከብለይ ዘመን ሰዎች በላይ የባሰ ፍርድ እንደሚጠብቃቸዉ እግዚአብሄር ከገለጸ፤ በምህረት ዘመን

ወንጌል በየአቅጣጫዉ በሚሰበክበት ዘመን በእዉነት እንደ ቃሉ ተገኝተን ካላመለክነዉ ደግሞ እጅግ የባሰ ፍርድ እንደሚጠብቀን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ባለጠጎች የሆን፤ በስግብግብነት፣ በራስ ወዳድነት፣ በምኞት፣ በመቅበዝበዝ እርካታን ያጣን ሰዎች፤በስርቆት፣ በግፍ፣ በብልጣብልጥነት፣ በአቋራጭ መንገድ ሀብት ንብረት ሰብስበን ወገኖቻችን ሲራቡ፣ ሲጠሙ፣ ሲቸገሩ፣ ሲታረዙ፣ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ሲያዙ፣ በአጠቃላይ ሲቸገሩና ሲጎሳቆሉ ዝም ብለናልና እግዚአብሄር በመጨረሻዉ ቁጣዉ ገስጾን የሰበሰብነዉን ሀብትና ንብረት ለመልካም ዘመን ለታደሉት ሰዎች አሳልፎ ሳይሰጥብን ለሀገራችንና ለህዝባችን ሁሉ በሚጠቅም ስራ ላይ እናዉል፡፡«ለኔ፣ ለልጆቼ፣ ለቤተሰቤ፣ ለዘሬ፣ለጎጤ» ብቻ የሚለዉን የስግብግብነትና የራስ ወዳድነት ጠባያችንን ትተን«ለወገኔ(ለሀገሬ ህዝብ)፣ ለአዳምና ሔዋን ዘር» ብለን በማሰብ የጽድቅ ስራ እንስራበት፡፡ የተራበዉ፣ የተጠማዉ፣ በየመንገዱ የወደቀዉ፣ የተቸገረዉ፣ የታመመዉ፣ የታረዘዉ፣ ጠያቂ ዘመድ ያጣዉ፣ የሚረዳዉ ያጣዉ፣ የአዳምና ሔዋን ዘር ወንድምና እህታችን ነዉ፡፡

በስጋዊ ወንበር ላይ ከዋናዉ የሀገር መሪ እስከታች መንደር ተሹመን ህዝብን እናስተዳድራለን እናገለግላለን የምንል ፤ መልካም ፍሬ ማፍራት አልቻልንምና ከወንበራችን ተቆርጠንና ተዋርደን መልካም ፍሬ ለሚያፈራ ህዝብ ከመሰጠቱ በፊት በክብር የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ምርጥ ባለሚሎቹ ወንበሩን እናስረክብ፡፡የኛ መሪ የሆነዉ በበለይ ዲያብሎስ ነዉና የርሱ ፈቃድ የሆኑትን ኃጢአት፣ ዝሙት፣ ዘፋኝነት፣ ዳንኪራተኛነት፣ ዘረኝነት፣ ጎጠኝነት፣ ጥላቻ፣ መለያየት፣ ግድያ፣ ዝርፊያ፣ ጦርነት፣ ርኩሰት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ትዕቢት፣ አመጻ፣ ምኑ ተነግሮ ያልቃል ያነገሥንበት ዘመን ይብቃ፡፡ለስጋችንም በረከት ለነፍሳችንም ድኅነትን የምናገኝበትን ሰማያዊ ስርዓት እንዘርጋ፡፡ ንጉሣችንም መሪያችንም አስተዳዳሪያችንም መጋቢያችንም እርሱ አንዱ እግዚአብሄር ብቻ ይሁን፡፡እንቢ ብለን የምንታበይና ወንበሩን በእግዚአብሄር ለተመረጡት አንለቅም ብንል መከራዉና ስቃዩ በኛ ላይ ይበረታል ፡፡ ተዋርደን ከወንበሩ እንቆረጣለን እንጂ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያሰበዉን ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ አይችልም፡፡ስለዚህ ሁላችንም እጃችንን ለእግዚአብሄር ልንሰጥና ስላለፈዉ በደላችን ንስሐ ልንገባ ይገባል እንጂ ከሃያሉ እግዚአብሄር ጋር ስንገዳደር እንዳንገኝ፡፡

በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ከዋናዉ የሃይማኖት አባት እስከ ገጠር አብያተ ክርስቲያን ሃላፊ የሆን፤ ራሳችንን ያስመለክንበትና በጎችን ለተኩላ አሳልፈን የሰጠንበት ዘመን ይብቃ፡፡በእዉነትና በቅንነት ምዕመናንን እያገለገልን ስለ እዉነት ራሳችንን በመካድ መመስከርና በእዉነት መኖር ሲገባን በስጋዊ ወንበር ላይ ያሉ ሰዎች ያልፈጸሙትን በደል ፈጽመናል፤ ራሳችንን አስመልከናል፤ የእግዚአብሄርን ክብር አቃለናል፡፡ ለስጋዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ለገንዘብና ለምድራዊ ብልጽግና ስንል አገልግሎታችንን እንደ ስራ መስክ ቆጥረን እዉነተኞችን ገፍተናል፣ አሳደናል፣ አሰቃይተናል፣ በሐሰት ወንጅለናል፣ አሳስረናል፣ አስገድለናል፣ አሰድበናል፣ አስደብድበናል፡፡ በማስመሰል በሸንገላ በከንቱ ዉዳሴ የተመላለስንበት ዘመን ይብቃን ፡፡ ስለ ነፍሳት መዳን ደንታ የሌለን፤ ስለ ስጋዊ ጥቅማችን ቤተ ክርስቲያንን ከመሸጥ የማንመለስ፤ከጸሐፍት ፈሪሳዉያን ከአይሁድ ካህናት የባስን አመጸኛ፤ ግመልን የምንዉጥ ትንኝን የምናጠራ፤ የእግዚአብሄርን ቃል በአንደበታችን ብቻ እንጂ የምንናገር በተግባር የማንፈጽም፤ አንደበታችን ሌላ ዉስጣችን ሌላ የሆን ፤ በእግዚአብሄር ቃል የምንነግድ፤ እኛም ወደ መንግስተ ሰማያት የማንገባ ሌሎች እንዳይገቡ እንቅፋት ማሰናከያ የሆን፤ የባሰ ፍርድ የሚጠብቀን የእግዚአብሄር አገልጋይ የተባልን ፤ ወንበራችንን ስለ እዉነት ለቆሙና በእዉነት ለሚያገለግሉ ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣ ካህናት፣ ሊቃዉንት፣መምህራን ዲያቆናት እንልቀቅ፡፡

እግዚአብሄር እያንዳንዳችንን በሚገባ ያዉቀናልና፤ ማገልገሉን እንተዉና በመጀመሪያ እኛዉ እንገልገል:: በቁጣዉ ጅራፍ ተገስጸንና ተዋርደን ከቤቱ ከመዉጣታችን በፊት ለእዉነተኛ አገልጋዮቹ ቦታዉን ለቀን በንስሐ በእጁ እንዉደቅ::

የእግዚአብሄርን ፈቃድ ባለማስተዋልና ባለማወቅ በኃጢአት ስራ የምንመላለስ ሰዎች፤ ያለፈዉ የአመጻ ዘመናችን ይብቃን::ነዉሩን እንደ ክብር፣ ኃጢአቱን እንደ ታላቅ ስራ፣ መታዘዙን እንደ ዉርደት፣ትዕቢቱንና አመጻዉን እንደ ጀግንነት፣ ርኩሰቱን እንደ ቅድስና ቆጥረን የተመላለስንበት ህይወት ይብቃን::እድሜ ሰቶን ለመልካሙ ዘመን ከደረስን ይህ እየፈጸምነዉ ያለዉ የኃጢአት ተግባር በእዉነተኛ ሕሊናችን ስንመለከተዉ «በዉኑ እኛ ሰዎች ነበርን ወይ እንዲህ የሰይጣናትን ተግባር የምንፈጽመዉ » ብለን ራሳችንን የምንታዘብ እንሆናለን::

አሁን ግን ኃጢአቱ ጽድቅ መልካም ታላቅ መስሎን እንፈጽማለን::ስለዚህ እግዚአብሄር በቁጣዉ ገስጾን ሳይቀጣን በፊት ከኃጢአት ተግባርና ንግግር ተለይተን ስላለፈዉ በደላችን ንስሐ እንግባ:: እዉነትን ያልተቀበልን ደግሞ እዉነትን ተቀብለን ለሰማያዊ መንግስት በሚያበቃን ሃይማኖት ዉስጥ እንደ እግዚአብሄር ቃል በመሆን እንመላለስ::

በተለያየ የብዙሃን መገናኛ(በመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በሬድዮ፣ በቴሌቭዥን፣ በመጽሐፍ፣ በኢንተርኔት) በመሳሰሉት አገልግሎት የምንሰጥ፤ እንግዲህ የዲያብሎስን ፈቃድ ያነገሥንበት፣ ጥላቻ የዘራንበት፣ ክህደትን ያስፋፋንበት፣ ርኩሰትን ያሳየንበት፣ አመጻ የቀሰቀስንበት፣ መናፍቅነት የዘራንበት፣ ጦርነት ያነሳሳንበት፣ መለያየት ያደረግንበት፣ በአጠቃላይ የርኩሳን መናፍስት ተግባር የፈጸምንበት ያለፈዉ ዘመን ይብቃ:: የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆኑትን መልካም ተግባሮችንና በስጋም በነፍስም የምንጠቀምበትን እዉነት ብቻ ይገለጽበት:: እግዚአብሄር ብቻ ከፍ ከፍ ይበልበት:: የሕሊናችን መሪ መንፈስ ቅዱስን አድርገን እርሱ የሚያሳስበንና የሚገልጽልንን ብቻ ለህዝቡ እያቀረብን እናሳዉቅበት፤ እናስተምርበት እንጂ በስጋም መርገም በነፍስም የገሃነም እሳት ፍርድ የሚያመጣ ትምህርትና ተግባር አናስተላልፍበት::

በተለያየ እምነት እንዲሁም በጣዖትና በባዕድ አምልኮ የምንመላለስ መንገዱ የጠፋብን፤ እንደ ስጋ ሐሳባችንና ምኞታችን የምንመላለስ፣ በራሳችን ፍልስፍና የምንኖር፣ ከወላጆቻችን በወረስነዉ ሃይማኖት የምንመላለስ፣ ያለፈዉ የክህደትና የጥርጥር የአመጻ ዘመናችን ይብቃን:: እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ እንደተገለጸዉ ከአንዱ እግዚአብሄር የሆነዉ ለሰማያዊ መንግስት የሚያበቃዉ ሃይማኖት የኦርቶዶክስ (የቀጥተኛዉ) ተዋህዶ ሃይማኖት ስለሆነ ሁላችንም በዚህ እምነት ልንኖርና እዉነተኛዉን አምላክ በማምለክና እንደ ቃሉ ሆነን በመገኘት ለህያዉነት ህይወት ራሳችንን እናዘጋጅ::

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን ሰዎች ምልጃቸዉና ምኞታቸዉ በምድራዊ ህይወታችን ዘመን ሁሉ እግዚአብሄርን በመፍራት እንድንመላለስ፤ ትዕዛዙን ሕጉን እንድንጠብቅ፤ ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ እግዚአብሄርነቱ እንድናመልከዉ ነዉ እንጂ መመስገንና መግነንን አይፈልጉም:: ነገር ግን እግዚአብሄር፣ እናቱ ለመሆን የበቃችዉና የሰዉ ልጆች መዳኛ ምክንያት የሆነችዉ፤ በምድራዊ ህይወት ዘመኗም ሐዘንተኛ የነበረች፤ አሁንም በእግዚአብሄር መንግስት ዉስጥ ሆና ስለእዉነትና ስለ ሰዉ ልጆች ሐዘን ላይ ያለች፤ ሁል ጊዜ ምህረትና ይቅርታን የምትጠይቅልን ቅድስት ድንግል ማርያም በአራቱም ማዕዘን እንድትመሰገን ፣ ከፍ ከፍ እንድትል፣ እንድትገን የእግዚአብሄር ፈቃዱ ነዉ::ለዚህም ነዉ ከሌሎች በዐላት በላይ የመታሰቢያዋ በዐል እጅግ የሚደምቀዉ::የእርሷ መመስገን፣ መግነን የእግዚአብሄር መመስገን መግነን ነዉና:: እንዲሁም ቅዱሳን መላእክት፣ ነብያት፣ ሐዋርያት ሰማዕታት፣ ጻድቃን ለሰዉ ልጆች ሁል

ጊዜ ጥብቅና የሚቆሙ፤ ምህረትን የሚለምኑ ናቸዉና እነርሱም እንዲመሰገኑና በተለየ ሁኔታ መታሰቢያ ተደርጎላቸዉ እንዲከበሩ የእግዚአብሄር ፈቃዱ ነዉ፡፡

ኢትዮጵያዉያን የሆን፤ ይህች ሀገር የእግዚአብሄር ምስጢር ሀገሩ የሆነች በቅዱሳን የምትጠበቅ፤ የእግዚአብሄር ስጦታ የበዛላት፤ እግዚአብሄር በእዉነት የሚመለክባት፤ እመቤታችን እመ አምላክ ድንግል ማርያም የምትፈቀርበት፤ ቅዱሳን መላእክት ነብያት ሐዋርያት ሰማዕታት ጻድቃን የሚከበሩባት፤ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከዜማ ጀምሮ የተለያዩ ጸጋ የተሰጣት፤ ምድሪቱም በተለየ ሀብት የተሞላች፤ ህዝቦቿም የዋሃን የሆኑ፤ እግዚአብሄር ሴት ተቀን የሚመሰገንባት ሀገር ናት፡፡

በበደላችንና በኃጢአታችን ምክንያት የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች በሆን ሰዎች ምክንያት ከእግዚአብሄር በረከት ተለየን እንጂ ያለን ስጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ሀብት ለህዝቦቿ ቀርቶ ለዓለም ህዝብ የሚተርፍ ነዉ፡፡ኢትዮጵያዉያን አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንድሞቼ፣ እህቶቼ ሁላችንም የተጠራነዉ ስጋችንም፣ነፍሳችንም በምትድንበት በኢትዮጵያ በቀጥተኛዋ ተዋህዶ ሃይማኖት ስለሆነ፤ በኃጢአት የወደቅን በንስሐ ተመልሰን፤ በሌላ በተለያየ ሃይማኖት (እምነት) እንዲሁም በባእድ አምልኮት ዉስጥ የምንመላለስ ወደ የጥንት የአባቶቻችንና የእናቶቻችን ሃይማኖት(እምነት) በመመለስ በሥላሴ ስም ተጠምቀን ልጅነትን ከእግዚአብሄር እናግኝ፡፡እንደ እግዚአብሄር ቃል ሆነን እንገኝ፡፡

ይህን ስናደርግ እግዚአብሄር ይህችን ሀገር በምህረት ይጎበኛል፡፡ ከራሷ አልፋ ለዓለም ሁሉ ስጋዊም መንፈሳዊም በረከትና አገልግሎት ትሰጣለች፡፡ እግዚአብሄር ከእርሷ ጋር ነዉና ማንም ምንም ሊያደርጋት አይችልም፡፡ሊያጠቋት ሆነ ሊያጠፏት የሚነሳሱ ካሉ እነርሱ ይደቃሉ፤ ይጠፋሉ እንጂ ሀገሪቱን የሚጠብቁ የእግዚአብሄር ሰራዊቶች በዙሪያዋ አሉና እርሷ ስንዱ እመቤት አንዲት የምትሆነዉ ነገር የለም፡፡

እግዚአብሄር፤ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ» በኋላ ላለዉ መልካም ዘመን ያብቃን እያልኩ፤ ጸሐፊዉ ወደ መንፈሳዊ ህይወት ከተጠራ በኋላ የሚጸልየዉ ጸሎት፤ በመጀመሪያ አመታት ላይ ዉዳሴ ማርያም የየእለቱን በመቀጠል ደግሞ አንቀጸ ብርሃንና ይዌድስዋን በመጨመር፤ ከተወሰነ አመታት በኋላ(ከሰባት አመታት በኋላ ) መዝገበ ፀሎት ላይ ያለዉን ዉዳሴ አምላክ የየእለቱን፣ መልክአ ኤዶም፣ እንዲሁም ወርሃዊ መታሰቢያ በሚደረግላቸዉ ቅዱሳን ስም የተዘጋጀዉን በእጄ ላይ ያሉትን መልክአ መልኮች በቀናቸዉ፣ አሁን በመጨረሻ ከስድስት ወር በፊት በእግዚአብሄር ቤት በተመረጠዉ አገልጋዩ አማካይነት ሰይጣን በእግዚአብሄር ቃል ታስሮ በሚለፈልፍበት ወቅት መጽሐፈ አርጋኖ ሲጸልዩበት እጅግ እንደሚቃጠል በሽተኛዉ ላይ አድሮ ሲለፈልፍ ሰምቶ፤መጽሐፈ አርጋኖ የየእለቱን ጸሎት አልፎ አልፎ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር በመጨመር ከጸለየ በኋላ በመጨረሻ የሚጸልየዉ የራሱ ፀሎት የሚከተለዉ ነዉ፡፡

«+በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ አሜን፡፡ ያልኖርክበት ጊዜ የሌለ የማትኖርበት ጊዜም የማይኖር፣ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ አልፋና ያሜጋ፣ ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣህ ከፈለክም በፈለከዉ ጊዜ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የምትችል፣ ሁሉ ያንተ በአንተ የሆነ፣ ካላንተ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል ሃያል ገናና አምላክ ፈጣሪያችን አባታችን ጌታችን መድኃኒታችን እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፤ እኔ ከጥንብ አንሳ፣ ከሞተ ዉሻ፣ ከአፈር፣ ከአመድ፣ ከትል፣ ከጥራጊ ቆሻሻ፣ ከጅብ፣ ከአይጥ፣ ከእንሽላሊት፣ ከአዞ፣ ከእባብ፣ ከነቀዝ፣ ከበጠጥ፣ ከእበት፣ ከአዛባ፣ ከፋንድያ፣ ከኩስ፣ ከአር፣ ከቅዘን፣ ከመግል፣ ከሽንት፣ ከትፋት እኩል ልቆጠር የማይገባኝን፤ ምክንያቱም እነዚህ ከመሸተት፣ ከመጠንባት፣ ከመግማት ዉጭ በአንተ ላይ የማያምጹ እኔ ግን ከመሸተትና ከመግማት በተጨማሪ ትዕዛዝህን እየጣስኩ እንደ ቃልህ የማልኖር ህግህን ያፈረስኩ፤ የአመጸኞች ዋና አመጸኛ፣ የርኩሳንም ዋና ርኩስ፣ የከሃድያንም ዋና

ከሃዲ፣ የሆንኩትን ሰዉ እንደሰዉ ቆጥረኸኝ ምህረትህንና ቸርነትህን አብዝተህልኝ በሰላም በጤና አሳድረኸኝ ለዚህች ሰዐት ስላደረስከኝ ዛሬም ዘወትርም ለህያዉነት ዘመን አመሰግንሃለዉ፤ አመሰግንሃለዉ፤ አመሰግንሃለዉ።

ሊያልፍ፣ ሊሻሻል፣ ሊቀር በማይችለዉ አምላካዊ ቃልህ «ለምኑ ይሰጣችኋል አንኳኩ ይከፈትላችኋል እሹ ታገኙማላችሁ» ብለሃልና የዘወትር ልመናዬና ማንኳኳቴ መሻቴ ራሴን ለአንተ ማዘጋጀት የተሳነኝ፣ ተስፋዬና ሩጫዬ ምድራዊ ስለሆነ ለአንተ እንደምገባ አንተዉ ራስህ በአምላካዊ ስልጣንህ አዘጋጅተኸኝ ሰዉ አድርገኸኝ ለማታልፈዉ ሰማያዊ መንግስትህ ታበቃኝ ዘንድ ነዉ። «ሰዉ አለሙን ቢገዛ ቢነዳ ነፍሱን ካላተረፈ ምን ይጠቅመዋል ምን ይረበዋል » ብለሃልና፤ በዚህ ዓለም ሁሉ የኔ ቢሆንና ከመንግስትህ የምለኝ ከሆነ ምን ጥቅም አለዉ? ለዚያዉም ያደፈና የጎሰቆለ ባህርይ ይዤ እየተመላለስኩ፤ ይኸዉም ለዉሱን አመት።ስለዚህ ከንቱ ነኝና ለሰማያዊ ህይወት የሚያበቃ ቅድስና ህይወት ስጠኝ።እንደምታየኝ እኔ የአለም የመጨረሻ ልክስክስ ክፋት ክርፋት የሞላብኝ ነኝና ለሰይጣናት ፈተን አሳልፈህ አትስጠኝ፤ እኔ አልችላቸዉም፤ እነእርሱ የክፋት፣ የተንኮል፣ የአመጻ፣ የእርኩሰት ጥበበኞች ናቸዉና በምን መንገድ መተዉ እንደሚያሰናክሉኝና እንደሚጥሉኝ የማላቅ ተራ ደካማ ወራዳ ኃጢአተኛ ሰዉ ነኝ።

እግዚአብሔር ሆይ፤ስለ እናትህ ቅድስተ ቅዱሳን ንጽህይተ ንጹሐን ድንግል ማርያም ስትል፣ ስለ ቅዱሳን መላእክት ስትል፣ ስለ ጻድቃን ሰማዕታት ነብያት ሐዋርያት፣ በዚህ ምድር ስለ እዉነት ስለሚያዝኑ ስትል፣ አለም ሁሉ ነገረ መስቀልህን እንዲያዉቅ፤ ማወቅ ብቻ አይደለም እንዲያስተዉል አድርግ፤እንደኔ እያወቀና እያስተዋለ የድፍረት በደልን እየፈጸመ እንዳያሳዝነህ ደግሞ አንተን መፍራት በልቦናችን ዉስጥ አኑርልን። ፈቃድህ ከሆነ ይህን ማድረግ ትችላለህ በአንተ ዘንድ ይህ እጅግ ቀላል ነዉ። እንኳን ይህ ቀላሉና መልካሙ ነገር ቀርቶ ለሰዉ ልጅ ሕሊና እጅግ የሚከብደዉንና የሚዘገንነዉን ሊደረግ የማይችለዉን ነገር ግን የተደረገዉን ታላቅ ነገር አድርገህልናል ይኸዉም በአምላካዊ ስልጣንህ ሁላን ማድረግ የምትችል «ለምን ይህን አደረክ?» ብሎ የሚጠይቅህ የሌለ፣ ሁሉን እንደወደድክ ማድረግ ስትችል መለኮታዊ ባህርይን ዝቅ አድርገህ ይህን ደካማ ስጋችንን በመልበስ ሰዉ ሆንክ፤ በምድር ላይ ተመላለስክ ፤ በፍጡርህ እጅ ብዙ መከራ ተቀበልክ ፤ ያም ሳይበቃህ በመስቀል ላይ ተሰቀልክ ፤ ታድያ ይህን ከባዱን ያደረክ አምላክ ሰዎች ሁሉ እንደፈቃድህ እንዲመላለሱና በቀራኒዮ አደባባይ በመስቀል ላይ የተቸነከርከዉ አንተ አባባ አምላካችን እንደሆንክ ተረድተዉ በእዉነት እንዲያመልኩህ ማድረግ ትችላለህ።ስለዚህ ያለፈዉ የአመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ዘመናችን ይብቃን። ያንተ ፈቃድ ብቻ የሚፈጸምበት ሰማያዊ ስርዐት ዘርጋልን።ንጉሳችን አስተዳዳሪያችን መጋቢያችን አንተ ብቻ ሁን። መድረኮች ሁሉ ያንተ ይሁኑ አንተ ከፍ ከፍ የምትልበት፣ ነገረ መስቀልህ የሚነገርበት ይሁን።የዲያብሎስ ባለጊዜነቴ ይሻር። በሰማያት ዉስጥ ያንተ ፈቃድ ብቻ እንደሚፈጸም ሁሉ በዚህች ምድር ላይም ያንተ መልካም ፈቃድ ብቻ እነዲፈጸም አደርግ። እኛ በራሳችን ስልጣን እንኳን መስራትና መናገር ቀርቶ ማሰብ የማንችል ደካማ ሰዎች ነን ።ይህ ሁሉ ልመናዬ ከኔ ከኃጢአተኛዉ ከንፈር ማለፍ የማይችል ቢሆንም በእናትህ ንጽህይት ድንግል ማርያም፣ በቅዱሳኖችህ አንደበት ተጣርቶና ተስተካክሎ እንዲቀርብልኝ ነዉ ልመናዬ ።

(ዉስጡ ስለ እዉነት ሲቃጠል አልፎ አልፎ እዚህ ላይ የሚጨምረዉ ጸሎት፣እግዚአብሄር ሆይ፤ የሰይጣናትን ስጦታ አንዳች አልፈልግም ህብረቴም አንድነቴም ካንተ ጋር ብቻ እንዲሆን ነዉ ልመናዬ። ሳይገባኝ ብዙ ምስጢራትን እንዳዉቅና ነገረ መስቀልህንም እንዳስተዉል አድርገኸኛል፤ ነገር ግን ባወኩት እዉነት ዉስጤ እየተቃጠለ ለአመታት እነዲሁ ምንም ሳልሰራ እመላለሳለሁ፤ወደ አንተ ብትጠራኝ ደግሞ ራስ ወዳድ እንደሆንኩ አድርጌ ነዉ ራሴን የምቆጥረዉ፤ምክንያቱም ያወኩትን

እዉነት ለሌላዉ ካላሳወኩና ፍሬ ካላፈራዉ እቆጫለሁና::ስለዚህ እግዚአብሄር ሆይ፤ የበለአምን አህያ ያናገርክ ከፈለክም ህይወት የሌለዉን ፍጥረት ማናገር የምትችል የማይገባኝ ብሆንም እኔን በአርያህና በአምሳያህ የፈጠርከኝን ታዲያ እንዴት አብልጠህ ልታናግረኝ አትችል!? እጅግ ትችላለህ :: «ካለ እኔ አንዳች ልታደርጉ አትችሉም» ብልሃልና:: አንተ ስታናግረኝ ስታሰራኝ ብቻ ነዉ ፍሬ ላፈራ የምችለዉና ፈቃድህ ከሆነ ስለ እዉነት እነድመሰክር ፍሬ እንዳፈራ ብታደርገኝ :: እዉነትን ባትገልጽልኝ ኖሮ እነዲሁ ተመላልሼ ወደ አንተ ብመጣ ምንም አይመስለኝም፤ አሁን ግን እዉነትን ስላወኳት አንተንም ከመዳሰስ ባላነሰ መልኩ ስላወኩህ ስለ እዉነት ሳልመሰክር ወደ አንተ ብትጠራኝ እጅግ ይቆጨኛል:: እግዚአብሄር ሆይ፤ እኔ ዋንኛ ኃጢአተኛዉን ሰማያዊ ምስጢርህን እንድረዳ የፈቀድክ አምላክ ፤ አለም ባለማወቅ ነዉና በኃጢአት የሚመላለሰዉ፤ ከኔ ርኩሰት ጋር ሲነጻጸር እነሱ ቅዱሳን ናቸዉና እንዴት አብልጠህ የበለጠዉን ምስጢር አታሳዉቃቸዉ? ታሳዉቃቸዋለህ እንጂ፤ እግዚአብሄር ሆይ፤ ፈቃድህ ከሆነ በዉስጤ ስለሚቃጠልበት እዉነት እንድመሰክርና ፍሬ እንዳፈራ ካደረከኝ አሟሟቴም አንተን የማከብርበት፣ ቅዱሳኖችህ ቁልቁል እንደተሰቀሉ፣ በሰይፍ እንደተሰየፉ፣ እንደተቃጠሉ፣ለአራዊት እንደተሰጡ፣እንደተፈጩ፣ እንደተሰነጠቁ፣ ቆዳቸዉ ተገፎ እንደተሰቃዩ፣ እኔ ደግሞ ስጋዬና አጥንቴ እንዳይገኝ ወደ ላይ ወደ ሰማይ በኢልኮፍትር ተንጠልጥዬ ከተወሰድኩ በኋላ ወደዚህች መሬት አስፋልት ወይንም አለት ላይ እንድወረወርና ሁለመናዬ ብትንትን ብሎ እንዲጠፋ ወይንም በእሳተ ገሞራ ዉሰጥ መላ አካሌ እንዲጣል በዚያም ሁለመናዬ እንዲቀልጥ በዚህ መልኩ በሞቴ እንዳከብርህ ነዉ ልመናዬ:: አንተን ሆነ እማን(እመቤታችን ድንግል ማርያምን) እንዲሁም ቅዱሳኖችህን በዚህ ቅርፊት ስጋዬ እያለሁ ማየት ሆነ የሚሰማዉን ድምጽ መስማት አልፈልግም፤ እንዲሁ ካለድምጽ ተናገረኝ የምትፈቅደዉን ብቻ ግለጽልኝ::)

ሰላም ለኪ፤እሰግድ ለኪ፤እሰግድ ለኪ፤እሰግድ ለኪ፤ ድምጹ በማያምር ዜማ ንዒ ሀቤዬ ኦ ድንግል ምሰለ ወልድኪ ፍቁርኪ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ንዒ ሀቤዬ ኦ ድንግል ምሰለ ቅዱሳን ወመላእክት፤ ንዒ ሀቤዬ ኦ ድንግል ምሰለ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ነብያት፣ ሐዋርያት ወቅድስት አርሴማ፣ ወእገሌ(በእለቱ የሚታሰብ ቅዱስ ስም):: እመቤትዬ ንጽህይተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን የአዳም ተስፋ የኖህ መርከብ የአብርሃም ድንኳን የያዕቆብ መሰላል የሙሴ ፅላት የአሮን በተር የሳሙኤል ሽቱ ሙዳይ የዳዊት በገና የጌድዮን ጸምር የኤልያስ ደመና የኤልሳ ማሰሮ የናሆም መድኃኒት የነብያት ትንቢት የሐዋርያት ስብከት የጻድቃን እመቤት የደናግል መመኪያ የአደራ እናታችን እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፤ አመሰግንሻለሁ፤ አመሰግንሻለሁ፤ አመሰግንሻለሁ:: ነፍሴንም ስጋዬንም ላንቺ አደራ አስረክቤአለሁ፤ ነፍሴን ለሰማያዊ ክብርና መንግስት አብቂያት፤ ስጋዬንም ከዚህ ምድራዊ ጉስቁልና ህመም ችግር ፈተና ጠብቂዉ :: ይህች አስራት ሀገርሽን አስቢያት የሰላም የፍቅር የበረከት የእምነት ሀገር አድርጊያት:: ቤተ ክርስቲያንን ጠብቂ::ምስኪኖችንም አስቢያቸዉ ከማይፈልጉት ህይወት ለያቸዉ::

እናንተ ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ነብያት፣ ሐዋርያት፣ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ (የሥላሴ) ባለሟሎች ወዳጆች ሁሉ እናንተም ክበሩልኝ ተመስገኑልኝ:: እኔ ዉዳቂ ባርያችሁን እገሌ ባርኩኝ፤የምሰራዉን ስራ የማላዉቅ ነኝና ቀኝ እጅ ሆናችሁ የምታሰሩኝ እናንተ ሁኑ፤ የምናገረዉን አላዉቅምና አንደበት ሆናችሁ የምታናግሩኝ እናንተ ሁኑ፤ የማስበዉን አላዉቅምና አእምሮ ሆናችሁ የምታሳስቡኝ እናንተ ሁኑ እንጂ፤ እንደዚህች እንደምትፈሰዉ አይኔ፣ እንደሚፈረካከሰዉ ስጋዬ፤ አሩን፣ ቅዘኑን፣ ጥምቡን ማቆሪያ እንደሆነዉ ሆዴ ፈቀድ ተመርቼ አንዳች የመስራት የመናገር የማሰብ ስልጣን አይኑረኝ:: እናንተ መርታችሁኝ የምታሰሩኝ፣ የምታናግሩኝ፣ የምታሳስቡኝ ከሆነ ፍጹም የእግዚአብሄር የሆነዉን ማከናወን እችላለዉና:: ምክንያቱም ፍጹም

የምትሰሩት እግዚአብሄር የሚያሰራችሁን ነዉና፤ የምትናገሩት እርሱ እግዚአብሄር የሚያናግራችሁን ነዉና፤ የምታስቡት እርሱ የሚያሳስባችሁን ነዉና ::ዓለሙንም የሰላም የፍቅር የበረከት የእምነት አድርጉ:: አቡነ ዘበሰማያት::ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ምስጋና ይሁን ለእመቤትዬ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም፤ምስጋና ይሁን ለቅዱሳን መላእክት ጻድቃን ሰማዕታት ነብያት ሐዋርያት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለሥላሴ ባለሟሎችና ወዳጆች:: » በማለት ነበር በ አስራ ስምንቱ(18) አመት መንፈሳዊ ህይወቱ ቆይታ ይጸልይ የነበረዉ::

*ማን ያዉቃል ይህ የማሃይምነቱና የጅልነቱ ጸሎት ትሆን ለዚህ መልእክት አስተላላፊነት ያስመረጠዉ!?*

ወስብሐት ለእግዚአብሄር ወለወላዲቱ ድንግል

*መስከረም 2003 ዓ.ም.ከሀገረ እግዚአብሄር ኢትዮጵያ*

ጸሐፊዉ የታዘዘዉን መልእክት ጽፎ፣ በኮምፒተር ጽሑፉን ካወጣና በዚህ ፈታኝ ዘመን በእምነት ጽናታቸዉና በአገልግሎት ትጋታቸዉ ምክንያት እግዚአብሄር ለመረጣቸዉ ለራሱ ዓላማ በዚህ ዘመን ላስነሳቸዉ አካላት በታዘዘዉ (ተገናኛቸዉ በተባለዉ) መሰረት ይወክላቸዋል ብሎ ለገመተዉ ግለሰብ መጽሐፉን ካስረከበ በኋላ፤ወደፊት ምን እንደሚሆን ስለ ራሱ በእርግጠኝነት ያላወቀዉ ለዚህ መልእክት አስተላላፊነት ሳይገባዉ በመመረጡ ሐዘንተኛ የሆነዉ ሰዉ መስከረም፳፱፥፳፻ወ፫ (29/2003) ዓ.ም. የቅድስት አርሴማ ዓመታዊ መታሰቢያዋን በዐል ለማክበር በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ቅዳሴ እያስቀደሰ እያለ ሁለት ሰአት ላይ በተለመደዉ የማይሰማ ድምፅ በቀጣይ ምን እንደሚሆን ተነግሮታል:: መልእክቱንም በደስታ ሳይሆን  በሐዘንና በለቅሶ ነዉ የተቀበለዉ:: ሁለተኛዉ ሐዘን ሆኖበታል:: አቀባበሉም እንደሚከተለዉ ነዉ: የዶሮ ኩስ ሁላችሁም እንደምታዉቁ እገምታለሁ፤ የዶሮ ኩስ ላይ የወርቅ ወይንም የከበረ ማዕድን ከእንቁ የተሰራ አክሊል ቢደረግለት ምን አይነት ስሜት ይሰማዋል? መልሱ ምንም አይነት ስሜት አይሰማዉም:: ጸሐፊዉም እንደ ኩሱ ስሜት ነዉ የተሰማዉ:: ትዕዛዙን አልቀበልም ማለት ስለማይቻል ስጦታዉን በሐዘንና በኩስ ስሜቱ ተቀብሎታል::

ስለዚህ አሁንም ወደፊትም ይህን ኩስ በአክሊል ዉስጥ ብታዩት ለኩሱ አንዳች ቦታ እንዳትሰጡት፤ ብታወድሱት፣ ብታገኑት ምንም አይነት ስሜት የማይሰማዉና ስላወደሳችሁትና ስላገነናችሁት አንዳች የተለየ ነገር የሚያደርግላችሁ አይደለም:: ኩሱን እንደ ሰዉ ቆጥሮ ለዚያ አክሊል የሚያበቃዉን ያን ምስኪን አባት፣ ምንም የሚሳነዉ ነገር የሌለ፣ ሁሉን በአምላካዊ ስልጣኑ ማድረግ የሚችል፣ የሁሉ ፈጣሪና አስገኝ፣ አልፋና ያሜጋ የሆነ፤ ስለ ሰዉ ልጆች ሲል ሲሰደብ፣ ሲገረፍ፣ ሲተፋበት፣ ሲዘበትበት፣ ሲወነጀል፣ሲያዳፉት፣ መስቀል ሲያሸክሙት፣ ሲቸነክሩት እንደ አቅመ ቢስ ዝም ያለ፤ ፍቅሩን በመስቀል ላይ ስጋዉን በመቁረስ ደሙን በማፍሰስ የገለጸዉን እዉነተኛዉን አምላክ እግዚአብሄር ኢየሱስ ክርስቶስን አመስግኑ፤ አግንኑ፤ ትዕዛዙንና ሕጉን ጠብቁ፤እንደ ቃሉ ሆናችሁ  ተገኙ ፤ ከእርሱ ዋጋ ታገኛላችሁና:: እንዲሁም ያችን ምስኪን እናት፣ ለሁለት ሺህ ዘመን ለሰዉ ልጆች ድኅነት ስትል በሐዘን ያላቸዉን፤ በእርሷና በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ሰዎች ሐዘንና ምልጃ አማካይነት የዲያብሎስ ስርዐት ተሽሮ በምትኩ ሰማያዊ ስርዐት የሚዘረጋበት መልካም ዘመንን እግጅ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የምታስመጣዉንና የምታመጣዉን፣ በስጋም በነፍስ ዋጋ የምታሰጠዉን፣ ይህን ዉዳቂ ኃጢአተኛን ሰዉ ከኩስነት ማእረግ አዉጥታ ለዚያ አክሊል የምታበቃዉን፤ የአደራ እናታችንን እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ እመቤታችን ቅድስት  ድንግል ማርያምን አመስግኑ፤ አግንኑ:: ሰዎች በስልጣናቸዉ ተጠቅመዉ ግፍን፣ አመጻን፣ ርኩሰትን፣ ክህደትን፣ በደልን፣ አድሎን በአጠቃላይ የዲያብሎስን ስራ የፈጸሙበትን፣ ያስፈጸሙበትን፣ ራሳቸዉን ያገነኑበትን፣ ያስመለኩበትን፣ የተለየ ነገር አድርገዉ የቆጠሩትን ከንቱና ተራ መሆኑን ለማሳየትና የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ብቻ ኢትዮጵያና አለም ተላልፋ ከተሰጠችዉ ከተቀባዉ የድንግል ማርያም ባለሟልና ምርጥ ልጅ ስር ሆኖ ለማገልገል ሳይገባዉ ስጦታዉን በጸጋ ተቀብሎታል::

ጸሐፊዉ በመስከረም ወር ፳፻፫ (2003) ዓ.ም. ወደ ሕሊናዉ የመጣለትን የእግዚአብሄር መልእክት በመቀመሪያ(በኮምፒተር) ጽፎ በሶፍት ኮፒና በሐርድ ኮፒ ለሚመለከተዉ አካላት ተወካይ ሰቶ የእግዚአብሄርን ፈቃድ እየተጠባበቀ ሳለ ከጥቅምት 1/2003 ዓ.ም. ጀምሮ «ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት የተደበቁ ምስጢሮች የተገለጡበት እና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት አንደኛ መጽሐፍ» በሚል ርዕስ በ1997 ዓ.ም. የተጻፈዉን ያነበበና የመጽሐፉ ጸሐፊን እግዚአብሄር ለተለየ አላማዉ ያዘጋጀዉና የተጻፈዉም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደሆነ ተገንዝቧል:: ከዚያም ቀጥሎ እስካሁን ድረስ « ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ!» በሚል ርዕስ 1993 ዓ.ም.«የምስራች» በሚል ርዕስ በ2001ዓ.ም. «ኢትዮጵያዊዉ፣ በማንነቱ ፍለጋ!» በሚል ርዕስ በ1991 ዓ.ም.የተጻፉ መጽሐፍቶችን በተከታታይ ያነበበ ሲሆን ያዉ እዉነትን የሚያጽፈዉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ በመሪነት ያጻፈዉ መሆኑንና ለዚህ ትዉልድ መፈራረጃ እንደሚሆንበት ተረድቷል::

የጸሐፊዉ ምክር የአዳምና ሔዋን ዘሮች ወይንም የወንድማማቾቹ የካም፣የሴም፣የያፌት ልጆች ወይንም የሶስቱ ነገዶች ዉህድ የሆነዉ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፤በመጽሐፍቶቹ እንደተገለጸዉ ኢትዮጵያዊዉ ሆነ ሌላዉ የዓለም ህዝብ በዚህች ምድር ዉስጥ በመከራና በችግር፣ በጠብና በጦርነት ፣ በቂም በቀልና በጥላቻ፣ በግፍና በአመጻ፣ በክህደትና በርኩሰት የሚመላለሰዉ ቅዱስ ኪዳኑን ባለመጠበቁና በማፍረሱ ስለሆነ በረከተ ስጋና ድኅነተ ነፍስ ለማግኘት ቅዱስ ኪዳኑን ሊጠብቅ ይገባዋል::ይህም በምድራዊ ዘመኑ በሰማያዊ ስርዐት በመመላለስ መልካሙን በረከት ለማግኘትና ከዚህ ቅርፊት ስጋዉ ሲለይ ደግሞ በእግዚአብሄር መንግስት ፍጹም የሆነዉን ደስታና ቅድስና አግኝቶ ሕያዉ ሆኖ እንዲኖር ነዉ:: ቅዱሱን ኪዳን ቢጠብቅ ጥቅሙ ለራሱ ነዉ ባይጠብቅ ደግሞ የሚጠፋዉና መከራና ፍዳዉን በዚህ ዓለምም ከሞት በኋላ ባለዉ ህይወት የሚቀበለዉ እራሱ ነዉ::ምርጫዉ ለእያንዳንዱ ሰዉ ክፍት ነዉ:: ያዋጣኛል ብሎ የፈለገዉን መከተል ይችላል::

ከመቶ በላይ የሆኑ የአገራት መሪዎች በበላይ ዲያቢሎስ የሚመራቸዉ የርኩሰት፣ የክህደት፣ የአመጻ፣ የግፍ ሥራ አስፈጻሚዎች በዓለም ማምጣት ያልቻሉትን ሰላምና ፍቅር፣ እዉነተኛ እምነትና አንድነት፣ ቅዱሱን ኪዳን በጠበቁ በኢትዮጵያዉያን ሲመጣ ዓለም ምን ይል ይሆን!? ይህ ለስልጣን፣ ለክብር፣ ለዝና፣ ለጥቅም ሕሊናዉን የሸጠ ትዉልድ በእግዚአብሄር ላይ ያመጸበት ነገሮች ሁሉ ከንቱ ሲሆኑበትና የዘራዉን የአመጽ ዋጋ እያንዳንዱ አገር ሲያጭድ ምን ይዉጠዉ ይሆን !? እግዚአብሄር የስልጣን ጥመኞችን ለማሳፈር ኢትዮጵያ ሆነች ዓለም በእግዚአብሔር በተመረጡትና በተቀቡት በኢትዮጵያዉያኑ በአንድ ንጉሠ ነገሥትና በአንድ እጨጌ እንድትመራ ሲያደርግ የአመጻ ልጆች ምን ይሉ ይሆን!? ከእግዚአብሄር ቁጣና መቅሰፍት ከጥፋት ማዕበል ተርፈን እጅግ በቅርቡ በሚመጣዉ የእግዚአብሄርን መንግስት ( ሰማያዊ ስርዐት የሚዘረጋበትን መልካም ዘመን) ለማየት በቅንነትና በእዉነት፣ በየዋህነትና በትሁት ስብዕና የምንመላለስ ሰዎች እንገኝ ይሆን !? የቅዱሱ ኪዳን ባለቤት የሆን ኢትዮጵያዉያን በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና አመጻ የፈጸምን ካለፈዉ ጥፋት መማር ያልቻልንና በበደል ላይ በደልን የፈጸምን በስጋዊዉም በመንፈሳዊዉም ወንበር ላይ የተቀመጥን የዘመኑ የጥፋት ዉሃ ሲመጣ የት ይሆን መግብያችን!? እዉነትን ይዘን በእዉነት ላይ በማመጻችን ምክንያት ከሁሉ በላይ በዓለም ዘንድ ማፈሪያ መሆናችን የማይገለጽብን ይመስለናል!?

ህዳር11/2003 ዓ.ም.